# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩመኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ድኅረ ምረቃ መርሐግብር

# በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት

በ

ተሻለ ክፍሌ

ሰኔ፣ 2005 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

# በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት

በ

ተሻለ ክፍሌ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩመኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐግብር

ለ በግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛ ቋንቋን ለማስተማር ኤም. ኤ. ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ሰኔ፣ 2005 ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩመኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## ድኅረ ምረቃ መርሐግብር


# በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት


በ

ተሻለ ክፍሌ


ሰኔ፣ 2005 ዓ.ም.

## የፈተና ቦርድ አባላት

| | | |
|---|---|---|
| 1. [illegible] | [illegible] | [illegible] |
| አማካሪ | ቀን | ፊርማ |
| 2. [illegible] | 27/10/05 | [illegible] |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |
| 3. [illegible] | [illegible] | 27/10/05 |
| ፈታኝ | ቀን | ፊርማ |

# ምስጋና

ይህን ጥናታዊ ጽሑፍ ባዘጋጀሁበት ወቅት ከንድፈ-ሐሳቡ ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ እያንዳንዱን ምዕራፍ ደጋግሞ በማረምና አቅጣጫ በማስያዝ ሙያዊ እገዛ ላደረጉልኝ አማካሪዬ ለዶ/ር አረጋ ኃይለሚካኤል (ተባባሪ ፕሮፌሰር) ያለኝ አክብሮትና ምስጋና ወሰን የለውም፡፡

በመቀጠል ለሁለት ዓመታት በዩኒቨርሲቲው በነበረኝ ቆይታ በሞራል፣ በሐሳብ፣ በቁሳቁስና በገንዘብ እገዛው ላልተለየኝ ለታላቅ ወንድሜ አበራ ክፍሌ፣ እንዲሁም መመረቂያ ጽሑፉ በታቀደለት የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቅ ይረዳኝ ዘንድ ላፕቶፕ ኮምፒዩተር በማዘጋጀት የበኩሉን አስተዋጽኦ ላበረከተልኝ ለታናሽ ወንድሜ ሀብተየሱስ ክፍሌ ያለኝን ልባዊ ምስጋና ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

የመመረቂያ ጽሑፉን ለማከናወን የሚያስፈልገውን በጀት በመመደብ እገዛ ላደረገልኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በጥናቱ ሂደት አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ በሆሳዕና ከተማ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መምህራን እና ለሥራው መሳካት የበኩላቸውን አስተዋጽኦ ላበረከቱልኝ ግለሰቦች በሙሉ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ከዚህ ባሻገር ባገኘሁት የትምህርት ዕድል ተጠቃሚ እንድሆንና የትምህርት ቆይታ ጊዜያትን ወጪዎች እንድሸፍን ደመወዝ በመፍቀድ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገልኝን የሀዲያ ዞን ግቤ ወረዳ ትምህርት ጽሕፈት ቤትን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

በመጨረሻ ሁሌም በትምህርቴ የላቀ ደረጃ ላይ እንድደርስ ለሚመኙልኝ ለሴት አያቴ ሴሞ ሌንደሞ፣ ለእናቴ (ኢቴ) ኤርቃሌ ኤረኖ እና ለአባቴ (ዳኛ) ክፍሌ ጌሴሾ፣ እዚህ የመድረሴ ምስጢር የእነሱ ድጋፍና ፀሎት ናውና ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ምስጋና ............ i
ማውጫ ............ ii
የሠንጠረዥ ማውጫ ............ v
አጠቃሎ ............ vi
ምዕራፍ አንድ፣ መግቢያ ............ 1
1.1. የጥናቱ ዳራ ............ 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 3
1.3. የጥናቱ ዓላማ ............ 4
1.4. የጥናቱ አስፈላጊነት ............ 4
1.5. የጥናቱ ወሰን ............ 5
ምዕራፍ ሁለት፣ ክለሳ ድርሳናት ............ 6
2.1. የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት ............ 6
2.1.1. የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንነት ............ 6
2.1.2. የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዓይነቶች ............ 7
2.1.2.1. ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት ............ 7
2.1.2.2. ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት ............ 8
2.1.3. የመማሪያ መጻሕፍት ባሕርያት ............ 9
2.1.3.1. እውነተኛነት ............ 9
2.1.3.2. ግልጽነት ............ 9
2.1.3.3. ተለጣጣቂነት ............ 10
2.1.3.4. ተግባራዊነት ............ 10
2.1.3.5. ተገቢነት ............ 10

2.1.4. የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች ....................................................11
2.1.4.1. የማዳመጥ ክሂል ....................................................11
2.1.4.1.1. የማዳመጥ ክሂል ምንነት ....................................................11
2.1.4.1.2. የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ዓላማ ....................................................13
2.1.4.1.3. የማዳመጥን ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎች ....................................................14
2.1.4.2. የንግግር ክሂል ....................................................15
2.1.4.2.1. የንግግር ክሂል ምንነት ....................................................15
2.1.4.2.2. የንግግር ክሂል ትምህርት ዓላማ ....................................................16
2.1.4.2.3. የንግግርን ክሂል የማስተማሪያ ብልሃቶች ....................................................16
2.1.4.3. የንባብ ክሂል ....................................................17
2.1.4.3.1. የንባብ ክሂል ምንነት ....................................................17
2.1.4.3.2. የንባብ ክሂል ትምህርት ዓላማ ....................................................19
2.1.4.3.3. የንባብን ክሂል የማስተማሪያ ብልሃቶች ....................................................20
2.1.4.4. የጽሕፈት ክሂል ....................................................21
2.1.4.4.1. የጽሕፈት ክሂል ምንነት ....................................................21
2.1.4.4.2. የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ዓላማ ....................................................22
2.1.4.4.3. የጽሕፈትን ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎች ....................................................23
2.1.5 የቋንቋ ክሂሎች ይዘትና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ....................................................25
2.1.5.1. የቋንቋ ክሂሎች ይዘት ምንነት ....................................................25
2.1.5.2. የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ ምንነት ....................................................26
2.1.5.3. የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ አቀራረብ ....................................................26
2.1.5.4. የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ አደረጃጀት ....................................................27
2.1.5.4.1. ተከታታይነት ....................................................27
2.1.5.4.2. ተለጣጣቂነት ....................................................27

2.1.5.4.3. ውህደት ..........27

2.2. የቀደምት ጽሑፎች ቅኝት ..........28

ምዕራፍ ሦስት፣ የአጠናን ዘዴ..........31

3.1. የመረጃ ምንጮች ..........31

3.2. የናሙና አመራረጥ ..........32

3.2.1. የጥናቱ ክልል አመራረጥ ..........32

3.2.2. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ..........32

3.2.3. የዘጠነኛ ክፍል አመራረጥ ..........33

3.2.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ ..........33

3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ..........34

3.3.1. የሰነድ ፍተሻ ..........34

3.3.2. የጽሑፍ መጠይቅ ..........35

3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ ..........35

ምዕራፍ አራት፣ የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት ..........36

4.1. የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ ..........37

4.2. የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አደረጃጀት ..........85

ምዕራፍ አምስት፣ ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ ..........90

5.1. ማጠቃለያ ..........90

5.2. የመፍትሔ ሐሳብ ..........93

ዋቢ ምንጮች ..........94

አባሪዎች፣ ..........ሀ

አባሪ አንድ፣ በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ ..........ለ

አባሪ ሁለት፣ የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ..........ሠ

አባሪ ሦስት፣ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ..........ሰ

አባሪ አራት፣ የድኅረ ንባብ ጥያቄዎች ..........ሸ

# የሠንጠረዥ ማውጫ

ርዕስ ገጽ

ሠንጠረዥ 1፣ የጽሑፍ መጠይቅ ስለሞሉ መምህራን የተገኘ አጠቃላይ መረጃ ...................36

ሠንጠረዥ 2፣ መልመጃዎቹ ለመማር ማስተማርና ለክሂሎች ልምምድ ያላቸው አመቺነት...38

ሠንጠረዥ 3፣ ክሂሎች በምዕራፎቹ ውስጥ ርዕስ ተሰጥቷቸው የቀረቡበት ደረጃ .................41

ሠንጠረዥ 4፣ አራቱም የቋንቋ ክሂል ይዘቶች በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡበት ሁኔታ ............41

ሠንጠረዥ 5፣ የክሂል መልመጃዎቹ በተገቢ ሁኔታ እንዲሁም ተሟልተው ስለመቅረባቸው..43

ሠንጠረዥ 6፣ የክሂል መልመጃዎች አቀራረብ ማራኪ፣ ሳቢና ተገቢ ስለመሆናቸው ............45

ሠንጠረዥ 7፣ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ያገናዘቡ
ስለመሆናቸው ....................................................................................49

ሠንጠረዥ 8፣ የክሂል መልመጃዎቹ ተግባራዊ፣ ግልጽና የተለመዱ ዓይነት ስለመሆናቸው...51

ሠንጠረዥ 9፣ የክሂል መልመጃዎቹ የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት ያላቸው ብቃት ............56

ሠንጠረዥ 10፣ የክሂል መልመጃዎቹ በተገቢ የማስተማሪያ ብልሃቶች ስለመታገዛቸው .......59

ሠንጠረዥ 11፣ ስለመልመጃዎች አተገባበር ዘዴ የቀረቡት ትዕዛዞች ..................................77

ሠንጠረዥ 12፣ የክሂል መልመጃዎቹ አዘገጃጀት ተማሪዎች ቋንቋውን እንዲለማመዱ
ስለመሆናቸው ....................................................................................78

ሠንጠረዥ 13፣ የክሂል መልመጃዎቹ ጥያቄዎች የቀረቡበት ስልት ...................................84

ሠንጠረዥ 14፣ የክሂል ርዕሶች በመጽሐፉ ውስጥ ያላቸው አደረጃጀት ..............................86

ሠንጠረዥ 15፣ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አደረጃጀት ............................................88

# አጠቃሎ


የዚህ ጥናት ዓላማ በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መተንተን ነው፡፡ በዚህ ዓላማ መሠረት በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ፍተሻ በማካሄድና ለጥናቱ በተመረጠው የክፍል ደረጃ በሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽሑፍ መጠይቅ በማስሞላት የቋንቋ ክሂል ይዘቶችን አቀራረብና አደረጃጀት ለመተንተን ለጥናቱ የሚረዱ መረጃዎች ተሰብስበዋል፡፡ ከሰነድ ፍተሻና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት አኳያ ተተንትነዋል፡፡ ከመረጃዎቹ የተገኙት ውጤቶች የሚያመለክቱት በክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ጠንካራና ደካማ ጎኖች መኖራቸውን ነው፡፡ ጠንካራ ጎኖቹ፡- የክሂል ይዘቶች አቀራረብ ለመማር-ማስተማሩ ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ የክሂል ልምምድ አመቺ መሆናቸውን፤ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜና ችሎታ እንዲሁም ዳራዊ ዕውቀታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን፤ የክሂል መልመጃዎቹ ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን ለሚያካሄዷቸው የቋንቋ ክሂል ልምምዶች አጋዥ መሆናቸውን፤ ወዘተ. የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ በአንጻሩም ደካማ ጎኖቹ፡- የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ያለመጣጣም ችግሮች መኖራቸውን፤ የማዳመጥ ክሂል ይዘት ከመለማመጃ ጥያቄዎች ጋር በበቂ ሁኔታ ተካቶ አለመቅረቡን፤ አልፎ አልፎ ስለመልመጃዎች አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ መካተታቸውን፤ የተወሰኑ ክሂሎች (ማዳመጥና ጽሕፈት) በተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶች ታግዘው አለመቅረባቸውን፤ የክሂል ይዘቶቹ ወጥነት ባለው መልኩ ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተልንም ሆነ የክብደት ደረጃ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው የተደራጁ አለመሆናቸውን፣ ወዘተ. ጥናቱ አረጋግጧል፡፡ በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ የሚያስችሉ ስልቶች በመፍትሔ ሐሳቦች ስር ተጠቁመዋል፡፡ በመሆኑም ይዘቶቹ በተጠቆሙት ሐሳቦች መሠረት ማስተካከያ ቢደረግባቸው መጽሐፉ ይበልጥ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል የአጥኚው አስተያየት ይጠቁማል፡፡

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ የሰው ልጆች እርስ በርስ በንግግር ድምፆች አማካይነት ሐሳባቸውን የሚለዋወጡበትና የሚግባቡበት መሳሪያ ነው፡፡ የቋንቋን ምንነት Lewis & Hill (1985፣22) ሲገልጹ "ቋንቋ ማለት ብዙ ነገር ነው፡፡ ከብዙዎቹ መካከል ጥቂቱን ለመግለጽ ያህል፡- ቋንቋ ሥርዓት ነው፤ ቋንቋ ምልክት ነው፤ ቋንቋ የህግጋት ስብስብ ነው፤ ቋንቋ የመግባቢያ ዘዴ ነው" ሲሉ አስረድተዋል፡፡

Jordan (1980፣38) በበኩላቸው የቋንቋን ምንነት ሲገልጹ፣ "ቋንቋ ከአንደበት ክፍሎች በሚፈልቁ የንግግር ድምፆች አማካይነት ሰዎች እርስ በርስ ለተግባቦት ተግባር የሚጠቀሙበት ዘዴ ነው" በማለት ይገልጻሉ፡፡

በመሆኑም ቋንቋ ሰዎች ወጋቸውን፣ ልማዳቸውን፣ ባህላቸውን፣ እምነታቸውን፣ አስተሳሰባቸውንና ታሪካቸውን ወዘተ. ከነበረው ትውልድ ወደሚቀጥለው ትውልድ የሚያሸጋግሩበት ዋነኛ ድልድይ ነው፡፡ ለእነዚህና መሰል ጉዳዮች ትልቅ ሚና ያለው ቋንቋ በትምህርት ሲታገዝ ለሰው ልጅ የዕለት ተዕለት ተግባራት ስኬታማነት የሚኖረው አስተዋጽኦ የጎላ ይሆናል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ማለት ደግሞ ልዩ ልዩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተዘጋጅተውለት በሰለጠነ ባለሙያ አማካይነት በተወሰነ የጊዜ ሂደት፣ በተወሰነ የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች የሚሰጥ የተሟላ የቋንቋ ቅርጽ፣ አጠቃቀምና መሰል ጉዳዮችን የሚመለከት ስልጠና ነው፡፡ የቋንቋ ትምህርትን ምንነት ሲገልጹ Lewis & Hill (1985፣22) "የቋንቋ ትምህርት ማለት ቋንቋን ማስተማር እንዲሁም መማር ማለት ነው" ሲሉ Gomez (2009፣389) "የቃላት፣ የመዋቅር፣ የድምፅ ቅላፄ፣ የባህል፣ ወዘተ. ፊርጀ ብዙ ደረጃዎች ድምር ውጤት ነው፡፡ አንድን ቋንቋ መማር ማለት በተለያዩ የመስተጋብር አውዶች ውስጥ በመሳተፍ አዳዲስ የሐሳብ አገላለጽ ዘይቤዎችን መጠቀም መቻል ማለት ነው" በማለት ይገልጹታል፡፡

ምሁራን እንደገለጹት የቋንቋ ትምህርት ማለት ቋንቋን ማስተማር የሚሆነው ቋንቋውን የሚማር አካል ሲኖር መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም። ምክንያቱም አንድ መምህር አንድን ቋንቋ አስተማረ ሊባል የሚችለው ቋንቋውን የሚማር ተማሪ ሲኖር ብቻ ነውና።

ይህንኑ አስመልክተው ባየ (2000፣xxv) ሲገልጹ፣ "የቋንቋ ትምህርት ማለት ራሱን የቻለ መርሀ ግብር ሆኖ በራሱ ዘዴና ዓላማ መሠረት በወጉ በሰለጠኑ መምህራን አማካይነት ትምህርቱን ማስተማር ማለት ነው። አንድ ተማሪም ቋንቋን ተማረ የሚባለው የቋንቋን ክሂሎች ከነሥርዓቱ ተገንዝቦ በተገቢ ሁኔታ መገልገል ሲችል ነው"፤ በማለት አብራርተዋል።

ስለሆነም ቋንቋን መማር ማለት የቋንቋውን ሰዋስው ማወቅ ብቻ ሳይሆን አገባቡን ከነአገልግሎቱ በማወቅ የመገልገልን ብቃት ማሳደግም ጭምር ነው። በአጠቃላይ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ በልዩ ልዩ የመስተጋብር አውዶችና ማኅበራዊ ጉዳዮች ውስጥ በመሳተፍ ብቃት ያለውን ተራክቦ የመፍጠር ችሎታን ያካትታል።

Richards (1990፣vii) ሲገልጹ፣ የቋንቋ ትምህርት ስኬታማ የሚሆነው የቋንቋ ትምህርት የመርሀ ትምህርት፣ የመምህራን፣ የተማሪዎች፣ የማስተማሪያ ዘዴ እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሲሟሉለት ነው። ምሁሩ እንደሚገልጹት ከሆነ በተለይ ለውጤታማ የቋንቋ ትምህርት ሦስት ነገሮች ሊጠቀሱ ይችላሉ። እነሱም፡- መርሀ ትምህርት፣ የማስተማሪያ ዘዴ እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ናቸው። ይህ ሲባል ግን ሌሎቹ አያስፈልጉም ማለት እንዳልሆነ ልብ የሏል።

መስፍን (2000፣1) የቋንቋ ትምህርት በውስጡ አራት የክሂል እንዲሁም ሁለት የዕውቀት ዘርፎችን አካቶ የያዘ መሆኑን ይናገራሉ። አራቱም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርሳቸው የተሳሰሩና ይዘቶቹም ለተማሪዎች የቋንቋ ትምህርት ልምምድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው እንደሆኑ እንዲሁም የቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች ሲዘጋጁ አራቱን ክሂሎችና ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች አካተው ሊዘጋጁ እንደሚገባ ይገልጻሉ።

የእነዚህ የቋንቋ አካላት ዋና ትኩረትም የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ ከግብ ማድረስ ሲሆን በሌላ አገላለጽ የቋንቋው ተማሪዎች ቋንቋውን በተገቢ ሁኔታና ብቃት ባለው መልኩ መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው። ለተለያዩ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ እንዲሆኑ ሆን ተብለው የሚዘጋጁ መጻሕፍት ዓቢይ ተልኳቸው የተማሪዎችን በአራቱም የቋንቋ ክሂሎች የመጠቀም ችሎታ ማሳደግ ነው።

በዚህ መሠረት ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መማሪያ እንዲሆኑ በተለያዩ ጊዜያት ተዘጋጅተው በአገልግሎት ላይ የነበሩ የአማርኛ ቋንቋ መጻሕፍት ከክሂል ይዘቶች አዘገጃጀትና አደረጃጀት አኳያ አልፎ አልፎ ችግሮች የነበሩባቸው መሆናቸውን አጥኚው በማስተማር ሂደት የተገነዘበ ሲሆን በተጨማሪም ይህን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት በጉዳዩ ላይ የመመረቂያ ጽሑፋቸውን ከሰሩ ተመራማሪዎች ሥራ ለማረጋገጥ ችሏል፡፡ ጥናቶቹም የሚያመለክቱት የክሂል መልመጃዎቹ በተመደበላቸው የጊዜ ገደብ የማይጠናቀቁ፣ የክብደት ደረጃ ቅደም ተከተልን ያልጠበቁ፣ የክሂል ይዘቶች ስርጭት ሚዛናዊነት የጎደላቸው፣ ወዘተ. መሆናቸውን ነው፡፡

በመሆኑም ለተጠቀሰው የክፍል ደረጃ በአዲስ መልክ ተሻሽሎ የቀረበው መጽሐፍ ከተጠቀሱት ችግሮች አኳያ ያመጣውን ለውጥ መመርመሩ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም በዚህ ጥናት ለደረጃው ተማሪዎች መማሪያ እንዲሆን በ2004 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በ2005 ዓ.ም. ሥራ ላይ በዋለው የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት በመፈተሽ ጠንካራና ደካማ ጎኖች ተለይተው ቀርበዋል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኚው በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ላለፉት አምስት ዓመታት አገልግሏል፡፡ በእነዚህ ጊዜያትም ቀደም ሲል በአገልግሎት ላይ ዉሎ በነበረው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የነበሩ የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ጥያቄ ሲፈጥሩበት ቆይተዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ ጊዜያት ከተሰሩ የመመረቂያ ጽሑፎች መካከል ይህንኑ ጉዳይ የሚያረጋግጡ ጽሑፎች መኖራቸውን አስተውሏል፡፡ በዚህ የተነሳ ከላይ ለተጠቀሰው ክፍል መማሪያ እንዲሆን በ2004 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በ2005 ዓ.ም. ሥራ ላይ በዋለው የአማርኛ ቋንቋ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት የክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን ያህል ተሻሽለዋል? የሚለውን መፈተሽ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት መተንተን ነው።

ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች በውስጡ አካቷል፤

1. አራቱን የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) የሚመለከቱ ይዘቶችና መልጃዎችን አቀራረብ መፈተሽ፣
2. ይዘቶቹና መልመጃዎቹ ለአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ያላቸውን የስርጭት መጠን መመርመር፣
3. የክሂል መልጃዎቹ ለተማሪዎቹ ከክፍል ውስጥ የመማር ተግባራት ባሻገር ላላቸው የቋንቋ ልምምድ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ማጤን፣ እና
4. የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ የተደራጁበትን ስልት መገምገም

የሚሉ ናቸው።

## 1.4 የጥናቱ አስፈላጊነት

የትኛውም የትምህርት ዓይነት ሲታሰብ ትምህርቱ የሚሰጥበት ዓላማና ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ የትምህርት ይዘቶች አብረው ይነሳሉ። የትምህርት ይዘቶቹ ደግሞ እንዲያሳኩ የሚጠበቅባቸውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችል መልኩ መዘጋጀትና መደራጀት ተገቢ ይሆናል። በመሆኑም የዚህ ጥናት ትኩረት በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች የቋንቋውን ትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ በሚያስችላቸው መልኩ መቅረባቸውንና መደራጀታቸውን መፈተሽ ነው። በዚህ መሠረት ጥናቱ የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፤

1. በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱት ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል ለጥናቱ አንባቢዎች ያሳያል፤
2. አራቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶች በመልመጃዎቹ ውስጥ ያላቸውን የስርጭት መጠን ለጥናቱ አንባቢዎች ይገልጻል፤

3. በጥናቱ ግኝት መሠረት ለመማሪያ መጽሐፉ አዘጋጆችና አርታኢዎች የእርምት ጥቆማ ይሰጣል፤

4. ወደፊት ይህን በመሳሰሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ጥናት ለሚያካሄዱ አጥኚዎች ፍንጭ ይሰጣል።

## 1.5 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች መማሪያ እንዲሆን በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ያተኮረ ነው። ዓቢይ ትኩረቱም በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ አራቱ የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች የቀረቡበትንና የተደራጁበትን ስልት መመርመር ነው።

በመሆኑም ጥናቱ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከተካተቱት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና እነዚህን ይዘቶች ከሚመለከቱ መልመጃዎች ውጭ ያሉትን ይዘቶችንም ሆነ መልመጃዎች አይመለከትም። እንዲሁም ጥናቱ ከተጠቀሰው የክፍል ደረጃ ውጭ የሚገኙትን የመማሪያ መጻሕፍት አያካትትም። በተጨማሪም በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት ከሀዲያ ዞን ሆሳዕና ከተማ ከተመረጡት አራት ትምህርት ቤቶችና በእነዚህ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ውጭ ያሉ ትምህርት ቤቶችና መምህራን የዚህ ጥናት አካል አይደሉም።

በሌላ በኩል መምህራንን ከአዲሱ መማሪያ መጽሐፍ ጋር ለማስተዋወቅ የተሰጠ ስልጠና ስለመኖሩ፣ ስለትምህርት ቤቶቹ አደረጃጀት፣ አመራርና ምቹ የመማር ማስተማር ሁኔታዎች ስለ መጽሐፉ አዘጋጆች ዳራ ጥናቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አይዳስስም።

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት

ይህ ክፍል ጥናቱ የተካሄደበትን ጉዳይ አስመልክቶ የተለያዩ ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝቶች የተካሄዱበት ነው፡፡ በዚህም መሠረት ከጥናቱ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አላቸው ተብለው የታመነባቸው ጉዳዮች በዝርዝር የቀረቡ ሲሆን ከእነዚህም መካከል የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንነትና ባሕርያት፣ የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች እንዲሁም የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት የሚሉ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

### 2.1.1 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ምንነት

የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎችን ዋና ግብ በማድረግ የክፍል ደረጃ ተወስኖላቸው ለተማሪዎች መማሪያ እንዲሆኑ ሆን ተብለው የሚዘጋጁ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ የመማሪያ መጻሕፍትን ምንነት አስመልክተው ምሁራን የሰጡትን ብያኔ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

Ur (2006፣183) እንደገለጹት፣ የመማሪያ መጽሐፍ የሚባለው የአንድ ትምህርት ዓይነት አጠቃላይ ይዘቶችን አካቶ የያዘ ጥራዝ ነው፡፡ ይህም ጥራዝ መምህሩም ሆነ ተማሪዎች ቅጂው የሚደርሳቸው ሲሆን መምህሩም ሆነ ተማሪዎች ሊከተሉት የሚገባውን መርሀ የሚጠቁምና ለቋንቋ ትምህርት መሠረት የሆነ የማስተማሪያና የመማሪያ መሳሪያ ነው፡፡ እንዲሁም Hutchinson & Torres (1994፣315) ሲገልጹ፣ የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ለመምህሩ መመሪያ በመሆን የሚያገለግል ነው፤ ለተማሪዎች ደግሞ ደጋፊ ማስታወሻ ከመሆኑም በተጨማሪ ቋሚ የሆነ የመማር ማስተማርን ተግባር መለኪያ መሳሪያ ነው፤ በማለት አብራርተዋል፡፡

ተስፋዬ (1981፣89) "የቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች የሚባሉት ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ወይም የተመደቡ ብቻ ናቸው፡፡ ሆን ተብለው ለቋንቋ ማስተማሪያነት የተዘጋጁት ለአንድ የተወሰነ ክፍል እንዲያገለግሉ ሥርዓተ ትምህርትን ወይም የክፍሉ ተማሪዎች ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ችሎታ መሠረት በማድረግ ለማስተማሪያ ተብለው የሚዘጋጁ ናቸው"፤ በማለት አብራርተዋል፡፡ ይህ ገለፃ በቀጥታ

የመማሪያ መጻሕፍትን የሚመለከት መሆኑን መገንዘብ አያዳግትም፤ ምክንያቱም መርሀ ትምህርትንና የተማሪዎችን ፍላጎት መሠረት አድርገው ከሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል ቀዳሚዎቹ የመማሪያ መጻሕፍት በመሆናቸው ነው፡፡

ወንድወሰን (1989፣29) እና አያልሰው (2003፣19) የመማሪያ መጽሐፍን ምንነት ሲገልጹ፣ "የቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ሀገሪቱ በምትከተለው የቋንቋ ፖሊሲና የሥርዓተ-ትምህርት ዓላማ ላይ ተመስርቶ ለተወሰነ የክፍል ደረጃ ይመጥናል ተብሎ በሚዘጋጅ መርሀ-ትምህርት ውስጥ የቀረቡት የትምህርት ዓላማዎች፣ ይዘቶች፣ ክንውኖች እና ግምገማዎች በተግባር የሚንጸባረቁበት መሳሪያ ነው"፤ ይላሉ፡፡

## 2.1.2 የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ዓይነቶች

የቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት በሁለት ይመደባሉ፡፡ እነሱም፡- ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት (Traditional textbooks) እና ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት (Communicative textbooks) በመባል የሚታወቁ ናቸው (Grant 1987፣12)፡፡ የሁለቱንም የመማሪያ መጻሕፍት ዝርዝር ባሕርይ ቀጥለን እንመለከታለን፤

### 2.1.2.1 ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት

ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት የሚባሉት ለተማሪዎቹ የመማር ተግባር ቀላል ሆነው በትምህርቱ ፍፃሜ ግን ተማሪዎች ስለቋንቋ አጠቃቀም በቂ ግንዛቤ ሳይጨብጡ ትምህርቱን እንዲያጠናቅቁ የሚያደርጉ መጻሕፍት ናቸው፡፡ ተማሪዎች በእነዚህ መጻሕፍት በመማራቸው የቋንቋውን ሰዋስውና ሥርዓት ሊያውቁ ይችላሉ፤ ነገር ግን በቋንቋው በሚፈለገው ደረጃ መግባባት ይሳናቸዋል (Grant 1987፣13)፡፡

ምሁሩ እንደገለጹት፣ ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት ዓቢይ ትኩረታቸው ተማሪዎች ቋንቋውን እንደ ሥርዓት እንዲማሩት ማድረግ ነው፡፡ ተማሪዎቹ አንድ ጊዜ ሥርዓቱን ከተማሩት በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ቋንቋውን ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ችሎታ ይጨብጣሉ ተብሎ የሚታመንበት ነው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት የሚከተሉትን ባሕርያት በከፊል ወይም በሙሉ ሊያሟሉ እንደሚችሉ አክለው ይገልጻሉ፡፡ እነሱም፡- ከቋንቋ ተግባቦታዊ ተግባራት

ይልቅ በቅርጽ፣ በሥርዓት፣ በሰዋስው፣ ወዘተ. ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፤ከማዳመጥና ከመናገር ክሂሎች በበለጠ ለንባብና ለጽሕፈት ክሂሎች አጽንኦት ይሰጣሉ፤ ከቋንቋ አፍልቆት ይልቅ ለአጠቃቀም ትክክለኛነት ቅድሚያ ይሰጣሉ፤ በፈተናዎች ላይ ያተኩራሉ፤ ለአጠቃቀምና ለፈተና ዝግጅት አመቺ ስለሆኑ በቋንቋ መምህራን ይወደዳሉ፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ገለጻ መሠረት ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት በተማሪዎች የቋንቋ ልምምድ ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ የቋንቋውን ሥርዓት ማሳወቅ ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፡፡ በዚህ የተነሳ ተማሪዎች በቋንቋው በበቂ ሁኔታ ለመገልገል ከመሞከር ይልቅ ሥርዓቱን ለመወቅ ብቻ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ መድረስ የራሱን አሉታዊ አስተዋጽኦ የሚያሳድር ነው፡፡

### 2.1.2.2 ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት

ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች ልዩ ልዩ ተግባቦታዊ የመማር አጋጣሚዎችን በመፍጠር በቋንቋው መግባባት የሚችሉበትን ሁኔታ የሚፈጥሩ ናቸው፡፡ ዓቢይ ትኩረታቸውም ቀደም ሲል በተጠቀሱት ልማዳዊ የመማሪያ መጻሕፍት ላይ የታዩትን ድክመቶች መቅረፍ ሲሆን ተማሪዎች በዕለት ተዕለት ህይወታቸው ቋንቋውን ሊጠቀሙበት በሚያስችላቸው መልኩ እንዲለማመዱ ያበረታታል፡፡ ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ሊገጥሟቸው የሚችሉትን ሁነቶች ታሳቢ በማድረግ በክፍል ውስጥ የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር ለተማሪዎቹ የቋንቋ ብቃት ማደግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ናቸው (Grant 1987፣13-14)፡፡

በምሁሩ አገላለጽ ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት ከልማዳዊ መማሪያ መጻሕፍት የሚለዩባቸውና የራሳቸው የሆኑ በርካታና ሰፋፊ ባሕርያት አሏቸው፡፡ እነዚህም፡- ዓቢይ ትኩረታቸው በተግባቦታዊ ተግባራት ላይ ነው፤ የቋንቋውን ህግጋት ከማሳወቅ ይልቅ ተማሪዎች ቋንቋውን እየተጠቀሙበት ሥራቸውን እንዲሰሩ ያደርጋሉ፤ የተማሪዎችን ፍላጎትና መሻት ለማንፀባረቅ ጥረት ያደርጋሉ፤ ከቋንቋው ሰዋስው ይልቅ ለክሂሎች አጽንኦት በመስጠት በአገልግሎት ላይ በሚውሉበት ሁኔታ ላይ ያተኩራሉ፤ ለአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ምዛናዊ ተግባራት ትኩረት የሚያደርጉ ሲሆኑ ለማዳመጥና ለመናገር ክሂሎች የተለየ ቦታ ይሰጣሉ፤ የቋንቋ ይዘቶችም ሆኑ የማስተማሪያ ዘዴዎቹ በቋንቋው የዕለት ተዕለት አገልግሎት ላይ ያተኮራሉ፤ በመምህራን የክፍል ውስጥ አደረጃጀት ብቃት ላይ ተመስርተው ተማሪዎቹ

በጥንድና በቡድን በመሆን ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እያከናወኑ እንዲማሩ ያበረታታሉ፤ ከቋንቋ አጠቃቀም ትክክለኛነት ይልቅ ለሐሳብ አፍልቆትና ፍሰት ቅድሚያ ይሰጣሉ።

በአጠቃላይ ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት ቀደም ሲል በነበሩት መጻሕፍት ላይ የታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ታስቦ የተዘጋጁት ናቸው። ዓቢይ ትኩረታቸውም ለተማሪዎች የቋንቋውን ሥርዓት ማሳወቅ ላይ ሳይሆን በቋንቋው መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ላይ ነው። ተግባቦታዊ የመማሪያ መጻሕፍት በሚዘጋጁበት ወቅት ታሳቢ የሚያደርጉት የቋንቋውን ህግጋት ሳይሆን የተማሪዎችን ሁኔታና ፍላጎት ነው። በመሆኑም መጻሕፍቱ ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከግብ መድረስ ጉልህ ድርሻ ያላቸው ናቸው።

### 2.1.3 የመማሪያ መጻሕፍት ባሕርያት

ከቋንቋ ማስተማሪያ መሳሪያዎች መካከል አንዱና ዋነኛው የመማሪያ መጽሐፍ ነው። ለተወሰኑ የክፍል ደረጃዎች መማሪያ እንዲሆኑ ታስበውና ሆን ተብለው የሚዘጋጁ መጻሕፍት በሚዘጋጁበት ወቅት የሚከተሉትን ባሕርያት አሟልተው እንዲይዙ ይጠበቅባቸዋል (ተስፋዬ 1981፣94-95)።

#### 2.1.3.1 እውነተኛነት

ለትምህርት የቀረበው የቋንቋ አካል እውነት የቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ የሚለው መሆን አለመሆኑ የሚዳኝበት ነው። ተማሪው እንዲማር የሚቀርብለት፣ እንዲለማመደው የሚደረገው የቋንቋ አካል ቋንቋውን ይበልጥ የሚያሳውቅ፣ በቋንቋው ይበልጥ የባለቤትነት ስሜት የሚያሳድር መሆን አለበት።

#### 2.1.3.2 ግልጽነት

የማስተማሪያ መሳሪያዎቹ የያዟው የትምህርት ጉዳዮች መምህሩ እንዲያስተምር ተማሪው እንዲማር ለማገዝ በግልጽ መስፈር አለመስፈራቸው የሚመዘንበት ነው። ግንዛቤ እንዲገኝባቸው የቀረቡ የቋንቋ ትምህርት ጉዳዮች ምንነታቸው በማያሻማ ስልት እንዲቀርብ ያስፈልጋል።

#### 2.1.3.3 ተለጣጣቂነት

በአንዱ መጽሐፍ ልዩ ልዩ ምዕራፎች መካከልም ሆነ ለተለያዩ ክፍሎች በተዘጋጁ መጻሕፍት መካከል ተለጣጣቂነት የቅደም ተከተል ጉዳይ ነው። ተማሪው ቀጥሎ የሚደርስበት ምዕራፍ ካለፈው የተለየና ያደገ መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ያለፈውን የሚደግም ከሆነ ግን ዕድገት ወይም አዲስነት የለበትምና መሰላቸት ይከተላል።

#### 2.1.3.4 ተግባራዊነት

ተግባራዊነት መምህሩ እንዲያስተምር፣ ተማሪውም እንዲማር የሚያግዝ መሳሪያ የመሆኑ ጉዳይ ነው። የተዘጋጀው የማስተማሪያ መሳሪያ የያዘው የትምህርት ይዘት በተማሪው ተግባራዊ የሚደረግ መሆን ይኖርበታል።

#### 2.1.3.5 ተገቢነት

የተገቢነት ጉዳይ የማስተማሪያው መሳሪያ በይዘቱ ለተማሪዎች ደረጃ፣ ለተማሪዎች ዕድሜ፣ ለተማሪዎች ችሎታና ለተማሪዎች ፍላጎት የሚመጥን መሆን እንዳለበት የሚያመለክት ነው። ለትምህርቱ ሂደትም ቢሆን የማስተማሪያ መሳሪያው ብቃት የሚታየው በዚሁ ዘርፍ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረቡት ሐሳቦች መገንዘብ የሚቻለው በየትኛውም የክፍል ደረጃ ለሚገኙ ተማሪዎች መማሪያ እንዲሆኑ የሚዘጋጁት መጻሕፍት ሊያሟሏቸው የሚገቡ ባህርያት መኖራቸውን ነው። ይህን ከቋንቋ ትምህርት አኳያ ስንመለከት በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርቡ የቋንቋ አካላት ተናጋሪው ህብረተሰብ ዘንድ እውነትነታቸው የተረጋገጠ መሆን ይኖርባቸዋል። ከዚህ ጎን ለጎን ይዘቶቹ ለመማር ማስተማር ሂደት አመቺ መሆናቸውና በግልጽ ቋንቋ መቅረባቸውም አብሮ ይታያል። እንዲሁም በመጽሐፉ አንድ ምዕራፍም ሆነ ተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች በስፋትና በጥልቀት ከፍ እያሉ መሄድና ይዘቶቹም በመምህሩና በተማሪዎቹ መተግበር መቻላቸው መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከእዚህ በተጨማሪ መጽሐፉ የያዛቸው ትምህርታዊ ክንውኖች ከተማሪዎች ልዩ ልዩ ሁኔታዎች አኳያ የተዘጋጁና ዳራቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ እንዲሆኑ ይጠበቅባቸዋል።

### 2.1.4 የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማዎች Widdowson (1978:1) ሲገልጹ፣ "የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ንግግርን ከመረዳት፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከመጻፍ ጋር የተቆራኘ ነው። እነዚህ ተግባራት ደግሞ ከተማሪዎች ትምህርታዊ ልምምድ ጋር በጥብቅ የሚዛመዱ ናቸው" በማለት አብራርተዋል። ይህን ሐሳብ በመጋራት (ትምህርት ሚኒስቴር 2004፣i) "የቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ማጎልበትና የሥነ-ጽሑፍና የሥነ-ልሳን ዕውቀቶችን ማዳበር ነው" ሲል ገልጾታል።

በየትኛውም ደረጃ የሚሰጥ የቋንቋ ትምህርት ቀዳሚ ትኩረቱ ተማሪዎች እነዚህን የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተክነው በአስፈላጊ ጊዜና ቦታ በትክክል መገልገል እንዲችሉ ማድረግ ነው። ከዚህ ባሻገር ተማሪዎቹ የሥነ-ጽሑፍና የሥነ-ልሳን ዕውቀትን እንዲጎናጸፉ ማድረግም ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች መካከል ይጠቀሳሉ። ይሁን እንጂ የዚህ ጥናት ዓቢይ ትኩረት የዕውቀት ዘርፎችን ሳይሆን የክሂል ዘርፎችን ብቻ የሚመለከት በመሆኑ የእነዚህን ዝርዝር ሁኔታ እንደሚከተለው ለመቃኘት ተሞክሯል።

ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች መካከል ቀዳሚው የክሂል ዘርፎችን ግንዛቤ ማዳበር መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቅሷል። በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የክሂል ዘርፎች የሚባሉት ደግሞ ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ ናቸው። አንድ የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግቡን ሊመታ የሚችለውም የቋንቋው ተማሪዎች በእነዚህ አራቱ ክሂሎች በተገቢ ሁኔታ መገልገል ሲችሉ ብቻ ነው። የአራቱንም ክሂሎች ምንነት፣ ክሂሎቹን የማስተማር ዓላማና የማስተማሪያ ስልቶች ቀጥሎ በዝርዝር እንመለከታለን፤

#### 2.1.4.1 የማዳመጥ ክሂል

##### 2.1.4.1.1 የማዳመጥ ክሂል ምንነት

ማዳመጥ ከቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱና የመጀመሪያው ሲሆን ከቃላዊ የመግባቢያ ዘዴዎች ውስጥ የሚመደብ የመቀበያ ክሂል ነው። የክሂሉን ምንነት አስመልክተው ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ የሰጡ ሲሆን Rexon (1986፣3) "ማዳመጥ ማለት ለሚሰማው ጉዳይ ትኩረት በመስጠት የጉዳዩን ፍሬ ነገር ለመረዳት የሚደረግ ተግባር ነው። በተለያዩ ዓላማዎች

ላይ በመመስረት የሰዎችን ንግግር መርጦ በመስማት መልዕክቱን የመረዳት ሂደት ነው" በማለት ገልጸዋል።

Underwood (1989:11) በበኩላቸው ስለማዳመጥ ክሂል የሚከተለውን ብለዋል፤

> *ማዳመጥ ማለት ለሚሰማው ጉዳይ ተገቢውን አትኩሮት በመስጠት መልዕክቱን ለመረዳት የሚደረግ ጥረት ነው። የንግግር ቋንቋን በትክክል ለማዳመጥ ከተፈለገ ተናጋሪው ምን ዓይነት ቃላትን በምን ዓይነት መልኩ እየተገለገለ መሆኑን ለይቶ ለማወቅ ጥረት መደረግ ይኖርበታል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ቃላትን በቁማቸው ለመተርጎም ከመሞከር ይልቅ ከሚነገሩባቸው ልዩ ልዩ አውዶች አንፃር መረዳት ተገቢ ይሆናል።*

በ Anderson & Lynch (1988፣6) አገላለጽ፣ ማዳመጥ ማለት መረዳት ነው፤ ይሁን እንጂ በማዳመጥ ሂደት የአንድ አድማጭ ሚናው በጣም የጎላ ሊሆን ይገባል፤ ምክንያቱም መረዳት ማለት አንድ ተናጋሪ የሚያሰማውን ንግግር ከመስማት የዘለለ ተግባር በመሆኑ ነው። አድማጩ በተናጋሪው ሐሳብ ላይ ልዩ ልዩ ሐሳቦችን በማከል፣ ያዳመጠውን ንግግር ከራሱ ቀደምት ልምድና ዕውቀት ጋር በማገናዘብ ተናጋሪው ለማለት የፈለገውን ጭምር የመገንዘብ ተግባር ነው።

በድሉ (1996፣45) የማዳመጥን ምንነት ሲገልጹ "ማዳመጥ በአእምሮአችን ውስጥ ንግግር ትርጉም የሚያገኝበት ውስብስብ ሂደት ነው። ጥሩ አድማጭ ከሚሰማው ንግግር አዲስ ሐሳብ ስለሚፈልግ አእምሮው ዘውትር ክፍት ነው። ...ጥሩ አድማጭ ለመሆን ደግሞ ተለምዷዊ ማዳመጥን የመማር መንገድ፣ በትምህርት መታገዝ አለበት" ይላሉ።

እቴነሽ (1986፣18) ማዳመጥን ሲገልጹ፣

> *ማዳመጥ ማለት መስማት ማለት አይደለም፤ ከዚያ የላቀ ተግባር ነው። ማዳመጥ ማለት ተናጋሪው ለማስተላለፍ የፈለገውን መልዕክት በትክክል መረዳት ማለት ነው። ማዳመጥ የተለያዩ ሁኔታዎችን ግንዛቤ የሚጠይቅ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ ከተናጋሪው ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ንግግሩ የሚካሔድበትን ቦታ፣ ጊዜና አውድ፣ የንግግር አድራጊውን ማንነት፣ የድምፅ ቅላጼ፣ የንግግሩን አላማ፣ የተናጋሪውን አካላዊ ገጽታ የመሳሰሉ ሁኔታዎችን መገንዘብ ይጠይቃል። የማዳመጥ ተግባር በትክክል ተከናወነ የሚባለው አድማጩ ንግግሩን ከአውዱ ጋር አገናዝቦ መልዕክቱን መረዳት ሲችል ነው።*

በማለት ጽፈዋል።

በእቴነሽ አገላለጽ ማዳመጥ ማለት አድማጩ ከተናጋሪው ጋር ያለውን ግንኙነት፣ ንግግሩ የሚካሄድበትን ቦታ፣ ንግግሩ የሚካሄድበትን ጊዜና አውድ፣ የንግግር አድራጊውን

ማንነት፣ የተናጋሪውን አካላዊ ገጽታ የመሳሰሉ ሁኔታዎችን እንደሚያካትት ነው። ነገር ግን ንግግር አድራጊው የሚቀርበው በሬዲዮ ከሆነ አድማጩ ቀደም ሲል የተገለጹትን ሁኔታዎች መገንዘብ ያስቸግራል።

### 2.1.4.1.2 የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ዓላማ

ጤናማ የሆነ የማዳመጫ አካል ያለው ሰው ሁሉ የሚደረገውን ንግግር ወይም የሚነበብለትን ጽሑፍ በማዳመጥ መልዕክቱን መረዳት ይችላል። ይሁን እንጂ የማዳመጥን ክሂል ማስተማር ወይም መማር የሚያስፈልገው የቋንቋው ተማሪዎች ጥሩ አድማጭ እንዲሆኑና በቋንቋ ትምህርት ሂደት ከሚደረግላቸው ንግግርና ከሚነበብላቸው ሥነጽሑፋዊ ሥራዎች በመነሳት የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እያከናወኑ ክሂሉን ይበልጥ እንዲያዳብሩ ለማስቻል ነው።

በሌላ በኩል ሲታይ የማዳመጥ ክሂል በአንድ ጊዜ ልምምድ የሚጠናቀቅ ተግባር እንዳልሆነ ምሁራን ይገልጻሉ። ይህን በሚመለከት Anderson & Lynch (1988፣18) ሲገልጹ፣ "የማዳመጥ ክሂል ልምምድ ሰዎች በእድሜያቸው መጀመሪያ፣ በአንድ ጊዜ፣ ለአንዴና ለመጨረሻ የሚካኑት ሳይሆን በረጅም የጊዜ ሂደት የሚጎለብት ነገር ነው" ብለዋል።

በድሉ (1986፣45) Lundsteen (1980)ን በመጥቀስ "በማኅበራዊ ግንኙነት ውስጥ ተለምዷዊ በሆነ መንገድ የሚደረግ ተራክቦ ብቻውን ጥሩ አድማጭ ለመሆን አያበቃም። ጥሩ አድማጭ ለመሆን ተለምዷዊ ማዳመጥን የመማር መንገድ በትምህርት መታገዝ አለበት" ይላሉ። ምሁሩ አክለው እንደገለጹት፣ ማዳመጥን የማስተማር ዓላማ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የተነበበላቸውን ወይም የተነገራቸውን ይዘት አዳምጠው በመጨረሻ የሚቀርቡላቸውን ጥያቄዎች መመለስ እንዲችሉ ነው። ከዚህ በተጨማሪ በትምህርት ቤት ውስጥ የሚሰጥ የማዳመጥ ትምህርት የሚከተሉት ልዩ ልዩ ዓላማዎች እንዳሉት ይገልጻሉ። እነሱም፡- ድምፆችን ለመለየት፣ መልዕክትን ለመረዳት፣ መረጃን በመቀበል ተማሪዎች ችግሮቻቸውን እንዲፈቱ ለማገዝ፣ መልዕክትን ለመገምገም፣ ራስን ለማዝናናትና ንግግርን ለማድነቅ የሚሉ ናቸው።

መስፍን (2000፣6) "የማዳመጥን ክሂል የማስተማር ዋነኛ ዓላማ ተማሪዎች የማዳመጥ ክሂላቸውን እንዲያጎለብቱ ለማስቻል ነው። ይህንኑ ክሂል ለማዳበር በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች

የተለያዩ ጽሑፎች የሚቀርቡ ከመሆናቸውም በላይ ትምህርቱም በክፍል ውስጥ የሚነገርበትን ማንኛውንም ገለጻዎች ያካትታል" በማለት ገልጸዋል፡፡

በአጠቃላይ የማዳመጥን ክሂል በትምህርት ቤት የማስተማር ዋነኛ ዓላማ ተማሪው የሚሰማውን ነገር ለመረዳት፣ ለመተርጎም፣ ለመገምገምና የራሱን ምላሽ ለመስጠት የሚያስችለውን ክሂል ማስጨበጥ ነው፡፡ ተማሪው በማዳመጥ ችሎታው እንዲተማመንና በህብረተሰቡ ውስጥ ማዳመጥን ውጤታማ በሆነ መንገድ እንዲጠቀም ለማስቻል በልዩ ልዩ የማዳመጥ አውዶች ተግባራዊ ልምምድ መስጠት አስፈላጊ ነው፡፡

### 2.1.4.1.3 የማዳመጥን ክሂል የማስተማሪያ ዘዴዎች

አንድ የማስተማሪያ መጽሐፍ በውስጡ በጥራትም ሆነ በቁጥር በርካታ የሆኑ የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ ይዘቶችን አካቶ ሊይዝ ይገባል፡፡ የማዳመጥን ክሂል ማስተማሪያ ይዘቶች በመጽሐፉ ውስጥ የሚካተቱበትን ስልት ስናጤን መምህሩም ሆነ ተማሪዎች ምን ምን ተግባራትን መከናወን እንዳለባቸው የሚጠቁሙ ናቸው፡፡ ክሂሉን ለማስተማር የሚያገለግሉ ዘዴዎችን ቀጥለን እንመለከታቸዋለን፡፡

Underwood (1987) እንደሚገልጹት፣ የማዳመጥ ክሂልን ለማስተማር ከሚረዱ ነገሮች መካከል የድምጽ ካሴቶች (cassette/tape recordings)፣ ቀጥተኛ የትምህርት ገለጻዎች (live presentations)፣ የድምጽና የምስል ቁሶች (audiovisual materials)፣ ቃለ ምልልሶች (conversations) እና የስልክ ላይ ንግግሮች (telephone speech) ይጠቀሳሉ፡፡ ተማሪዎች በእነዚህ የሚደረጉ ንግግሮችን እንዲያዳምጡና ካዳመጡት ነገር ተነስተው ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን እንዲያካውኑ በማድረግ ክሂሉን ማስተማር ይቻላል፡፡ እንደነዚህ ያሉ ዘዴዎች የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የሚኖራቸው ፋይዳ የላቀ መሆኑን ምሁሩ ይገልጻሉ፡፡

ምሁሩ አክለውም እንደገለጹ ተማሪዎች በተለያዩ አውዶች ውስጥ በመሳተፍ የሰዎችን ንግግር በሚያዳምጡበት ጊዜ ልዩ ልዩ የድምጽ ቅላጼዎችንና የፍጥነት ደረጃዎችን ይገነዘባሉ፡፡ በዚህ መነሻነት በተለያዩ ስልቶች የሚቀርቡ ንግግሮችን በመከታተል መልዕክቶቻቸውን በቀላሉ ሊረዷቸው ይችላሉ፡፡ በተለይም በምስል ወይም በአካል ከሚቀርቡ ንግግሮች ተማሪዎች የንግግር አቅራቢውን ማንነት፣ ዕድሜ፣ ስሜት፣ አካላዊ ገለፃ ወዘተ. በመገንዘብና ንግግሮቹን ከሁኔታዎች ጋር በማገናዘብ ሊረዱና ለሚቀርብላቸው ጥያቄዎች ምክንያታዊ የሆነ ምላሽ

ሊሰጡ ይችላሉ። ስለሆነም ማንኛውም የማዳመጥ ክሂል ትምህርት ለተማሪዎች በሚቀርብበት ጊዜ አስቀድሞ ተማሪዎቹ የሚያዳምጡበት ምክንያት ሊገለጽላቸው ይገባል።

### 2.1.4.2 የንግግር ክሂል

#### 2.1.4.2.1 የንግግር ክሂል ምንነት

የንግግር ክሂል ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱ ሲሆን ሐሳብን በቃላት አማካይነት አቀናብሮ ለሌላ ሰው የማስተላለፍ ሂደት ነው። አንድ ሰው በአእምሮው ውስጥ ያለውን ሐሳብና የሚሰማውን ስሜት በንግግር ድምፆች አማካይነት ለአድማጭ የሚያቀብልበት ዘዴ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ንግግር ትርጉም ያለው የመስተጋብር ሂደት ሲሆን ሂደቱም የሚከናወነው ሐሳብን በማቀበልና በመቀበል ነው።

የንግግር ክሂልን ምንነት ሲገልጹ አያልሰው (2003፣10) "ንግግር የአንደበት ክፍሎች በተቀናጀ የድምጽ አፈጣጠር ሥርዓት አማካይነት የሚፈጠር ጉዳይ ነው። ንግግር ሐሳባችንን ለመግለጽ ከሚያስችሉን ዘዴዎች መካከል አንዱ ነው። አንድ ሰው ሐሳቡን፣ ስሜቱን ወይም ጥያቄውን በተለየ መንገድ ለመግለጽ ንግግርን ይጠቀማል" በማለት ገልጸዋል። እንደዚሁም Bygate (1987፣vii) "ንግግር በመጀመሪያም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ ለእያንዳንዱ የሐሳብ አገላለጽ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት የሚተገበር የክሂል አይነት ነው" ሲሉ ይገልጻሉ።

በተመሳሳይ መልኩ በየነ (1985፣4) ንግግርን ሲገልጹ "መናገር ስሜት ያፈለቀውን፣ ዓይን የተመለከተውን፣ በንባብ የተገኘውን፣ ውይይትና ጨዋታ የወለደውን ጉዳይ መነሻ በማድረግ ሐሳብን ለሌላ ወገን ሥርዓት ባለው ዘዴ ለማስደመጥ መሞከር ነው" በማለት አስፍረዋል።

በድሉ (1986፣57) በበኩላቸው "ንግግር በተናጋሪውና በአድማጭ መካከል የሚከናወን የሁለትዮሽ ሂደት ነው። ማቀበያ ክሂል የሆነው የንግግር ክሂል ይዳብር ዘንድ መቀበያ የሆነው የማዳመጥ ክሂል መዳበር አለበት። የሁለቱ ክሂሎች መዳበር በእጅጉ የተቆራኘ ነው" በማለት ይገልጻሉ።

ከዚህ ገለጻ የምንገነዘበው የንግግርና የማዳመጥ ክሂሎች እርስ በርሳቸው የተሳሰሩና አንዱ ለሌላኛው ህልውና የጎላ ድርሻ ያላቸው መሆኑን ነው። በሌላ አገላለጽ ንግግር

የሚከናወነው አድማጭ እንዳለ በማሰብ ሲሆን የማዳመጥ ተግባርም የሚካሔደው የሚናገር አካል ሲኖር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

### 2.1.4.2.2 የንግግር ክሂል ትምህርት ዓላማ

ከቋንቋ ትምህርት ዓላማዎች አንዱና ዋነኛው ተማሪዎች የንግግር ችሎታቸውን እንዲያዳብሩና ተግባቦትን እንዲያቀላጥፉ ማስቻል ነው። የተማሪዎች የንግግር ችሎታ የሚዳብረው ደግሞ ክሂሉ በትምህርት ሲታገዝ ነው። የንግግር ትምህርት ዓላማን በሚመለከት ምሁራን የሰነዘሩትን አስተያየት ቀጥለን እንመለከታለን።

በድሉ (1986፣59) የንግግር ትምህርትን ዓላማ ሲገልጹ፡-

> *"ተማሪዎች ከትምህርት ቤት በኋላ ባለው ሀይወታቸው ያለምንም ችግር ሀሳባቸውን በንግግር ለመግለጽ ሲቸገሩ ይስተዋላሉ። በራስ ያለመተማመን፣ መልዕክትን በምክንያትና ውጤት አቀናጅቶ ያለማቅረብና የቋንቋን ሥርዓት ያለመጠቅ ከሚገጥሟቸው ችግሮች ዋነኞቹ ናቸው። የንግግር ክሂልን በክፍል ውስጥ የማስተማር ዋና ዓላማም እነዚህን ንዑሳን ክሂሎች በማዳበር ተማሪዎች ጥሩ የመናገር ችሎታ እንዲኖራቸው ለማድረግ ነው።*

በማለት አስፍረዋል።

### 2.1.4.2.3 የንግግርን ክሂል የማስተማሪያ ብልሃት

በቋንቋ ክፍል ውስጥ ንግግርን ለማስተማር የሚረዱ በርካታ ብልሃቶች አሉ። ተዘውትረው ጥቅም ላይ የሚውሉት ግን ጭውውት፣ ቃላዊ ሪፖርት፣ ቃለ መጠይቅ፣ ስዕል፣ ጥያቄ፣ ወዘተ. ናቸው (በድሉ1996፣65-67)። የእነዚህን ብልሃቶች ዝርዝር ባሕርይ ቀጥሎ እንመለከታለን።

ጭውውት፡- የንግግር ክሂልን ለማዳበር አንጻራዊ ተመራጭነት ያለው ዘዴ ነው። ተማሪዎች እንደየክፍል ደረጃቸው አግባቢነት በተመረጡ ቅንጫቢዎች በመጠቀም የሚያካሂዱት የጭውውት ተግባር እውነተኛ የንግግር አውድን ይፈጥራል። ይህ ሐሳብ በመጋራት ትምህርት ሚኒስቴር (2004፣127) "ጭውውት ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች እርስ በርስ የሚያካሄዱት ውይይት ነው" በማለት ገልጾታል።

ቃላዊ ሪፖርት፡- ይህ ዘዴ ተማሪዎች ያነበቡትን ጉዳይ በራሳቸው የቃላት አጠቃቀምና የአገላለጽ ችሎታ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው፡፡

ቃለ-መጠይቅ፡- ይህ የንግግር ማስተማሪያ ብልሃት ተማሪዎች አንድን ርዕስ ጉዳይ አስመልክተው በቃለ-መጠይቅ ከሰዎች መረጃ የሚሰበስቡበትና ያገኙትን መረጃ አቀናብረው በክፍል ውስጥ በንግግር የሚያቀርቡበት ነው፡፡

ሥዕል፡- መምህሩ አንድ ስዕል መርጦ በማዘጋጀት ያቀርባል፡፡ ተማሪዎች ስዕሉን መሠረት በማድረግ እርስ በርስ እንዲወያዩና የግል አመለካከታቸውን እንዲገልጹ በማድረግ የክፍል ውስጥ ተግባሩ ይከናወናል፡፡

ጥያቄ፡- ጥያቄ መጠየቅ መመህራን በቋንቋ ክፍል ንግግርንም ሆነ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎችን ለማስተማር አዘውትረው የሚጠቀሙበት ብልሃት ነው፡፡ የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ወይም ለትምህርቱ የተመረጠውን ቅንጫቢ መሠረት በማድረግ የተለያዩ አነጋጋሪ ጥያቄዎች ለተማሪዎች ይቀርባሉ፡፡ ጥያቄዎቹ መፍትሔ የሚሹ፣ የሚያብራሩና ምናባዊ ጉልበትን የሚጠይቁ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ክርክር፡- ክርክር ማለት በሁለት ሰዎች ወይም በሁለት ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት ነው (ትምህርት ሚኒስቴር 2004፣165)፡፡ መምህራን አከራካሪ የሆኑ ሐሳቦችን በክፍል ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎች በግል ወይም በቡድን ሆነው አንድን ሐሳብ በመደገፍ አሊያም በመቃወም የሚሰማቸውን ስሜት በንግግር እንዲያቀርቡ የሚደረግበት ብልሃት ነው፡፡

ውይይት፡- የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት እያንዳንዱ ተማሪ የበኩሉን አስተያየት እንዲሰነዝር በማድረግ የሚከናወን የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ብልሃት ነው፡፡ ለምሳሌ አንድን ውሳኔ ለመወሰን እንዲያስችል ተማሪዎች መሆን አለበት ብለው የሚያምኑበትን በንግግር እንዲገልጹ በማድረግ ይከናወናል፡፡

### 2.1.4.3 የንባብ ክሂል

#### 2.1.4.3.1 የንባብ ክሂል ምንነት

ንባብ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ ማንበብ ማለት የፊደል ቅርጽን መለየት አይደለም፤ ከዚያ የዘለለ ተግባር ነው፡፡ ይህን አስመልክተው በርካታ ምሁራን የየበኩላቸውን ብያኔ የሰጡ ሲሆን ከእነሱም መካከል የተወሰኑትን ቀጥለን ለመመልከት እንሞክራለን፡፡

Nuttall (1982፣4) የንባብን ምንነት ሲገልጹ፣ "ንባብ ማለት የሥነ-ልሳን ልምምድ አይደለም፤ ንባብ በአንድ ዓላማ ላይ ተመስርቶ ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ መልዕክቱን የማግኘት ተግባር ነው" ሲሉ Williams (1984፣12) "ማንበብ አንድን መጽሐፍ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ መመልከት ማለት አይደለም። ማንበብ ማለት የተጻፈን ነገር መረዳት፣ ማመዛዘን፣ መገመት፣ ማወቅና መርካት ማለት ነው" ሲሉ አብራርተዋል። የሺጥላ (2000፣8) "ንባብ የሰው ልጅ በጊዜና በቦታ ርቀት ምክንያት ሊያጣቸው የነበሩትን ነገሮች እንዲያገኝ በማድረግ ከፍተኛ አገልግሎት ከሚሰጡ የመገናኛ ዘዴዎች አንዱ ነው" በማለት ገልጸውታል። ይህን ብያኔ የሚጋሩ ሌሎች ምሁራንም ሀሳባቸውን እንደሚከተለው ሰንዝረዋል።

እንደ Smith (1987፣11) አገላለጽ፣ "ንባብ ማለት የተጻፉ ቃላትን መለየት ነው። በሌላ አገላለጽ ንባብ ማለት የጸሐፊውን መልዕክት የመገንዘብ ሂደት ነው"። ምሁሩ አክለውም እንደገለጹት ንባብ አእምሮአዊና አካላዊ ወይም ውስጣዊና ውጫዊ ሂደት ሲሆን ማሰብን፣ ማሰላሰልን፣ መገንዘብን፣ መረዳትን፣ ወዘተ. ስለሚያጠቃልል ውስብስብነቱ የጎላ ነው። እንዲሁም Davies (1995፣1) "ማንበብ የግል ተግባር ነው። ይህም አእምሮአዊ ሂደት ሲሆን አንባቢው የጸሐፊውን መልዕክት በመረዳት በቦታና በጊዜ ርቀት ሳይገደብ ምላሽ ለመስጠት የሚሞክርበትን ስልት ያካትታል" በማለት አብራርተዋል።

Grellete (1981፣1) በበኩላቸው "ንባብ ማለት ከተጻፈ ወይም ከታተመ ጽሑፍ መልዕክትን የመረዳት ሂደት ነው" በማለት ገልጸዋል። ምሁሩ አክለውም "ንባብ ማለት በሌላ ሰው ጭንቅላት ማሰብ ሲሆን አንባቢው የራሱን እውቀት እንዲፈትሽ የሚያግዝ መሳሪያ ነው" ሲሉ ይገልጻሉ።

በ Grellete (1981፣8) አገላለጽ፣ ንባብ ማለት ልዩ ልዩ ተግባራትን ማከናወን ማለት ነው። "ንባብ ማለት መገመት፣ መተንበይ፣ ማመሳከርና ራስን ጥያቄ መጠየቅ የሚሉትን የሚያጠቃልል ደግሞም ንቁ ተሳትፎ የሚያስፈልገው ሂደት ነው" ይህን ሐሳብ በመጋራት Nuttall (1992፣18) "ንባብ በባሕርዩ የአንባቢን ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ፣ ከአንድ አእምሮ ወደሌላ፣ ከጸሐፊ ወደ አንባቢው ፍቺ ወይም መልዕክት የሚተላለፈፍበት ዘዴ ነው" በማለት አብራርተዋል።

ተስፋዬ (1981፣60) ማንበብ እውቀትን የማግኛ መንገድ ብቻ ሳይሆን እንደ ዋና፣ ኳስ ጨዋታ፣ ሽርሽርና እንደ አደን ሁሉ መዝናኛ ሆኗል" ሲሉ ዕውቀትን ከማግኛ ዘዴ ባሻገር ያለውን የንባብ ምንነት ገልጸዋል።

በአጠቃላይ ከእነዚህ ምሁራን ብያኔዎች መረዳት የሚቻለው ንባብ የተጻፈን ነገር በትክክል የመመልከት፣ የማስተዋል፣ የመገንዘብና መልዕክትን የመረዳት ተግባር መሆኑንና በጽሑፍ ውስጥ በቃላት አማካይነት የቀረቡ መልዕክቶች ተቀናጅተውና ተደራጅተው የሚመሰርቱትን መልዕክት መረዳት መሆኑን ነው።

### 2.1.4.3.2 የንባብ ክሂል ትምህርት ዓላማ

የንባብ ትምህርት ዓላማ የንባብን ክሂል ለምን እንማራለን? ወይም ለምን እናስተምራለን? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ የሚሰጥ ነው። በቅድሚያ አንድ ሰው ለምን ያነባል? ከሚለው ብንነሳ ምላሹ የተለያዩ ውስጣዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የሚል ሊሆን ይችላል። አንድ ሰው የሚያነብበትን ምክንያት አስመልክተው Greenall & Swan (1986፣2) ሲገልጹ፣ "ማንኛውም ሰው አንድን ጽሑፍ ሲያነብ በአእምሮው ውስጥ አንድ ዓላማ ይዞ ነው። በሌላ አነጋገር የሚያነብበት ዓላማው ለመዝናናት ወይም መረጃ ለማግኘት ሊሆን ይችላል" በማለት አስረድተዋል።

ከዚህ ገለጻ መረዳት የሚቻለው አንድ ሰው እውቀት ለማግኘት፣ ለመዝናናት፣ መረጃ ለመፈለግ፣ የጽሑፉን አጠቃላይና ዝርዝር መልዕክት ለመረዳት፣ ወዘተ. ለመሳሰሉ ምክንያቶች የተለያዩ ጽሑፎችንና ስነጽሑፎችን ሊያነብ እንደሚችል ነው። በሌላ በኩል ተማሪዎች የንባብ ክሂል እንዲማሩ የሚደረግበት ትልቁ ምክንያትም እነዚህን ተግባራት በላቀ ደረጃ እንዲያከናውኑ ለማስቻል ነው። በዚህ ረገድ ምሁራን ያሉትን ቀጥለን እንመለከታለን።

Nuttall (1992፣2) "ሰዎች መጽሔትን፣ ጋዜጦችን፣ መጻሕፍትን፣ ሌሎችንም የሥነ-ጽሑፍ ሥራዎች ሲያነቡ የየራሳቸው የሆነ ዓላማ ይኖራቸዋል፤ የሚያነቡበት ዓላማ ደግሞ የአነባበብ ስልታቸውን ይወስነዋል። ጥሩ አንባቢ የሚባለውም ከሚያነብበት ምክንያት ወይም ዓላማ አንፃር የአነባበብ ስልቱን ማስማማት የሚችል ነው" ሲሉ በሌላ በኩል የሺጥላ (2000፣9) የንባብ ክሂልን ትምህርት ዓላማ ሲገልጹ፣ "የንባብ ትምህርት የተማሪውን የንባብ ችሎታ ለማዳበር፣ አንብቦ ጠቃሚውንና የማይጠቅመውን ነገር ለይቶ እንዲረዳ፣ የሥነ-ጽሑፍ

ችሎታውን ለማሳደግ፣ ታሪክ እንዲያውቅ፣ ለጠቅላላ ዕውቀት፣ አእምሮአዊ ብቃትን ለማጎልበት፣ ወዘተ. የመሳሰሉ በርካታ ጥቅሞች አሉት" ሲሉ ገልጸዋል፡፡

Nuttall እንደገለጹት፣ የአነባበብ ስልት በአንባቢው ዓላማ ላይ ይመሰረታል፡፡ የአንድን ጽሑፍ ፍሬ ሀሳብ ወይም ቁም ነገር ለመረዳት ገረፍታ ንባብ ጥቅም ላይ ሲውል እንዲሁም አንባቢው ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ የሚፈልገውን ጉዳይ ብቻ መርጦ ለማውጣት የአሰሳ ንባብ ስልትን ይከተላል፡፡ የጽሑፉን አጠቃላይና ዝርዝር ይዘት ለመረዳት ጥልቅ የአነባበብ ስልት ሲተገብር ነገር ግን የሚያነበው ለመዝናናት፣ ለመደሰት፣ ጊዜ ለማሳለፍና ለጠቅላላ ዕውቀት ከሆነ መጠነ ሰፊ የአነባበብ ዘዴን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎች የንባብ ክሂልን በትምህርት ቤት እንዲማሩ የሚደረግበት ትልቁ ዓላማ አንድን ጽሑፍ አንብበው መልዕክቱን በወጉ መገንዘብ እንዲችሉ ለማድረግ ነው፡፡ በዚህ ሂደት ተማሪዎች የተለያዩ የአነባበብ ስልቶችን በማወቅ ለሚያነቡበት ዓላማ ተስማሚ የሆነውን የንባብ ስልት መርጠው መተግበር የሚያስችላቸውን እውቀት ያገኛሉ፡፡

### 2.1.4.3.3 የንባብን ክሂል የማስተማሪያ ብልሃቶች

አንብቦ መረዳትን ለማስተማር የሚረዱ የተለያዩ ብልሃቶች አሉ፡፡ እነዚህም፡- ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ አንድምታና ትንበያ እንዲሁም ምስላ ናቸው (በድሉ 1996፣36-42)፡፡

ጥያቄ መጠየቅ፡- መጠየቅ ተፈጥሯዊ ነው፡፡ ሰዎች በዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ ጥያቄ ይጠይቃሉ፡፡ በመጠየቃቸው ከዚህ በፊት ግራ የሚገባቸውን ጉዳይ አስመልክቶ ጥርት ያለ ዕውቀት ያገኛሉ፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ተገቢ ጥያቄ መጠየቅ ከቻሉ ስለራሳቸውና ስለአካባቢያቸው በሚገባ ይረዳሉ፡፡

ማብራራትና መተርጎም፡- ተማሪዎች ያነበቡትን ቅንጫቢ ፍሬ ሀሳብ ለምን በዚያ መንገድ እንደተረዱት፣ ፍሬ ሀሳቡ ይህ ነው ብለው ለማጠቃለል ያበቋቸው መረጃዎች ምን ምን እንደሆኑ ምክንያቶቻቸውን እንዲዘረዝሩ ቢደረግ የዘነጓቸውን ጠቃሚ ዝርዝር መረጃዎች ያስታውሳሉ፡፡ ዝርዝር መረጃዎችን ማስታወስ ደግሞ ማን፣ መቼ፣ እንዴት፣ የትና ለምን ከዋናው ሀሳብ ጋር እንደሚገናኝ ለማወቅ ይረዳል፡፡

ማጠቃለል፡- ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ በየደረጃቸው ማጠቃለያ እየሰጡ ቢያነቡ የመረዳት ችሎታቸው እንደሚጨምር የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን ዋቢ በማድረግ ምሁሩ ይገልጻሉ።

አንድምታና ትንበያ፡- አንድምታ ከቅንጫቢ የተገኘን መረጃ በመገምገምና መረጃውን በመመርኮዝ መደምደሚያ ላይ መድረስ፣ ወይም ዝርዝር መረጃዎችን ተጠያቂ በሆነ መንገድ ማቀናጀት ሲሆን፣ ቅንጫቢው ውስጥ በግልጽ ያልተቀመጡ ሐሳቦችን ለማግኘት የመጀመሪያ እርምጃ ነው። ትንበያ አንባቢ ካነበበው መረጃ በመነሳት ያላነበበውን የቅንጫቢውን ክፍል ሐሳብ ምን ሊሆን እንደሚችል የሚገምትበት ሂደት ነው።

በአጠቃላይ አንድ መምህር የተማሪዎቹን የንባብን ክሂል ሲያስተምር እነዚህንና ሌሎችንም የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች ተግባራዊ ቢያደርግ የክሂሉን ትምህርት ዓላማ በተገቢ ሁኔታ ማሳካት ይችላል። ተማሪዎችም በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ የንባብ ክሂል ልምምድ በሚያደርጉበት ወቅት እነዚህን ብልሃቶች ቢተከተሉ የማንበብ ችሎታቸው እንደሚጎለብት ጥርጥር የለውም።

### 2.1.4.4 የጽሕፈት ክሂል

#### 2.1.4.4.1 የጽሕፈት ክሂል ምንነት

ከቋንቋ ክሂሎች መካከል ጽሕፈት አንዱ ሲሆን ለንግግር ድምጾች በሚወከሉ ምልክቶች አማካይነት ሐሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር የመግባባት ተግባር ነው። የጽሕፈት ክሂል የሚመደበውም ከማቀበያ ክሂሎች ውስጥ ነው። የክሂሉን ምንነት አስመልክተው ምሁራን የየራሳቸውን አስተያየት የሰጡ ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታቸዋለን።

Byrne (1988፣1) ጽሕፈት የሚከናወነው በድምጽ ምልክቶች አማካይነት ነው። ለንግግር ተግባር የሚውሉ ድምፆችን ሥርዓታዊ ውህደት የሚመለከት ነው። በሌላ አገላለጽ "ጽሕፈት ማለት እነዚህን የንግግር ድምፆች ትርጉም ሊሰጡ በሚችሉ እና ሥርዓት ባለው መልኩ በማቀናጀት ሐሳብን የመግለጫ እንዲሁም የመግባቢያ ስልት ማለት ነው" ሲሉ ገልጸዋል። ይህን ሐሳብ በመደገፍ አንለይ (1987፣13) በመመረቂያ ጽሑፋቸው ውስጥ አስፍረዋል።

ይሁን እንጂ Byrne አክለው እንደገለጹት ጽሕፈት የንግግር ድምፆችን ከማዋቀር ያለፈ ተግባር ነው። እንደዚሁም ንግግርም ቢሆን ድምፆችን ከማፍለቅ የዘለለ ተግባር መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። አንድ ተግባር ጽሕፈት ነው ሊባል የሚችለው የድምጽ ምልክቶቹ በሥርዓት ተቀናጅተው የተሟላ መልዕክት የያዘውን ዓረፍተነገር መመስረት ሲችሉ ነው፤ በማለት ያብራራሉ።

የጽሕፈት ክሂልን ምንነት አለም (1995፣14) እንደሚከተለው ያብራራሉ፤

> *ጽሕፈት ሀሳብን በትክክል ለማስተላለፍ ከድምጽ ጀምሮ ያሉት ቃላትና አረፍተ ነገሮች በቋንቋ ስርዓት መሠረት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀውና ተቀናብረው የሚቀርቡበት ነው። አንባቢም መልዕክቱን በትክክል የሚረዳው የቋንቋውን ሥርዓት የጠበቀ እንደሆነ ብቻ ነው። በዚህ መንገድም ሀሳብን ማስተላለፍ እንዲችል ሰፊ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። ጽሑፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተደጋጋሚ በሚደረጉ ሙከራዎች ያድጋል፤ ይዳብራል፤ ይበለጽጋል።*

በተጨማሪ ተስፋዬ (1981፣61) የጽሕፈትን ምንነት ሲገልጹ "ጽሕፈት ሲባል የእጅ ጽሕፈት አጣጣልን ብቻ የሚመለከት አይደለም። የሐሳብ አቀነባበርን፣ የሐሳብ አደረጃጀትን፣ የቃላት አመራረጥንና አገላለጽንም ስልት የሚጠይቅ ነው" በማለት በአጭሩ በይነውታል።

### 2.1.4.4.2 የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ዓላማ

የጽሕፈት ክሂልን የማስተማር ዓላማ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጥሩ ጽሑፍ ማስተላለፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። Littlejohn (1993፣27) እንደሚገልጹት፣ "አንድ ጽሑፍ ጥሩ ጽሑፍ ነው የሚባለው ትክክለኛ የፊደላት አቀማመጥና የተሟላ መልዕክት ያለው ሆኖ ሲገኝ ነው"። በተመሳሳይ መልኩ ሃና (2003፣9) የጽሕፈት ትምህርት ቀዳሚ ዓላማ ተማሪዎች በጽሑፍ አማካይነት ሐሳባቸውን በተቃናና በተዋበ መንገድ በመግለጽ ጽሑፋዊ ተግባቦትን እንዲለማመዱ ማስቻል ነው" በማለት ይገልጻሉ።

የጥሩ ጽሑፍን ምንነት McCrimmon (1863፣3) ሲገልጹ፣ "ጥሩ ጽሑፍ በአንድ ቅጽበት የሚከሰት ነገር አይደለም፤ ጸሐፊው ሐሳብን፣ እውነታን፣ ወዘተ. አስመልክቶ ለሌሎች ሰዎች ለማስተላለፍ ሲያስብ ሆን ብሎና አቅዶ በሚያደርግ ሙከራ የሚዳብር ተግባር ነው" በማለት አስፍረዋል።

ጽሕፈት (guided wititing) እና ነፃ ጽሕፈት (free writing) በመባል የሚታወቁ ናቸው (Raimes 1983)፣ (Richards 1990)፣ (Pincas 1982)፣ (Doff 1988)።

**የቁጥጥር ጽሕፈት፡-** የቁጥጥር ጽሕፈት ልምምድ ሁለት ዓይነት ሲሆኑ እነሱም፡- ማዋኸድ እና መተካት በመባል የሚታወቁ ናቸው። በማዋኸድ የሚተገበር የቁጥጥር ጽሕፈት ክሂል ልምምድ ቃላትን አቀናጅቶ ዓረፍተነገርን በመመሥረት፣ ዓረፍተነገሮችን አቀናጅቶ አንቀጽን በመመሥረት፣ ወዘተ. የሚከናወን ነው (Pincas 1982፡91)። በመተካት የሚተገበር የጽሕፈት ክሂል ልምምድ መሠረታዊ ስልቱ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ቃላት ተጠቅመው አዳዲስ ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ እንዲሁም ቃላትን በሌላ ቃላት እንዲተኩ በማድረግ የሚከናወን ነው።

በምሁሩ አገላለጽ የቁጥጥር ጽሕፈት መልመጃ ዓቢይ ትኩረቱ ስህተትን ባለመፈጸም ወይም ከስህተት በጸዳ ጽሁፍ ላይ ሲሆን አብዛኛውን ጊዜ መልመጃው ለጀማሪ የጽሕፈት ትምህርት ተማሪዎች የሚቀርብ ነው። የቁጥጥር ጽሕፈት መልመጃ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ትዕዛዝ በመከተል ከስህተት ተቆጥበው የተለያዩ ትምህርታዊ ተግባራትን በማከናወን ጽሕፈትን የሚማሩበት ስልት ነው።

**መር ጽሕፈት፡-** ተማሪዎች የጽሕፈት ክሂልን በሚለማመዱበት ወቅት ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን ችግሮች ለመቅረፍና የሚፈጥሯቸውን ስህተቶች ለመቀነስ እንዲረዳ የተለያዩ ተግባራት የሚከናወኑበት ሂደት ነው። ተማሪዎች በቁጥጥር የጽሕፈት ሂደት ካዳበሩት የዓረፍተነገር አመሠራረት ችሎታ በተጨማሪ የአፃፃፍ ስልትን ለመለየት የሚረዱና ወደሚቀጥለው ነፃ የጽሕፈት ተግባር ለመሸጋገር የሚያግዙ የጽሕፈት ልምምዶችን ያካተተ ነው (Doff 1988፣148-150)።

መር የጽሕፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ በቁጥጥርና በነጻ የጽሕፈት ስልቶች መካከል እንደመሸጋገሪያ ድልድይ የሚያገለግል ነው። መር የጽሕፈት ስልት ለተማሪዎች የሚደረግን ማንኛውንም እገዛ የሚያካትት ሲሆን ለምሳሌ ተጀምሮ የቀረን ጽሑፍ ለመጨረስ ሐሳብ እንዲያፈልቁ፣ ስዕሎችን ወደጽሑፍ እንዲቀይሩ፣ ወዘተ. በማበረታታት የሚተገበር ነው (Pincas 1982፡102)።

**ነጻ ፅህፈት፡-** ለተማሪዎች ርዕስ ይሰጣቸውና በፈለጉት ሁኔታ ነጻ ሆነው እንዲጽፉ በማድረግ የሚተገበር ስልት ነው። በዚህ ስልት የሚሰጥ የጽሕፈት ትምህርት ዓላማው

ተማሪዎቹ ራሳቸውን ችለውና ነጻ ሆነው እንዲጽፉ ለማድረግ ነው። በዚህ ዘዴ ተማሪዎች እንዲጽፉ የሚጠበቅባቸው ስለተማሩት ጉዳይ እንጂ ስለጠቅላላ ነገር ያላቸውን ግንዛቤ አይደለም። ስለሆነም ተማሪዎቹ ጽሕፈትን በሚጀምሩበት ጊዜና ሐሳባቸውን በሚያደራጁበት ወቅት ከመምህራቸው ተገቢ እገዛ ያስፈልጋቸዋል (Pincas 1982፡110-111)።

**ሂደታዊ የጽሕፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ፡-** ይህ ዘዴ በዋናነት የሚጻፈውን ጽሑፍ ከተለያዩ አቅጣጫዎች አንፃር የሚመለከት ሲሆን ጽሑፉ በራሱ የተሟላ ጽሑፍ ለመሆን በሚያልፍባቸው ሂደቶች ላይ ትኩረት የሚያደርግ ነው (Nunan 1989፣36)። በተመሳሳይ መልኩ Raimes (1983፣10) ሲገልጹ፣ ይህ አቀራረብ ትኩረት የሚሰጠው ለሚደረስበት ውጤት ሳይሆን በጽሕፈት ጊዜ ለሚታለፍባቸው ሂደቶች ነው። በዚህ ዘዴ ሲማሩ ተማሪዎች የሚያስቡት የጽሑፉን ዓላማና የአንባቢያንን ፍላጎት ሳይሆን ጽሑፉን በምን ዓይነት መንገድ እንደሚጀምሩት እና ሐሳባቸውን እንዴት እንደሚያደራጁት ነው።

### 2.1.5 የቋንቋ ክሂሎች ይዘትና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት

#### 2.1.5.1 የቋንቋ ክሂሎች ይዘት ምንነት

የቋንቋ ትምህርት በአጠቃላይ አራት የክሂል ዘርፎችና ሁለት የዕውቀት ዘርፎች እንዳሉት ቀደም ሲል ተገልጿል። የአራቱ ክሂሎች ዓቢይ ትኩረት ደግሞ ቋንቋውን የሚማሩ ተማሪዎች ክሂሎቹን በተገቢ ሁኔታ ተለማምደው በአስፈላጊ ጊዜና ቦታ ለተግባቦት ተግባር ማዋል እንዲችሉ ማድረግ ነው። አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ይዘት ምንነት አስመልክተው Widdowson (1978፣57) ሲገልጹ፣ "ማዳመጥና መናገር ሐሳብን በቃል የመቀበያና የማቀበያ ዘዴዎች ሲባሉ ማንበብና መጻፍ ደግሞ በሚታዩ ምልክቶች አማካይነት መልዕክትን የመቀበያና የማስተላለፊያ ስልቶች ናቸው" ብለዋል።

ምሁሩ አክለው እንደገለጹት የቋንቋ ክሂሎች የሚባሉት ሐሳብን የመቀበያና የማቀበያ ዘዴ ብቻ አይደሉም፤ ነገር ግን የቋንቋ ክሂሎች የቋንቋው ተጠቃሚ በሚያደርጋቸው ልዩ ልዩ የቋንቋ ልምምዶች አማካይነት ሲገለጹ የሚችሉ ተግባራትን የሚመለከቱ መሆናቸውንም ጭምር ነው። በዚህ መሠረት ንግግርና ጽሕፈት ርቱእ ወይም የማመንጫ ክሂሎች (active or productive skills) ሲባሉ እንዲሁም ማዳመጥና ማንበብ ኢ-ርቱእ ወይም የመቀበያ ክሂሎች (passive or receptive skills) ይባላሉ (Widdowson 1978፣57)።

በመሆኑም የክሂል ይዘቶች የምንላቸው ለቋንቋ ትምህርት ዓላማ ማሳኪያ እንዲሆኑ ታስበው የሚዘጋጁ መልመጃዎችንና ልዩ ልዩ ትምህርታዊ ተግባራትን ሲሆን ይዘቶቹና ትምህርታዊ ተግባራቱም የተማሪዎችን ስሜት የመግዛት፣ የመማር ዝንባሌያቸውን የመቀስቀስና ትኩረታቸውን የመሳብ፣ ወዘተ. ኃይል ያላቸውና ፍላጎታቸውን መሠረት አድርገው የሚዘጋጁ ናቸው።

#### 2.1.5.2 የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ ምንነት

የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ ማለት ለተማሪዎቹ ትምህርታዊ ልምምድ የሚሆኑ የቋንቋ ክሂል ጥያቄዎችን የሚመለከት ጉዳይ ሆኖ በዋናነት ለቋንቋ ትምህርት የተነደፈለትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ እንዲያስችሉ ሆነ ተብለው የሚቀረጹትን ክንውኖች የሚመለከት ነው። መልመጃ የሚባለው የቋንቋ ክሂሎች ይዘት ለክፍል ውስጥ ትምህርታዊ ልምምድ ወደ ተማሪዎች የሚቀርቡበትን ስልት ነው። መልመጃ ልዩ ልዩ ቅርጽና አቀራረብ ኖሮት ተማሪዎች በየክፍል ደረጃቸው እንዲተገብሩት የሚጠበቀውን የቋንቋ ተግባራት እንዲያከናውኑ የሚያግዙ ጥያቄዎችን የሚያካትት ነው።

ለተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎች ልምምድ የሚቀረጹ መልመጃዎች ከክፍል ውስጥ ልምምድ ባሻገር ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም በአግባቡ እንዲገለገሉበት የሚያበቁ ሊሆኑ ይገባል። ይህን አስመልክተው Grant (1987፣800) ሲገልጹ "ለየትኛውም የክፍል ደረጃ መልመጃዎች ሲቀረጹ ተማሪዎች ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም እንዲጠቀሙ በሚያስችል መልኩ መሆን ይኖርባቸዋል" በማለት አስረድተዋል።

#### 2.1.5.3 የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ አቀራረብ

ለቋንቋ ልምምድ ታስበው የሚዘጋጁት መልመጃዎች የተለያዩ ቅርጾች ሊኖሯቸው ይችላሉ። ይህን መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ በመልማጃዎቹ ስር የቀረቡ ጥያቄዎች ከሚፈልጉት የምላሽ አሰጣጥ ሁኔታ በመነሳት ነው። ይህን በሚመለከት ምሁራን የሰነዘሩትን አስተያየት ቀጥለን እንመከለታለን።

Nuttall (1992፣132) ሲገልጹ፣ በቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የሚቀርቡ መልመጃዎች ቀጥተኛ፣ ማገናዘብንና ማቀናበርን የሚሹ፣ መመራመርን፣ ግምገማንና የግል

አስተያየትን የሚጠይቁ፣ ወዘተ. ጥያቄዎችን የሚመስሉ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ብለዋል፡፡ የሺጥላ (2000፣21) በበኩላቸው "መልመጃዎች የተፈለገውን የቋንቋ ትምህርት ከግብ ሊያደርሱ የሚችሉ እንዲሁም ውጤታማ ትምህርትን ለማስተማር የሚረዱ መሆን ይኖርባቸዋል" በማለት መልመጃዎች ሲዘጋጁ ሊደረግ የሚገባውን ጥንቃቄ ይገልጻሉ፡፡

### 2.1.5.4 የቋንቋ ክሂሎች መልመጃ አደረጃጀት

የቋንቋ ትምህርትን ዓላማ እንዲያሳኩ የሚዘጋጁት የክሂል መልመጃዎች በተገቢ ሁኔታ መደራጀት ይኖርባቸዋል፡፡ መልመጃዎቹ በሚፈለገው መልኩ ካልተደራጁ የሚጠበቀውን ውጤት ሊያስገኙ አይችሉም፡፡ ለትምህርትነት የሚዘጋጁ ይዘቶችና መልመጃዎች ሲደራጁ ሊከተሏቸው የሚገቡ ሦስት መስፈርቶች አሉ፡፡ እነሱም፡- ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት እና ውህደት ናቸው (ተስፋዬ 1981፣40)፡፡

#### 2.1.5.4.1 ተከታታይነት

ተከታታይነት ለተገቢው ቀጥተኛ አወቃቀር ወይም አደረጃጀት ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ተከታታይነት ሲባልም በአንድ የትምህርት አይነት ውስጥ እያደገ ግን በተደጋጋሚ የሚመጣ ነው፡፡

#### 2.1.5.4.2 ተለጣጣቂነት

ተለጣጣቂነት ከተከታታይነት ጋር የሚዛመድ ቢሆንም የሚለይበት ባሕርይ አለው፡፡ ለትምህርትነት የሚቀርብ ጉዳይ በየደረጃው ስፋትና ጥልቀት እያገኘ እንዲሄድ የሚመራ ነው፡፡ ተለጣጣቂነት የጉዳዩን ተደጋጋሚነት ሳይሆን የጉዳዩን እንደገና እየሰፋ መሄድ የሚመለከት ነው፡፡

#### 2.1.5.4.3 ውህደት

ተዋህዶ የሚባለው ደግሞ በማስተማሪያ መሳሪያው ውስጥ ያሉትን የትምህርት ልምዶች መስመራዊ ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ የተዋህዶ የትምህርት ልምዶች ቅንብር የትምህርት ልምዶቹን የርስ በርስ መደጋገፍ፣ የትምርህርት ልምዶቹ አንዱ ሌላውን የማዳበርና የማበልጸግ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡

## 2.2 የቀደምት ጽሑፎች ቅኝት

የዚህ ጥናት አቅራቢ በመረጠው ርዕስ ላይ ጥናት ለማካሄድ ከመጀመሩ አስቀድሞ ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን የቀደምት ጽሑፎች ዳሰሳ አካሂዷል። በዚህም ሂደት የዚህ ጥናት ትኩረት በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በተካተቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ትንተና ላይ በመሆኑ ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውን ጥናቶች ማግኘት አልቻለም። ዳሩ ግን በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን ተቀራራቢነት ያላቸውን ሥራዎች በመለየት ከዚህ ጥናት ጋር ያላቸውን ተመሳሳይነትና ልዩነት እንደሚከተለው ለማሳየት ሞክሯል።

አጥኚው የቀደምት ጽሑፎችን ቅኝት ባደረገበት ወቅት በቀጥታ እንኳን ባይሆን ተቀራራቢነት ያላቸው አምስት ጥናቶች መኖራቸውን ለመገንዘብ ችሏል። ከእነዚህም መካከል አንዱ በመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የተሰራ ሲሆን አራቱ ግን ለሁለተኛ ዲግሪ መሟያነት የተካሄዱ ጥናቶች ናቸው።

የመጀመሪያው በየነ (1985) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋውን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው?" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ እንዲሆን ያካሄዱት ነው። የጥናቱም ዋና ዓላማ በ1984 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ማስተማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተጠቀሱትን ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) የሚያዳብሩ መሆን አለመሆናቸውን ማረጋገጥ ነው።

ጥናቱ በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ማተኮሩና ሰነድ ፍተሻን በዋና እንዲሁም የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅን በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት መጠቀሙ ከዚህኛው ጥናት ጋር ያመሳስለዋል። በሌላ በኩል የበየነ ጥናት ፍትነታዊ /ሙከራዊ/ የምርምር ዘዴን የተከተለና ትኩረቱም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች የቋንቋውን ክሂሎች የሚያዳብሩ መሆን አለማሆናቸውን የሚፈትሽ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ያላቸውን አቀራረብና አደረጃጀት መተንተን በመሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

ሁለተኛው አንለይ (1987) "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽሕፈትን ክሂል ለማዳበር መልመጃዎች እንዴት መቅረብ አለባቸው?" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ

እንዲሆን ያካሄዱት ጥናት ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች አይነትና አቀራረባቸው ክሂሉን ለማዳበር ብቁ መሆን አለመሆናቸውን መገምገምና ክሂሉን ሊያዳብሩ የሚችሉ ናሙና መልመጃዎችን ማቅረብ ነው።

ጥናቱ በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ላይ ማተኮሩና የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች የቀረቡበትን ሁኔታ የሚፈትሽ መሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ያደርገዋል። በሌላ በኩል ጥናቶቹ በተለያዩ ጊዜያት በታተሙ መጻሕፍት ላይ ማተኮራቸውና በተለይ ይኼኛው ጥናት ሁሉንም የቋንቋ ክሂሎች የሚመለከቱ መልመጃዎች አቀራረባቸውንና አደረጃጀታቸውን የሚዳስስ መሆኑ ከአንለይ ጥናቱ ልዩ ያደርገዋል።

ሦስተኛው መስፍን (2000) "በአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡት መልመጃዎች ይዘትና አደረጃጀት ግምገማ በ11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተተኳሪነት" በሚል ርዕስ ላይ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ እንዲሆን የሠሩት ጥናታዊ ጽሑፍ ነው። የጥናቱ ዋና ዓላማ በ1998 ዓ.ም. ለ11ኛ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች የተዘጋጁት የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሐፎችን የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀትና የመልመጃዎችን ይዘት ተገቢነት መፈተሽ ነው።

ጥናቱ የሰነድ ምርመራን በዋና የመረጃ ምንጭነት እንዲሁም የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅን በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት ከመጠቀሙ በተጨማሪ በተጠቀሱት መጽሐፎች ውስጥ ያሉትን የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች ይዘትና አደረጃጀት መገምገሙ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ያመሳስላቸዋል። በአንጻሩ ደግሞ የክፍል ደረጃና ጥናቶቹ የተካሄዱበት ወቅት መለያየት እንዳለ ሆኖ ይኼኛው ጥናት አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት የሚተነትን መሆኑ ልዩ ያደርገዋል።

አራተኛው የሺጥላ (2000) "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ እንዲሆን ያካሄዱት ጥናት ነው። የጥናቱም ዋና ዓላማ በ1997 ዓ.ም. ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ያለው አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ አንብቦ የመረዳትን ችሎታ ለማዳበር በሚያግዝ መንገድ መቅረቡን መፈተሽ ነው።

ጥናቱ በክፍል ደረጃ እንዲሁም በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተመሳሳይነት አለው። በሌላ በኩል ሲታይ የየሺጥላ ጥናት ቀደም ሲል በነበረው መጽሐፍ ውስጥ በሚገኙ ምንባቦችና

ከምንባቦቹ በተወጣጡ የአንብቦ መረዳት መልመጃዎች ላይ ሲያተኩር ይህ ጥናት ግን አዲስ በተዘጋጀው መጽሐፍና በውስጡ በተካተቱ አራቱም የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ ማተኮሩ ልዩ ያደርገዋል፡፡

አምስተኛው አያልሰው (2003) "ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ" በሚል ርዕስ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ እንዲሆን ያካሄዱት ጥናት ነው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማም ከ9ኛ - 12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የተዘጋጁ ይዘቶችን አቀራረብ መተንተንና መገምገም ነው፡፡

የአያልሰው ጥናት የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ የንግግር ክሂል ይዘቶችን አቀራረብ የሚመለከት በመሆኑና በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ አጠቃቀም ከዚህኛው ጥናት ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት ቀደም ሲል እንደተገለጸው በ2004 ዓ.ም. አዲስ በተዘጋጀው መጽሐፍና በውስጡ በተካተቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ላይ በማተኮሩ ይለያል፡፡

በአጠቃላይ ቀደም ሲል የተጠቀሱት ሁሉም ጥናቶች በቀደሙት ጊዜያት አገልግሎት ላይ በነበሩ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻሕፍት ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዓቢይ ትኩረታቸውም በመጻሕፍቱ ውስጥ የቀረቡ መልመጃዎች ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አንዱን ወይም ከአንድ በላይ የሆኑ ክሂሎችን የማዳበር ብቃት የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህ ጥናት ግን በዋናነት በ2004 ዓ.ም. ተዘጋጅቶ በ2005 ዓ.ም. መተግበር በጀመረው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት የሚተነትን በመሆኑ ከሁሉም ጥናቶች እንደሚለይ መገንዘብ ይቻላል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

## የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ለመፈተሽ የተካሔደ ነው፡፡ ጥናቱም የተከተለው ዓይነታዊና መጠናዊ የምርምር ዘዴን "Qualitative & Quantitative Research Method" ነው፡፡ በመሆኑም የትንተና ዘዴም ከጥናቱ የተገኙ መረጃዎችን በዓይነትና በመጠን በማቀናጀት ገላጭ ስልትን "Descriptive Method" ተከትሎ የቀረበ ሲሆን ከሰነድ ፍተሻና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን መጠቀም ያስፈለገበት ምክንያት አጥኚው በተጠቀሰው መጽሐፍ ላይ ጥናት ባካሄደበት ወቅት ለግምገማው በተዘጋጁት መስፈርቶች አማካይነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች በዓይነት በዓይነት በማድረግ መተንተን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡ መጠናዊ የምርምር ዘዴ ደግሞ ለጥናቱ አጋዥ የመረጃ ምንጭ ከሆኑት መምህራን በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት ለተሰበሰቡት መረጃዎች የቁጥር መለኪያ በመስጠት ተንትኖ በመቶኛ ለማስቀመጥ አማራጭ ዘዴ በመሆኑ ነው፡፡

### 3.1. የመረጃ ምንጮች

ለዚህ ጥናት በመረጃ ምንጭነት ሊያገለግሉ የሚችሉ በርካታ አካላት ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ ሁሉንም አካላት በጥናቱ ለማካተት አጥኚው ካሉበት የጊዜ፣ የጉልበትና የገንዘብ ውስንነት የተነሳ በጥቂት ምንጮች ላይ ለመወሰን ተገዷል፡፡ ከእነዚህም መካከል የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በዋና የመረጃ ምንጭነት ያገለገለ ሲሆን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በሀዲያ ዞን ሆሳዕና ከተማ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት የመንግስትና አምስት የግል አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በአንድ የመንግስትና በሦስት የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት በመውሰድ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡

X

መምህራን ለጥናቱ በአጋዥ የመረጃ ምንጭነት የተመረጡበት ምክንያት የመጽሐፉ ዋነኛ ተጠቃሚ በመሆናቸው ስለመጽሐፉ ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ሁኔታ በቂ ግንዛቤ ይኖራቸዋል ተብሎ በመታመኑ ነው፡፡ በመሆኑም መምህራኑ ባላቸው ግንዛቤ መሠረት በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት የሰጡት ምላሽ ለጥናቱ አጋዥ መረጃ ሊሆን በመቻሉ ነው፡፡

## 3.2. የናሙና አመራረጥ

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ይቻል ዘንድ ለጥናቱ ተገቢውን መረጃ ሊሰጡ ወይም ሊያስገኙ ይችላሉ ተብለው የታመነባቸው ምንጮች በተለያዩ የናሙና አመራረጥ ስልቶች አማካይነት ተመርጠዋል፡፡

### 3.2.1 የጥናቱ ክልል አመራረጥ

በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልላዊ መንግስት፣ በሀዲያ ዞን ውስጥ ሆሳዕና ከተማ አጥኚው ተወልዶ ያደገበትና ረዘም ላለ ጊዜ በመምህርነት ሙያ የሰራበት አካባቢ ነው፡፡ ስለሆነም አጥኚው ከመምህራን አገኛቸዋለሁ ብሎ ላሰባቸው መረጃዎች አማራጭ በመሆኑ ሆሳዕና ከተማ የጥናቱ ክልል እንዲሆን በአመቺ የናሙና አመራረጥ (convenience sampling) ስልት በጥናቱ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

### 3.2.2. የትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ

በትምህርት ቤቶች ናሙና አመራረጥ ረገድ ለጥናቱ በተመረጠው ክልል ሁለት የመንግስትና አምስት የግል በድምሩ ሰባት አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡- 1. የካቲት 25/67 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 2. ሄጦ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 3. ዩናይትድ ቨ.ገርን አካዳሚ 4. ቨ.ገርን አካዳሚ 5. ኤፍ. ኤ. ኢንተርናሽናል አካዳሚ 6. ሐርቫርድ አካዳሚ እና 7. አክሌገርያ አካዳሚ ናቸው፡፡ ከእነዚህ መካከል የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የመንግስት ትምህርት ቤቶች ሲሆኑ ሌሎቹ የግል ትምህርት ቤቶች ናቸው፡፡

ጥናቱ በዋናነት የሚመለከተው ሰነድ ፍተሻን በመሆኑና ከመምህራን የሚገኘው መረጃ ለጥናቱ በአጋዥነት የሚያገለግል መሆኑ አስቀድሞ ስለታመነበት ሁሉንም ትምህርት ቤቶች

በተሳታፊነት መውሰድ አላስፈለገም። ስለሆነም ከሁለቱ የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል አንዱ፣ እንዲሁም ከአምስቱ የግል ትምህርት ቤቶች መካከል ሦስቱ በተራ የዕጣ ናሙና ዘዴ (simple random sampling) በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል።

በወጣውም ዕጣ መሠረት በከተማዋ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት የመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል የካቲት 25/67 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ እንዲሁም ከአምስቱ የግል ትምህርት ቤቶች መካከል ዩናይትድ ቪዥን አካዳሚ፣ ቪዥን አካዳሚ እና ኤፍ.ኤ. ኢንተርናሽናል አካዳሚ በድምሩ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጥናቱ ተሳታፊነት ተመርጠዋል።

### 3.2.3. የዘጠነኛ ክፍል አመራረጥ

አጥኚው በሁለተኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ለአምስት ዓመታት ያህል ሲያገለግል መቆየቱ ቀደም ሲል ተጠቁሟል። በዚህ ምክንያት ከዚህ ቀደም በአገልግሎት ላይ ዉሎ የነበረውን የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በቅርበት ያውቀዋል። በመሆኑም በመጽሐፉ ውስጥ ተካተው የነበሩ የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ችግሮች አዲስ በተዘጋጀው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ ምን ያህል መሻሻል እንዳሳዩ ሳይንሳዊ መርሆችን በመከተል መመርመር አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል። በመሆኑም የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በዓላማ-ተኮር የናሙና አመራረጥ (purposive sampling) ስልት ተመርጧል።

### 3.2.4. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በጥናቱ እንዲሳተፉ የተመረጡት ትምህርት ቤቶች ብዛት አራት መሆናቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል። ከመንግስት ትምህርት ቤቶች መካከል በተመረጠው በየካቲት 25/67 አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የሚገኙት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አሥራ ሁለት ሲሆኑ ከአሥራ ሁለቱም መካከል ለዘጠነኛና ለአሥረኛ ክፍል ተብለው ሳይለዩ ሁሉም መምህራን ከ9ኛ እስከ 10ኛ ያሉትን ክፍሎች የሚያስተምሩ ሆነው ተገኝተዋል። በመሆኑም ከአሥራ ሁለቱ መካከል ስድስቱ ለጥናቱ በመረጃ ምንጭነት እንዲያገለግሉ በተራ የዕጣ ናሙና ዘዴ (simple random sampling) አማካይነት ተመርጠዋል።

እንዲሁም ከአምስቱ የግል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል ከተመረጡት ሦስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንዱ ሁለት መምህራን ሲገኙ በሌሎቹ አንዳንድ በድምሩ አራት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተገኝተዋል። ስለሆነም ወካይ ናሙና መምረጥ አስፈላጊ ባለመሆኑ አራቱም መምህራን በጠቅላይ ናሙና ዘዴ (availability sampling) በጥናቱ እንዲሳተፉ ተደርገዋል።

በሌላ በኩል በተመረጡት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚገኙ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በተጨማሪ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በጥናቱ ተሳታፊነት እንደሚመረጡ አስቀድሞ ታስቦ ነበር። ይሁን እንጂ የመማሪያ መጽሐፉ በ2005 ዓ.ም. ሥራ ላይ የዋለና ተማሪዎቹ ቅጂውን ያላገኙት በመሆናቸውና መረጃን በሚፈለገው ሁኔታ ሊሰጡ እንደሚቸገሩ በመግለጻቸው ከጥናቱ ተሳታፊነት እንዲገለሉ ተደርጓል።

## 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የጥናቱን ዓላማ ከግብ እንዲያደርሱ ሁለት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተመርጠዋል። እነሱም፦ ሰነድ ፍተሻ እና የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው።

### 3.3.1. የሰነድ ፍተሻ

የሰነድ ፍተሻ ለዚህ ጥናት ዓላማ ከግብ መድረስ ትልቁን ድርሻ የያዘ ነው። ይህም ያተኮረው በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችንና መልመጃዎችን አቀራረብና አደረጃጀት በተለያዩ መረጃዎች አስደግፎ በመተንተን ላይ ነው። ለዚህም እንዲያግዝ የክሂል ይዘቶች በተለያዩ ንድፈ-ሐሳቦች አማካይነት የተቃኙ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ንድፈ-ሐሳቦቹን መሠረት ያደረጉ የመገምገሚያ መስፈርቶች ተዘጋጅተው ጥቅም ላይ ውለዋል። ይሁን እንጂ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ከሁሉም መስፈርቶች አንጻር አሥሩንም ምዕራፎች መመልከት ባለመቻሉ የተወሰኑ ምዕራፎች እንዲቀሩ ተደርገዋል። ለዚህም ምክንያቱ ያልተዳሰሱ ምዕራፎች ምርመራ ከተደረገባቸው ምዕራፎች ጋር ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው በመሆናቸው ነው።

### 3.3.2. የጽሑፍ መጠይቅ

የጽሑፍ መጠይቅ ከሰነድ ፍተሻ ለሚገኙ መረጃዎች በማጠናከሪያነት እንዲገለግሉ ታስበው የተዘጋጁ ናቸው። የጽሑፍ መጠይቅ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚመረጠው ጊዜን ጉልበትንና ገንዘብን የሚቆጥብ በመሆኑ፣ የመላሾችን ማንነት ስለማይገልጽ መላሾቹ አስተማማኝ መረጃ እንዲሰጡ ስለሚያስችል፣ እንዲሁም ለሁሉም ተጠኒዎች አንድ ዓይነት ጥያቄ ለማቅረብ ስለሚያስችል ነው (ያለው 2004)። ለዚህ ዓላማ የዋሉ የጽሑፍ መጠይቆች በዝግ እና በክፍት የአቀራረብ ስልት ተዘጋጅተውና ለጥናቱ ተሳታፊ መምህራን ቀርበው ምላሽ እንዲሰጥባቸው ተደርገዋል።

## 3.4. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዓቢይ የመረጃ ምንጭ ሰነድ ፍተሻ መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቁሟል። የሰነድ ፍተሻ ዋነኛ ዓላማ ለጥናቱ በተመረጠው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀትን በጥልቀት ማጤን ነው። ይህን መረጃ አስተማማኝ ከማድረግ ረገድ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክተዋል።

በመሆኑም የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችንና መልመጃዎችን አቀራረብና አደረጃጀት አስመልክተው ቀደም ሲል በተጠቀሱት ሁለቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች በቅድሚያ ከተመሳሳይነታቸው አንፃር በየንዑስ ርዕሳቸው ስር ተከፍለዋል። በመቀጠልም መረጃዎቹ ከአጥኚው እይታ አንጻር በገላጭ የአተናተን ስልት ከተተነተኑ በኋላ የጽሑፍ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን እይታ አንጻር የቁጥር መለኪያ ተሰጥቷቸው በመቶኛ ተገልጸዋል።

# ምዕራፍ አራት

## የመረጃ ትንተናና የጥናቱ ውጤት

ቀደም ባሉት ክፍሎች እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዓቢይ አላማ በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ክሂል ይዘቶችንና መልመጃዎችን አቀራረብና አደረጃጀት ለመተንተን ነው፡፡

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስ በመረጃ ምንጭነት ካገለገሉት መካከል ሰነድ ፍተሻ በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች በአጋዥነት አገልግለዋል፡፡ ለዚህም የጽሑፍ መጠይቅ ተዘጋጅቶ በመምህራን የተሞላ ሲሆን በሌላ በኩል አጥኚው በሰነድ ፍተሻ ወቅት መጽሐፉ ላይ ላካሔደው ቅኝት የጽሑፍ መጠይቆቹ በመስፈርትነት በአገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በመጨረሻም ከሰነድ ፍተሻና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ከዝምድናቸው አኳያ በንዑስ ርዕስ ተከፋፍለው በገላጭ የምርምር ዘዴ ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 1፣ የጽሑፍ መጠይቅ ስለሞሉ መምህራን የተገኘ አጠቃላይ መረጃ*

| ፆታ | መላሾች | | የትም/ ደረጃ | መላሾች | | የስልጠና ዘርፍ | መላሾች | | የአገል/ ዘመን | መላሾች | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በቁ. | በመቶኛ | | በቁ. | በመቶኛ | | በቁ. | በመቶኛ | | በቁ | በመቶኛ |
| ወ | 4 | 40 | ሰርቲፍኬት | - | - | ሁለገብ | - | - | 1-5 | 4 | 40 |
| ሴ | 6 | 60 | ዲፕሎማ | - | - | አማርኛ | 9 | 90 | 6-10 | 3 | 30 |
| - | - | - | ዲግሪ | 10 | 100 | ጋዜጠኝነት | 1 | 10 | 11-15 | 2 | 20 |
| - | - | - | ማስተርስ | - | - | ሌላ | - | - | 16-20 | - | - |
| - | - | - | - | - | - | - | - | - | 20 በላይ | 1 | 10 |
| ድምር | 10 | 100 | ድምር | 10 | 100 | ድምር | 10 | 100 | ድምር | 10 | 100 |

ይህ ሠንጠረዥ የሚያስገነዝበን መጠይቁን የሞሉት ሁሉም መምህራን ከከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የተመረቁና የተለያየ የአገልግሎት ደረጃ ያላቸው መሆናቸውን ነው፡፡ የስልጠና ደረጃቸው ደግሞ በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲ መሠረት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚያስተምሩ መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ ሊኖራቸው ይገባል የሚለው ደንብ በትክክል ተግባራዊ መደረጉን ያመላከተ ነው፡፡ የስልጠና ዘርፍን በሚመለከት መጠይቁን ከሞሉት አሥር መምህራን መካከል ዘጠኙ በአማርኛ ቋንቋ የሰለጠኑ ሲሆኑ አንዱ በጋዜጠኝነት ሙያ የሰለጠነ መሆኑን መረጃው ያመለክታል፡፡ ስለሆነም ዘጠኙ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ የሰለጠኑ በመሆናቸው የሚሰጡት መረጃ ለጥናቱ ተገቢና ተአማኒ እንደሚሆን ይገመታል፡፡

የጽሑፍ መጠይቆቹ በቁጥር አርባ አንድ ቢሆኑም አጠቃላይ ይዘታቸው ሲታይ ግን በሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያነጣጠሩ ናቸው፤ የክሂል ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት በሚሉ። በዚህ መሠረት እነዚህ ሁለት ዓበይት ጉዳዮችና በውስጣቸው የተካተቱ ሌሎች ንዑሳን ነጥቦች በጥናቱ ውስጥ በጥልቀት ተመርምረዋል።

## 4.1. የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ

የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በአሥር ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን በሁሉም ምዕራፎች ስር የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ቀርበዋል። ለዚህ የመረጃ ትንተና ያመች ዘንድ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ በሚል ንዑስ ርዕስ ለይቶ መመልከቱ ተገቢ ነው። በዚህም መሠረት ከርዕሱ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ጥያቄዎች ከአጥኚው እይታና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ አኳያ እንደሚከተለው ተተንትነዋል።

መጽሐፉ በአጠቃላይ በአሥር ምዕራፎች ተከፋፍሎ የቀረበ ሲሆን ለሁሉም ምዕራፎች ትምህርት መግቢያ እንዲሆኑ የቅድመ ንባብ መልመጃዎች ቀርበውላቸዋል፤ በበርካታ ምዕራፎች ደግሞ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በምንባቦቹ መካከል ላይ ሲቀርቡ እንዲሁም ለሁሉም ምዕራፎች የድኅረ ንባብ ጥያቄዎች በዓይነትም ሆነ በመጠን በብዛት ቀርበዋል።

የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ባሕርይ ሲጤን የተማሪዎችን ቀደምት ልምድ የሚመለከቱ፣ ቀጥሎ ወደሚማሩት ትምህርት የሚያንደረድሩ፣ በቃል አሊያም በጽሑፍ የሚመለሱ፣ የተማሪዎችን የመማር ሂደት ገና ከጅማሮው የሚያመቻቹ፣ ወዘተ. ናቸው። ለዚህም ማሳያ እንዲሆኑ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል ምዕራፍ አንድ፣ "ቋንቋና ህብረተሰብ" ቅድመ ንባብ ጥያቄ 1. ቋንቋ ምንድነው? 2. ቋንቋ በማኅበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድን ነው? የሚሉ እና ሌሎችም ይገኙበታል። ምዕራፍ ሁለት፣ "ስነ-ቃል" ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች 1. ተረት አውርታችሁ ወይም ሲወራ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? 2. ተረት ማዳመጥ የሚሰጠው ጥቅም ምንድነው? የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል። ሁሉም ምዕራፎች እነዚህን የመሳሰሉ ጥያቄዎችን በመነሻቸው ላይ የያዙ ናቸው /አባሪ ሁለትን ይመልከቱ/።

የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ በማንበብ ሂደት መካከል ቆም ብለው ስላነበቡት ጉዳይ እንዲያስቡ፣ ቀጥሎ ምን ሊከሰት እንደሚችል እንዲገምቱ፣ የራሳቸውን የአንብቦ መረዳት

ችሎታ እንዲገልጹ፣ ወዘተ. የሚያበረታቱ ናቸው። ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ፣ "ቋንቋና ህብረተሰብ" የንባብ ጊዜ ጥያቄ 1. ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው ካልን፣ እንስሳትም ድምጽ በማውጣት መልዕክት ይለዋወጣሉ። ይህን የእንስሳት መግባቢያ ቋንቋ ነው ልንለው እንችላለን? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናገሩ። ምዕራፍ ሦስት፣ "ቤተ-መጻሕፍትና የስነ-ጽሑፍ" የንባብ ጊዜ ጥያቄ 1. ደራስያን ለምን ይጽፋሉ? ወይም እንዲጽፉ የሚያነሳሳቸው ምክንያት ምንድነው? የሚሉ ይገኙበታል። እነዚህን የመሳሰሉ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙት በአብዛኞቹ ምዕራፎች ውስጥ ይገኛሉ /አባሪ ሦስትን ይመልከቱ/።

የድኅረ ንባብ ጥያቄዎች ተማሪዎች ካነበቡት ርዕሰ ጉዳይ በመነሳት የቋንቋ ክሂሎቻቸውን እንዲያዳብሩ የሚያግዙ ናቸው። በዚህ ስር የቀረቡ ጥያቄዎች በአይነትም ሆነ በቁጥር ቀደም ሲል ከተጠቀሱት በርከት ያሉ ናቸው። ጥያቄዎቹ የቀረቡበት ስልት ሲጤን በክሂሎች ርዕስ (ንባብ፣ ንግግር፣ ማዳመጥ እና ጽሕፈት) ተከፋፍለውና ለእያንዳንዱ ክሂል ከልምምድ ጋር በተያያዙ ጥያቄዎች ታግዘው መሆናቸው ተመልክቷል። ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ መመሪያ 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፤ 1. ዘዬ ምንድን ነው? ወዘተ. ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፤ 1. ዘዬ እንዴት ይፈጠራል? ወዘተ. ክፍል ሦስት፡- ማዳመጥ፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ "ኢ-መደበኛ ቋንቋ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፤ 1. እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፣ ወዘተ. ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ ...በምሳሌው መሠረት በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦችን በሠንጠረዥ አስፍሩ /አባሪ አራትን ይመልከቱ/። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*ሠንጠረዥ 2፣ መልመጃዎቹ ለመማር ማስተማርና ለክሂሎች ልምምድ ያላቸው አመቺነት*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ ነው። | 4 (40%) | 5 (50%) | - | 1 (10%) | - |
| 4 | መልመጃዎቹ ለክሂሎች ልምምድ አመቺ ናቸው። | 4 (40%) | 4 (40%) | 2 (20%) | - | - |
| 3 | የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ተጣጣሚነት አላቸው። | - | 2 (20%) | - | 3 (30%) | 5 (50%) |

በጥያቄ ቁጥር 1፣ የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ለመማር-ማስተማሩ ሂደት አመቺ ነው፣ በሚል ለተነሳው ጥያቄ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 5(50)% ሲሆኑ እንዲሁም "አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን ያስፈሩት 1(10%) ናቸው።

እንዲሁም በጥያቄ ቁጥር 4፣ መልመጃዎቹ ለክሂሎች ልምምድ አመቺ ናቸው፣ ተብሎ ለተነሳላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" በማለት ምላሽ የሰጡት 4(40%) ሲሆኑ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ የመለሱት 2(20%) ናቸው። ከእነዚህ የአሃዝ መረጃዎች መረዳት የሚቻለው የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ በአብዛኛው ለመማር-ማስተማር ሂደትና ለቋንቋ ልምምድ አመቺ መሆናቸውን ነው። መልመጃዎቹን መጽሐፉ በሚያዘው መሠረት ለማስተማር ያላቸውን አመቺነት በሚመለከት መምህራኑ በክፍት መጠይቅ የሰጡት ምላሽም ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ አጥኚው ጉዳዩን አስመልክቶ በመጽሐፉ ላይ ምርመራ ባካሄደበት ወቅት ካገኘው መረጃ ጋር የሚመሳሰል ነው። በዚህም መሠረት በመጽሐፉ ውስጥ በቅድመ ንባብ ጊዜ፣ በንባብ ጊዜ እንዲሁም በድኅረ ንባብ ጊዜ ተማሪዎች በቋንቋው ተጠቅመው ክሂሎችን እንዲለማመዱ ታስበው የተዘጋጁ የክሂል መልመጃዎች አቀራረብ ለተማሪዎቹ የመማር ብሎም ለመምህራኑ የማስተማር ሂደት አመቺ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል።

የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ያላቸውን ተጣጣሚነት ለማነጻጸር እንዲያመች በቅድሚያ ይዘቶችንና የተመደበላቸውን ሰዓት በጥቂቱ ማየት ተገቢ ነው። ይህን በምዕራፍ አንድ ምሳሌነት ስናየው ለጠቅላላ የምዕራፍ ትምህርት የተፈቀደው ሰዓት አራት ክፍለ ጊዜ ነው። በምዕራፉ መግቢያ ላይ የሚገኙ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ብዛት ሦስት ሲሆኑ በትክክል ከተተገበሩ አንድ ክፍለ ጊዜን ሊወስዱ ይችላሉ። ቀጥሎም ምንባቡ ሦስት ተኩል ገጾች ሲኖሩት በንባብ መካከልም ውይይት ተካሄዶበት የሚመለስ አንድ ጥያቄ ይገኛል። በዚህ ጥያቄ ላይ ለመወያትና ምንባቡን እስኪረዱት ድረስ ደጋግሞ ለማንበብም እንዲሁ አንድ ክፍለ ጊዜ ይወስዳል ተብሎ ይገመታል። ከምንባብ ቀጥሎ ወዳሉት የቋንቋ ልምምድ ተግባራት ስናመራ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች የሚመለከቱ በቁጥር በርካታ መልመጃዎችና የክለሳ ጥያቄዎች ይገኙበታል። ይህ ዓይነቱ ሁኔታ ምዕራፍ ሁለትን ጨምሮ በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙ ሌሎች ምዕራፎችም ውስጥ የሚታይ ነው።

ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ የመልመጃ ጥያቄዎች ባላቸው ትዕዛዝ መሠረት ለማከናወን የማያስችሉና ከተመደበላቸው ሰዓት ጋር የማይጣጣሙ ናቸው። ለምሳሌ ምዕራፍ ሦስት፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ ገጽ 44፣ መመሪያ 2 "ባለፈው ሳምንት ያሳለፋችሁትን የእሁድ ቀን ውሎ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ ከ3 - 5 ደቂቃ የሚረዝም ንግግር አድርጉ" የሚል ይገኝበታል። በአጠቃላይ ለምዕራፉ ትምህርት የተፈቀደው ሰዓት ስድስት ክፍለ ጊዜ ብቻ ነው። በአንድ ክፍል ውስጥ ስማንያ ተማሪ ይኖራል ተብሎ ቢታሰብና ሁሉም ተማሪዎች አምስት አምስት ደቂቃ ተጠቅመው የታዘዙትን ንግግር ቢያደርጉ በአጠቃላይ የሚያስፈልጋቸው የክፍለ ጊዜ መጠን አሥር ይሆናል። ስለሆነም ለጠቅላላ የምዕራፉ ትምህርት የተፈቀደው ሰዓት ስድስት ክፍለ ጊዜ ሆኖ ሳለ ይህ አንድ መልመጃ ግን ብቻውን አሥር ክፍለ ጊዜ ሊወስድ የሚችል መሆኑ ለዚህ ማረጋገጫ ነው። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

በጥያቄ ቁጥር 3፣ የመልመጃዎቹ አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ተጣጣሚነት አላቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ እንደሚያመለክተው "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 2(20%)፣ "አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን ያሰፈሩት 3(30%) ሲሆኑ እንዲሁም "ፈጽሞ አልስማማም" በማለት መጠይቁን የሞሉት 5(50%) ናቸው። "አልስማማም" እና "ፈጽሞ አልስማማም" በማለት የመለሱበት ምክንያት መልመጃዎቹ በተፈቀደው ጊዜ ሊጠናቀቁ የማይችሉ በመሆናቸው ነው።

በአጠቃላይ አጥኚው ከመጽሐፉ ምርመራ እንዲሁም ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ መረጃዎች መረዳት እንደቻለው ለያንዳንዱ መልመጃ ተገቢውን ምላሽ ለመስጠት፣ ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል ደረጃ ለመከታተልና ለማሳተፍ ሲታሰብ በአብዛኞቹ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ የክሂል መልመጃዎችና ለመልመጃዎቹ የተመደበው ሰዓት ተጣጣሚነት የሌላቸው መሆናቸውን ነው። ይህ በሚሆንበት ጊዜ ደግሞ መምህራን ከጊዜ ጋር ለመጓዝ ሲሉ ተማሪዎች ሳይለማመዱባቸው የሚዘሏቸው መልመጃዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ ለመምህራን በክፍት መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ ያመለክታል።

የቋንቋ ትምህርት አጠቃላይ ዓላማ አራቱን የክሂልና ሁለቱን የዕውቀት ዘርፎች ማዳበር መሆኑ ቀደም ባሉት ክፍሎች በዝርዝር ተመልክቷል። የክሂል ዘርፎችን ለማሳካት እንዲረዱ የተዘጋጁት መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡበት ደረጃ በመጠንም ሆነ በቁጥር የተለያዩ ሆነው ተገኝተዋል። ይህን ጉዳይ በሁለት መልኩ ማየት የሚቻል ሲሆን የመጀመሪያው

አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች የሚመለከቱ ርዕሶች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ፣ መጻፍ) የቀረቡበት መጠን ሲሆን ሁለተኛው በያንዳንዱ የክሂል ርዕስ ስር የቀረቡትን የመለማመጃ ጥያቄዎች ቁጥር የሚመለከት ነው።

በክሂል ርዕስ ደረጃ ስንመለከት አራቱም የቋንቋ ክሂሎች ራሳቸውን ችለውና ርዕስ ተሰጥቷቸው የቀረቡባቸው ምዕራፎች ከአሥሩ መካከል በሦስቱ (በምዕራፍ 1፣ 3 እና 4) ብቻ ነው። በቀሩት ሰባቱ ምዕራፎች ውስጥ የንባብ፣ የንግግር እና የጽሕፈት ክሂሎች ሲኖሩ የማዳመጥ ክሂል ግን እንደ ሌሎቹ ክሂሎች ርዕስ ተሰጥቶት አልቀረበም። ይህንን በአጭሩ ከሚከተለው ሠንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል።

*ሠንጠረዥ 3፣ ክሂሎች በምዕራፎቹ ውስጥ ርዕስ ተሰጥቷቸው የቀረቡበት ደረጃ*

| ክሂል | ም.1 | ም.2 | ም.3 | ም.4 | ም.5 | ም.6 | ም.7 | ም.8 | ም.9 | ም.10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ማዳመጥ | ✓ | - | ✓ | ✓ | - | - | - | - | - | - |
| መናገር | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| ማንበብ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |
| መጻፍ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ |

ከዚህ ሠንጠረዥ መገንዘብ የሚቻለው መናገር፣ ማንበብና መጻፍ በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ትኩረት ተሰጥቷቸው፣ በርዕስነት ተሰይመውና በስራቸው የተለያዩ የመለማመጃ ጥያቄዎችን አካተው መቅረባቸውን ነው። በአንጻሩም በአብዛኞቹ ምዕራፎች ውስጥ የማዳመጥ ክሂል ብዙም ትኩረት እንዳልተሰጠው መገንዘብ ይቻላል። ከመልመጃ ጥያቄዎች ቁጥር አንጻር ስንመለከታቸውም በሦስቱ ምዕራፎች ስር የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በቁጥርም በጣም ጥቂት ናቸው። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*ሠንጠረዥ 4፣ አራቱም የቋንቋ ክሂል ይዘቶች በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡበት ሁኔታ*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | አራቱም የቋንቋ ክሂሎች በመልመጃዎቹ ላይ በእኩል ደረጃ ቀርበዋል። | 1 (10%) | 1 (10%) | 3 (30%) | 3 (30%) | 2 (20%) |
| 20 | መጽሐፉ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር የሚያስችሉ በቂ ይዘቶችን አሟልቶ ይዟል። | 2 (20%) | 2 (20%) | 1 (10%) | 3 (30%) | 2 (20%) |

በጥያቄ ቁጥር 5፣ አራቱም የቋንቋ ክሂሎች በመልመጃዎቹ ላይ በእኩል ደረጃ ቀርበዋል፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 1(10%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 1(10%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ የገለጹት 3(30%)፣ "አልስማማም" በማለት የመላሱት ደግሞ 3(30%) ሲሆኑ

"ፈጽሞ አልስማማም" ያሉት 2(20%) ናቸው፡፡ ይህ መረጃ የሚያመለክተው አራቱም የክሂል መልመጃዎች የቀረቡበት ደረጃ እኩል አለመሆኑንና ለክሂሎቹ ተመሳሳይ ትኩረት አለመሰጠቱን ነው፡፡ በክፍት መጠይቅ መጽሐፉ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል በይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው ለየትኛው ነው? ሲል ለቀረበላቸው ጥያቄ በአብዛኛው ለንባብና ለንግግር የሚል ምላሽ ሰፍሯል፡፡

እንደዚሁም በጥያቄ ቁጥር 20፣ መጽሐፉ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር የሚያስችሉ በቂ ይዘቶችን አሟልቶ ይዟል፣ በሚል ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 2(20%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 2(20%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት የመለሱት 1(10%)፣ "አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 3(30%) ሲሆን "ፈጽሞ አልስማማም" ያሉት 2(20%) ናቸው፡፡ ከዚህ የአሃዝ መረጃ መረዳት የሚቻለው በመጽሐፉ ውስጥ ካሉት ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል በቂ የመለማመጃ ይዘቶች ኖሯቸው የቀረቡ ክሂሎች የመኖራቸውን ያህል በበቂ ይዘቶች ያልታገዙ ክሂሎችም መኖራቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከመጽሐፉ ይዘቶች ቅኝት እንዲሁም ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ እንደተቻለው፣ በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡ የቋንቋ ክሂሎች መካከል ንባብና ንግግር ሰፊ ሽፋን ተሰጥቷቸዋል፡፡ ከንባብና ከንግግር ቀጥሎ የጽሕፈት ክሂል መካከለኛ ሽፋን ሲሰጠው በአንጻሩም የማዳመጥ ክሂል ግን በጣም ውስን ሽፋን የተሰጠው መሆኑን መረዳት ትችሏል፡፡

ቀደም ሲል እንደተጠቆመው መጽሐፉ በአሥር ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ በአሥሩም ምዕራፎች የንባብ፣ የንግግርና የጽሕፈት ክሂሎች ርዕስ ተሰጥቷቸው መጠናቸው ቢለያይም በስራቸው የመለማመጃ ጥያቄዎች ቀርበውላቸዋል፡፡ የማዳመጥ ክሂል ግን በሦስት ምዕራፎች ብቻ በርዕስነት የተገለጸ ሲሆን በስራቸውም የቀረቡት የመለማመጃ ጥያቄዎች በቂ አይደሉም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የንባብ፣ የንግግርና የጽሕፈት ክሂሎች በሚተገበሩበት ጊዜ እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉና አንዱ ለሌላኛው መዳበር ጉልህ ድርሻ እንደሚኖራቸው ይታወቃል፡፡ በአንጻሩ ለማዳመጥ ክሂል የሚሆን የትምህርት ይዘት ተለይቶ ካልቀረበ በአንድ በኩል ለክሂሉ የተሰጠው ቦታ አነስተኛ ስለሚሆን ተማሪዎችም ክሂሉን ለማዳበር እንደሚቸገሩ ማሰብ አያዳግትም፡፡ ይህን ከመጽሐፉ ውስጥ አንድ ምዕራፍ በመውሰድ ማየት ይቻላል፡፡

ምዕራፍ ሁለት "ስነ-ቃል" በሚል ምንባብ ስር ለንባብ ክሂል ዘጠኝ ጥያቄዎች፣ ለንግግር ክሂል ስድስት ጥያቄዎች እንዲሁም ለጽሕፈት ክሂል አሥር ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ ነገር ግን በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የማዳመጥን ክሂል አስመልክቶ ርዕስም ሆነ ካዳመጡት ነገር ተነስተው በቃል ወይም በጽሑፍ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች የቀረቡበት ቦታ አልታየም፡፡

ሌሎቹ ሦስቱም (የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ) ክሂሎች እርስ በርስ ስለሚደጋገፉበት ሁኔታ ማሳያ እንዲሆን አንድ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ምዕራፍ አምስት፣ ገጽ 85፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ መልመጃ 1 "የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ በጥሞና *አንብቡና* 'እሱ' የተባለው ሰው ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለው፣ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ የቱን ያህል ጎጂ እንደሆነ *ጽፉችሁ* ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡ ባቀረባችሁት ላይም *ተወያዩ*"፤ ሲል ያዛል፡፡

በሌላ በኩል የንግግር ክሂል በርዕስነት ቀርቦ ነገር ግን በስሩ ንግግርን የሚመለከት ምንም ዓይነት የመለማመጃ ጥያቄ ያልቀረበበት ሁኔታ እንዳለ ከመጽሐፉ ምዕራፍ ስድስት፣ ገጽ 104፣ ክፍል ሁለት፡- "ንግግር"፣ ከሚለው ይዘት ማየት ይቻላል፡፡ በዚህ ርዕስ ስር የቀረቡትን ጥያቄዎች ስንመለከታቸው 1. አንድ የተውኔት ጽሑፍ ምረጡ፤ 2. የመረጣችሁት የተውኔት ታሪክ ዋና ዋና ነጥቦችን ለይታችሁ መዝግቡ፤ 3. የተውኔት ታሪኩ ከምትኖሩበት የእውነት ዓለም ጋር እንዴት ያለ ግንኙነት እንዳለው አጭር ማስታወሻ ጽፉችሁ ማብራሪያ ስጡ የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ መልመጃዎች ለንግግር ክሂል ታስበው የተዘጋጁ ናቸው፤ ነገር ግን ትኩረታቸው ንግግር ሳይሆን የጽሕፈት ክሂልን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 5፣ የክሂል መላመጃዎቹ በተገቢ ሁኔታ እንዲሁም ተሟልተው ስለመቅረባቸው*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 7 | እያንዳንዱ የክሂል ይዘት በተገቢ የመለማመጃ ጥያቄዎች ታግዞ ቀርቧል፡፡ | 3 (30%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 2 (20%) | - |
| 2 | የክሂል መልመጃ ጥያቄዎቹ ተሟልተው የቀረቡ ናቸው፡፡ | 2 (20%) | 6 (60%) | 1 (10%) | 1 (10%) | - |

በጥያቄ ቁጥር 7፣ እያንዳንዱ የክሂል ይዘት በተገቢ የመለማመጃ ጥያቄዎች ታግዞ ቀርቧል፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ የተሰጠው ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 3(30%)፣ "ለመወሰን

እችገራለሁ" ሲሉ ምላሻቸውን ያሰፈሩት 2(20%) ሲሆኑ "አልስማማም" ሲሉ የመለሱት ደግሞ 2(20%) ናቸው፡፡

በጥያቄ ቁጥር 2፣ የክሂል መልመጃዎቹ ተሟልተው የቀረቡ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለተነሳላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ በጣም እስማማለሁ ያሉት 2(20%)፣ እስማማለሁ በማለት የመለሱት 6(60%)፣ ለመወሰን እቸገራለሁ ሲሉ መጠይቁን የሞሉት 1(10%) ሲሆኑ አልስማማም ብለው የመለሱት 1(10%) ናቸው፡፡ ከእነዚህ የአሃዝ መረጃዎች መረዳት የሚቻለው የክሂል ይዘቶቹ በአብዛኛው በተገቢ የመለማመጃ ጥያቄዎች ታግዘውና ተሟልተው መቅረባቸውን ሲሆን በሌላ በኩል ግን የክሂል ርዕሶችና የመልመጃ ጥያቄዎች ከተዛምዶ አንጻር አልፎ አልፎ ችግሮች መኖራቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ ከመምህራን የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው ሁሉም የክሂል መልመጃዎች በተገቢ መለማመጃ ጥያቄዎች ታግዘውና ተሟልተው መቅረባቸውን ነው፡፡ ነገር ግን ከአጥኚው እይታ አንጻር ሲታይ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል ሦስቱ ከሞላ ጎደል በተገቢ የመለማመጃ ጥያቄዎች ታግዘው መቅረባቸውና የማዳመጥ ክሂል ግን በበቂ መልመጃዎች አለመታገዙና ተሟልቶ አለመቅረቡ ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አልፎ አልፎ በአንዳንድ ምዕራፎች ለተወሰኑ ክሂሎች በቂ የመለማመጃ ጥያቄዎች እንዳልቀረቡ ብሎም ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው ምንም ጥያቄ ሳይቀርብበት የተዘለለ ክሂልም እንዳለ ማወቅ ተችሏል፡፡

በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ለቅድመ ንባብ፣ ለንባብ ጊዜ እና ለድኅረ ንባብ ጊዜ የልምምድ ተግባራት ታስበው የቀረቡ መልመጃዎች ለቋንቋው ልምምድ ተስማሚ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በእያንዳንዱ የመለማመጃ ወቅት በየትኛው ክሂል ላይ ትኩረት ሊሰጥ እንደሚገባ በሚያሳይ መልኩ በርዕስ ተለይቶ በግልጽ ቀርቧል፡፡ ይህ አቀራረብ በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙ አሥሩም ምዕራፎች የታየ ሲሆን አንዱን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡፡

ምዕራፍ አራት፣ "ልቦለድ" ከሚለው ርዕስ አስቀድሞ ስለልቦለድ ዓይነቶች አራት የተለያዩ ጥያቄዎችን በማንሳት ተማሪዎች የንግግር ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያግዙ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያዛል፡፡ በምንባቡ መካከል ላይ ደግሞ በድኅረ ንባብ ጊዜ ስለገመቱትና ካነበቡት ውስጥ ስላገኙት ነገር መመሳሰልና መለያየት እንደዚሁም ቀጥሎ በሚያነቡት የጽሑፉ አካል ስለሚከሰት ጉዳይ እንዲገልጹ ሲጠይቃቸው ይታያል፡፡ በድኅረ ንባብ ጊዜ ልምምድ

የሚደረግባቸውን መልመጃዎች ስንመለከት ተማሪዎች ያነበቡትን ምንባብ መሠረት በማድረግ በቃልና በጽሑፍ የሚመልሷቸው የተላያዩ በርካታ ጥያቄዎች ቀርበዋል፡፡ የክሂል መልመጃዎቹ በምዕራፉ ውስጥ በዓይነትም ሆነ በቁጥር በስፋት ከመቅረባቸው በተጨማሪ በርዕስ ተለይተው (ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ ክፍል ሁለት፡- ማዳመጥ፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት) ማራኪና ሳቢ በሆነ ስልት ቀርበዋል፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 6፣ የክሂል መልመጃዎች አቀራረብ ማራኪ፣ ሳቢና ተገቢ ስለመሆናቸው*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 9 | የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ማራኪነትና ሳቢነት አላቸው፡፡ | 4 (40%) | 4 (40%) | 1 (10%) | - | 1 (10%) |
| 8 | ለክሂል መልመጃዎቹ ተገቢ የሆኑ መመሪያዎች ተሰጥተዋል፡፡ | 3 (30%) | 2 (20%) | 2 (20%) | 2 (20%) | 1 (10%) |

በጥያቄ ቁጥር 9፣ የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ማራኪነትና ሳቢነት አላቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 4(40%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት 1(10%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን ያስፈሩት 1(10%) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ አጥኚው በሰነድ ፍተሻ ወቅት ያገኛቸው፣ እንዲሁም በጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት ከመምህራን ያገኛቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በመጽሐፉ ውስጥ ለቋንቋ ክሂሎች ልምምድ እንዲሆኑ የቀረቡ መልመጃዎች ሳቢና ማራኪ መሆናቸውን መረዳት ተችሏል፡፡

እያንዳንዱ የቋንቋ ትምህርት ይዘት ለልምምድ ሲቀርብ በቅድሚያ የሚታሰበው የትምህርቱ ዓላማ ነው፡፡ የታሰበውን የትምህርት ዓላማ ከግብ ለማድረስ ደግሞ የመለማመጃ ጥያቄዎቹ በትክክለኛ መመሪያ ታጅበው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህ አንጻር በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት መልመጃዎችና ለመልመጃዎቹ ከተሰጡት መመሪያዎች መካከል የተወሰኑትን በመውሰድ ጥንካሬያቸውንና ድክመታቸውን መመልከት ይቻላል፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ለቋንቋ ክሂሎች ልምምድ እንዲያገለግሉ ከቀረቡት ልዩ ልዩ መመሪያዎች መካከል ብዙዎቹ በጠንካራ ጎናቸው የሚጠቀሱ ናቸው። የተሟሉ መመሪያዎች ናቸው ከሚባሉት መካከል ጥቂቱን ለመጥቀስ ያህል፡-

ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 2፣ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሠረት ቡድን መስርታችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። መመሪያ 2 በውይይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ። ገጽ 8፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። ገጽ 9 - 10፣ መመሪያ 2 ..."የቋንቋ ልደትና ሞት" በሚል ርዕስ በመንስኤና ውጤት የተዋቀሩ አንቀጾችን የያዘ አንድ አጭር ጽሑፍ በንባብ ይቀርብላችኋል። በቡድን ሆናችሁ በተናጠል የመዘገባችኋቸውን በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦች ዝርዝር አስተያዩ፤ ባዳመጣችሁት መሠረት በትክክል የተወሰዱ ስለመሆናቸው ተወያዩ። በውይይታችሁ የተስማማችሁባቸውን በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦች ዝርዝር በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 20፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ የምታወቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች በየተራ ተጠያየቁ። መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ መብራሪያ ይስጥ። ገጽ 23፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ መመሪያ 2 ቀጥሎ "የስነ-ቃል ዘውጎች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ጽሑፍ መምህራችሁ አንድ ጊዜ ያነቡላችኋል። ቡድን መስርታችሁ በተናጠል የያዛችሁትን ማስታወሻ አስተያዩ። የተስማማችሁባቸውን ፍሬ ሐሳቦች የያዘ ማስታወሻ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 42፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ የውይይት መመሪያን ተከትላችሁ ተወያዩ፤ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

በአንጻሩም ለቋንቋ ክሂሎች ልምምድ እንዲሆኑ ከተሰጡት መመሪያዎች መካከል ግልጽነት የጎደላቸውና ተማሪዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገብሩት ፍንጭ የማይሰጡ መመሪያዎችም እንዳሉ ማረጋገጥ ተችሏል። የእነዚህ መመሪያዎች ትልቁ ችግራቸው ተማሪዎች በየትኛው መንገድ (በቃል ወይም በጽሑፍ)፣ (በጥንድ ወይም በቡድን) መመለስ

እንዳለባቸው በግልጽ አለመቀመጣቸው ነው። እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ ካላቸው በርካታ መመሪያዎች መካከል ማሳያ እንዲሆኑ የተወሰኑትን ለመጥቀስ ያህል፦

ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 6፣ ክፍል አንድ፦ ንባብ፣ መመሪያ 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት"፣ ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ፤ መመሪያ 3 ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ቃላት ቀርበዋል። ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሠረት ፍቻቸውን ስጡ፤ መመሪያ 4 ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት መዝገበ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ፤ የመሳሰሉት ይገኙበታል። በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል የመጀመሪያው ተማሪዎቹ በግል፣ በጥንድ ወይስ በቡድን ሆነው መሥራት እንዳለባቸው፣ እንደዚሁም ምላሾቹ የሚሰጡበት ዘዴ በቃል ይሁን በጽሑፍ በግልጽ አለመጠቀሱ ነው።

ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 23፣ ክፍል ሦስት፦ ጽሕፈት፣ መመሪያ 1 ስለ ስነ-ቃል ተግባራት ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች በማንበብ በመትከል (ማጠናከር)፣ በመግለጽና በማምለጥ ተግባራት ላይ ማስታወሻ ያዙ። የያዛችሁትን ማስታወሻ ተመርኩዛችሁ ከአንድ ገጽ ያላነሰ ማብራሪያ በጽሑፍ አቅርቡ። ገጽ 23፣ መመሪያ 3 ...ከሚከተሉት የጭውውት ተሳታፊ ገጸ-ባሕርያት መካከል አንዱን መርጣችሁ፦ ከ3 - 5 ደቂቃ የሚረዝም አንድ ጭውውት ጻፉ፤ የሚሉ ይኙበታል። በእነዚህ መመሪዎች ላይ የሚታየው ችግር ተመሳሳይ ሲሆን ይህም መልመጃዎቹ የሚሰሩት በግል፣ በጥንድ ወይም በቡድን እንደሆነ አለመገለጹ ነው።

ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 42፣ ክፍል ሁለት፦ ማዳመጥ፣ መመሪያ 2 ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቂዎች አንብባችሁ በአእምሮአችሁ በመያዝ ማብራሪያውን እያዳመጣችሁ መልሶቻችሁን ስጡ። በዚህ መመሪያ መሠረት መልሱ የሚሰጠው በቃል ይሁን ወይም በጽሑፍ ተለይቶ አልቀረበም። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

በጥያቄ ቁጥር 8፣ ለክሂል መልመጃዎቹ ተገቢ የሆነ መመሪያዎች ተሰጥተዋል፣ ተብሎ ለቀረበላቸው በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 2(20%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 2(20%)፣ "አልስማማም" ብለው የመለሱት 2(20%) ሲሆኑ ፈጽሞ አልስማማም በማለት ምላሻቸውን

ያሰፈሩት 1(10%) ናቸው። ይህ የአሃዝ መረጃ የሚያመለክተው የመመሪያዎች አቀራረብ የተለያየ መሆኑንና ተገቢና ተገቢ ያልሆኑ መመሪያዎች መኖራቸውን ነው።

በአጠቃላይ አጥኚው ለክሂል መልመጃዎቹ የቀረቡትን መመሪያዎች በመመርመር ካገኛቸው መረጃዎች እንዳረጋገጠው ጥሩ የሚባሉና በአርአያነት ሊጠቀሱ የሚችሉ መመሪያዎች መኖራቸውን ነው። በአንጻሩም ግልጽነት የጎደላቸው፣ ከተማሪዎች የሚጠበቀው ተግባር ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚከውኑት በትክክል የማይገልጹ መመሪያዎችም እንዳሉ ማየት ተችሏል። ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎችም ይህንኑ የሚያረጋግጡ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

ለአንድ የክፍል ደረጃ የሚቀርብ የትምህርት ይዘት የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ፍላጎት፣ ወዘተ. ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል። የትምህርቱ አቀራረብ የተማሪዎቹን ደረጃ፣ ዕድሜ፣ ችሎታ፣ ፍላጎት እንዲሁም ዳራዊ ጉዳዮችን ትኩረት ካላደረገ በመማር-ማስተማሩ ሂደት አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ይሆናል። በዚህ ምክንያት ከትምህርቱ የሚጠበቀው ዓላማም ግቡን ሳይመታ እንደሚቀር ይታመናል።

እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱትን የቋንቋ ክሂሎች ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ ስናጤን በአብዛኛው ታስቦባቸውና ለጉዳዮቹ ትኩረት ተሰጥቷቸው የተዘጋጁ እንደሆኑ መገንዘብ ይቻላል። ይህን ለማለት መሠረት የሆነው በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ የክሂል ይዘቶች በደራጃው ለሚገኙ ተማሪዎች እንግዳ ያልሆኑ፣ አቅማቸውን ያገናዘቡ፣ የመማር ፍላጎታቸውን የሚያነሳሱና ከተማሪዎቹ ባህላዊ ደራዎች ጋር የሚዛመዱ ይዘቶችና መልመጃዎችን ያካተቱ መሆኑ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ለቋንቋ ክሂሎች ልምምድ መነሻ እንዲሆኑ በአሥሩም ምዕራፎች ውስጥ የቀረቡት ምንባቦች በሁሉም ዘንድ በሚታወቁና ሁሉንም ተማሪዎች ሊያጋሩ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ በመሆናቸውና የክሂል መልመጃዎችም እነዚህን ምንባቦች ተመሥርተው በመዘጋጀታቸው ነው።

ለዚህም ማሳያ እንዲሆን የተወሰኑ ይዘቶችን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ምዕራፍ አንድ፣ "ቋንቋና ህብረተሰብ"፣ ገጽ 8፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1፣ ጥያቄ 1 ዘዬዎች እንዴት ይፈጠራሉ? 2. በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚኖር የዘዬ ልዩነት መግባባትን አያግድም ሚባለው ለምንድነው?፣

ምዕራፍ ሁለት፣ "ስነ-ቃል"፣ ገጽ 20፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1. በጥንድ ሆናችሁ የምታውቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች በየተራ ተጠያየቁ። መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ፣ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ማብራሪያ ስጡ፤

ምዕራፍ ሦስት፣ "ቤተ-መጻሕፍትና ስነ-ጽሑፍ"፣ ገጽ 44፣ ክፍል አራት፡-ጽሕፈት፣ መመሪያ 1. ከዚህ በታች ስለአንቀጽ ምንነት የቀረበውን ማስረጃ በማንበብና የተሰጠውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡት ርዕሰ-ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ (ማርፈድ፣ ከትምህርት ቤት መቅረት፣ የጥናት መርሐ-ግብር)፤

ምዕራፍ አራት፣ "ልቦለድ"፣ ገጽ 62፣ ክፍል ሁለት፡- ማዳመጥ፣ መመሪያ 2 መምህራችሁ አንድ አጭር ጽሑፍ ያነቡላችኋል። በጥሞና አዳምጡና በ"ሀ" ስር የተገለጹትን ገለጻዎች በ"ለ" ስር ከተዘረዘሩት ተገላጮች ጋር አዛምዱ፤

ምዕራፍ አምስት፣ "ሥነ-ግጥም"፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ ገጽ 85፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የቀረቡ ገለጻዎችን፣ ማብራሪያዎችን ወይም ጥያቄና መልሶችን ተከታትላችሁ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፣ ...የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*ሠንጠረዥ 7፣ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎቹ የተማሪዎችን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ያገናዘቡ ስለመሆናቸው*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎቹ ለደረጃው ተማሪዎች የሚመጥኑ ናቸው። | 5 (50%) | 4 (40%) | 1 (10%) | - | - |
| 12 | የክሂል መልመጃዎቹ ከተማሪዎቹ እድሜ፣ ችሎታና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ ናቸው። | 4 (40%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 1 (10%) | - |
| 13 | የክሂል መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ዳራዊ ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ናቸው። | 3 (30%) | 4 (40%) | 1 (10%) | 1 (10%) | 1 (10%) |

በጥያቄ ቁጥር 11፣ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎቹ ለደረጃው ተማሪዎች የሚመጥኑ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 5(50%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 4(40%) ሲሆኑ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ የመለሱት 1(10%) ናቸው። ይህ መረጃ የክሂል ይዘቶቹና መልመጃዎቹ ለደረጃው ተማሪዎች የሚመጥኑ መሆናቸውን ያመለክታል።

በጥያቄ ቁጥር 12፣ የክሂል መልመጃዎቹ ከተማሪዎቹ እድሜ፣ ችሎታና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፣ ተብሎ ለተጠየቁት ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" በማለት ምላሻቸውን ያሰፈሩት 3(30%) "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት 2(20%) ሲሆኑ "አልስማማም" በማለት የመለሱት ደግሞ 1(10%) ናቸው። ከዚህ የአሃዝ መረጃው መገንዘብ የሚቻለው የክሂል መልመጃዎቹ ከተማሪዎቹ እድሜ፣ ችሎታና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸውን ነው።

እንዲሁም በጥያቄ ቁጥር 13፣ የክሂል መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ዳራዊ ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ናቸው፣ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት የገለጹት 1(10%)፣ "አልስማማም" ሲሉ የመለሱት 1(10%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን ያሰፈሩት 1(10%) ናቸው። ከዚህ የአሃዝ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የክሂል መልመጃዎቹ የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ መሆናቸውን ነው።

በአጠቃላይ አጥኚው በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ፍተሻ ማስተዋል እንደቻለው እንዲሁም በመምህራን የተሞሉ የጽሑፍ መጠይቆች እንደሚያመለክቱት፣ ከላይ ከተጠቀሱት ነጥቦች አንጻር የሚታዩ ጉልህ ችግሮች አለመኖራቸውን ነው። በሌላ አገላለጽ ለቋንቋ ልምምድ የቀረቡት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች የተማሪዎችን ደረጃ ያገናዘቡ፣ ፍላጎታቸውን መሠረት ያደረጉና ዳራዊ ጉዳዮችን ትኩረት ያደረጉ ናቸው።

የክሂል መልመጃዎቹ በመምህራንና በተማሪዎች ተግባራዊ የመደረግ ሁኔታ ሲል ይዘቶቹ ከደረጃው ተማሪዎች አቅም በላይ ያለመሆናቸውንና በሚታወቁ ጉዳዮች ላይ ማተኮራቸውን የሚመለከት ነው። ከዚህ አንፃር ለቋንቋ ክሂሎች ልምምድ እንዲረዱ የተዘጋጁት መልመጃዎች በመምህራንና በተማሪዎች ተግባራዊ ከመደረጋቸው አንጻር የጎላ ችግር የሌለባቸው መሆናቸውን ከጽሑፍ መጠይቆች ከተገኙ መረጃዎች አረጋግጠዋል። ይህ የሆነበት ምክንያት ቀደም ሲል እንደተገለጸው ለቋንቋ ልምምድ መነሻ እንዲሆኑ የተመረጡት ጽሑፎች በሚታወቁ ነገሮች ላይ ያተከሩ በመሆናቸውና መልመጃዎችም እነዚህን ጽሑፎች ተንተርተሰው በመቀረጻቸው ነው። በመሆኑም መልመጃዎቹ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች የማያስቸግሩና የተግባራዊነት ችግር የሌለባቸው መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*ሠንጠረዥ 8፣ የክሂል መልመጃዎቹ ተግባራዊ፣ ግልጽና የተለመዱ ዓይነት ስለመሆናቸው*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 14 | የክሂል መልመጃዎቹ በመምህራንና በተማሪዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው። | 4 (40%) | 5 (50%) | - | - | 1 (10%) |
| 15 | በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የክሂል ይዘቶች በሙሉ መምህሩ እንዲያስተምር፣ ተማሪውም እንዲማር በሚያስችል መልኩ በግልጽ ቋንቋ ቀርበዋል። | 4 (40%) | 4 (40% | 1 (10%) | - | 1 (10%) |
| 16 | ተማሪው እንዲማረውና እንዲለማመደው የቀረበው የቋንቋ አካል (ይዘት) በቋንቋው ተናጋሪ ኅብረተሰብ ዘንድ የተለመደ ነው። | 3 (30%) | 4 (40%) | 2 (20%) | - | 1 (10%) |
| 31 | በክሂል መልመጃዎቹ ላይ የቀረቡ ይዘቶች ከተማሪዎቹ አካባቢያዊና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው። | 3 (30%) | 4 (40%) | 2 (20%) | 1 (10%) | - |

በጥያቄ ቁጥር 14፣ የክሂል መልመጃዎቹ በመምህራንና በተማሪዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 5(50%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን ያሰፈሩት 1(10%) ናቸው። ይህ የአሃዝ መረጃ የሚያመለክተው መልመጃዎቹ በተማሪዎችና በመምህራን ተግባራዊ ከመደረጋቸው አኳያ በጣም ጥሩ የሚባሉ መሆናቸውን ነው።

በሌላ በኩል በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች መምህሩ እንዲያስተምር፣ ተማሪውም እንዲማር ከማስቻልና ከቋንቋ ግልጽነት አንጻር ሲቃኙ አሻሚነት የሌላቸው፣ በግልጽ ቋንቋና በተለመዱ የአገላለጽ ስልቶች የቀረቡ ናቸው። የክሂል መልመጃዎቹ የተገነቡበትን ሁኔታ ስንመለከት ከግልጽነት ጉድለት የተነሳ የመማር-ማስተማሩን ሂደት የሚያደናቅፉ ያለመሆናቸውን ለመረዳት ተችሏል።

በቁጥር 15፣ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የክሂል ይዘቶች በሙሉ መምህሩ እንዲያስተምር፣ ተማሪውም እንዲማር በሚያስችል መልኩ በግልጽ ቋንቋ ቀርበዋል፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደተቻለው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 4(40%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 1(10%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ብለው የሞሉት 1(10%) ናቸው። ይህ የአሃዝ መረጃ የሚያሳየው የክሂል መልመጃዎቹ በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች ተግባራዊ ከመደረግና ከቋንቋ ግልጽነት አንጻር ጥሩ መሆናቸውን ነው።

የደረጃው ተማሪዎች እንዲማሩባቸውና ቋንቋውን እንዲለማመዱባቸው የቀረቡት የቋንቋ ይዘቶች በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ዘንድ የተለመዱና መደበኛ መሆን እንዳለባቸው ይታመናል። ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋን እንዲማሩበት የተዘጋጀው መጽሐፍ በውስጡ የያዛቸው የክሂል ይዘቶች ሲቃኙ ጉዳዩን አስቀድመው ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባት የተዘጋጁ ይመስላሉ። ምክንያቱም ከክሂል መልመጃዎች መካከል በቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ ዘንድ ያልተለመዱና እንግዳ የሆኑ አገላለጾችም ሆኑ የአጠያየቅ ስልቶች በመጽሐፉ ውስጥ የማይገኙ በመሆናቸው ነው።

ይህን አስመልክቶ ከመጽሐፉ ተጠቃሚ መምህራን መረጃ ለማግኘት በጥያቄ ቁጥር 16፣ ተማሪው እንዲማረውና እንዲለማመደው የቀረበው የቋንቋ አካል (ይዘት) በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ዘንድ የተለመደ ነው፣ ተብሎ ለተነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ የመለሱት 2(20%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 1(10%) ናቸው። ይህ መረጃ የሚያሳየው የክሂል መልመጃዎች የቀረቡበት ቋንቋ እንግዳ ያልሆንና በተናጋሪ ህብረተሰብ ዘንድ የተለመደ መሆኑን ነው።

ለክሂሎች ልምምድ በቀረቡት ጥያቄዎች ውስጥ የሚንጸባረቁ ጉዳዮች የተማሪውን አካባቢያዊና ባህላዊ ዳራዎች ከትኩረት ያስገቡ ሊሆኑ እንደሚገባቸው ይታመናል። በዚህ ረገድ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱ የክሂል መልመጃዎች የያዟቸው ነጥቦች ለአብዛኞቹ ተማሪዎች አዲስ ያልሆኑና የጋራ የሚሆኑ ጉዳዮች መሆናቸውን መመልከት ይቻላል። ለዚህ ማሳያ እንዲሆን የተወሰኑትን መጥቀስ ተገቢ ይሆናል። በመጽሐፉ ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 24፣ መመሪያ 4፣ ጥያቄ ቁጥር 1. በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ ባህላዊ ምግቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ፤ ምዕራፍ አራት፣ ገጽ 62፣ መመሪያ 1፣ ጥያቄ ቁጥር 1. ፊት ለፊት ከሚደረግ የሐሳብ ልውውጥና በስልክ ከሚደረግ ንግግር በቀላሉ አዳምጦ ለመረዳት የሚያስችለው የትኛው ነው? ለምን? የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ የሆኑ የጋራ ጉዳዮችን የያዙ ጥያቄዎች ይገኙበታል።

ይህን በሚመለከት በጥያቄ ቁጥር 31 በክሂል መልመጃዎቹ ላይ የቀረቡት ይዘቶች ከተማሪዎቹ አካባቢያዊና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን በቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ የገለጹት 2(20%)

ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 1(10%) ናቸው። ይህ አሃዝ የሚያስረዳው በክሂል መልመጃዎቹ ላይ የተነሱ ጉዳዮች በአብዛኛው አካባቢያዊና ባህላዊ ነገሮችን የሚዳስሱ መሆናቸውን ነው።

በአጠቃላይ አጥኚው የመማሪያ መጽሐፉን በተመለከተበት ወቅት እንዳስተዋለው፣ እንዲሁም ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቆች ያገኛቸው መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቀረቡበት ሁኔታ የሚበረታታ መሆኑን ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት የክሂል መልመጃዎቹ በቋንቋው ተናጋሪ ህብረተሰብ ዘንድ በተለመደውና ግልጽ በሆነ ቋንቋ በመቅረባቸውና የተማሪዎችን አካባቢያዊና ባህላዊ ጉዳዮችን ከግንዛቤ ውስጥ በማስገባታቸው ነው። በመሆኑም በቋንቋ ልምምድ ወቅት መልመጃዎቹ በመምህሩም ሆነ በተማሪዎች ያለ ምንም ችግር ተግባራዊ እንዲያደርጉ እንደሚያስችላቸው መረዳት ይቻላል።

ለቋንቋ ትምህርት መለማመጃ እንዲሆኑ የሚቀረጹት ጥያቄዎች ዓቢይ ዓላማቸው ተማሪዎች በአራቱም የቋንቋ ክሂል ዘርፎች በቂ ዕውቀትን ቀስመው በአስፈላጊው ጊዜና ቦታ በተገቢ መልኩ መገልገል እንዲችሉ ለማድረግ ነው። ይህ ስኬታማ የሚሆነው ደግሞ የመልመጃ ጥያቄዎቹ ተሟልተውና ለክሂሎች ልምምድ አመቺ ሆነው ሲዘጋጁ ነው። ከዚህ የመልመጃ ጥያቄዎቹ ተሟልተውና ለክሂሎች ልምምድ አመቺ ሆነው ሲዘጋጁ ነው። ከዚህ አንጻር በመጽሐፉ ውስጥ ለአራቱም ክሂሎች የቀረቡትን የመልመጃ ጥያቄዎች ከተወሰኑ ማሳያዎቻቸው ጋር እንደሚከተለው ማሳየት ተገቢ ይሆናል።

ለንባብ ክሂል መልመጃ እንዲሆኑ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች መሠረት ያደረጉ ናቸው። የጥያቄዎቹም ባሕርይ ሲጤን ተማሪዎቹ ካነበቡት ምንባብ በመነሳት ቃል በቃል፣ "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት፣ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛውን ምላሽ በመምረጥ፣ ወዘተ. የሚመለሱ ናቸው። ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 6፣ ክፍል አንድ፣ መመሪያ 1. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፤

1. ዘዬ ምንድነው?
2. የሰው ልጅ ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ የሚለየው በምንድነው?
3. ቋንቋ እንዴት እንደሚያድግ በምሳሌ አስረዱ።

መመሪያ 2. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ።

1. ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው። ማንኛውም ቋንቋ ደግሞ እስካግባባ ድረስ ቋንቋ ነው።

2. ቋንቋ በሥርዓት የሚሰደሩ ድምጾች ስብስብ ነው።

3. አንድ ቋንቋ "ሞተ" የሚባለው በተናጋሪዎቹ ላይ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስ ነው።

የእነዚህ ዓይነቶቹ መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙ ምዕራፎች ውስጥ በብዛት ይገኛሉ። ጥያቄዎቹ ትክክለኛ ምላሽ እንዲያገኙ ከተፈለገ ምንባቡ አስቀድሞ መነበብ ይኖርበታል፤ በዚህም ሂደት ተማሪዎቹ የንባብ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ያግዛቸዋል ማለት ነው /አባሪ አራትን ይመልከቱ/።

ለንግግር ክሂል ልምምድ እንዲውሉ ከተዘጋጁት መልመጃዎች መካከልም የተወሰኑትን በማሳያነት መመልከት ይቻላል። ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 8፣ ክፍል ሁለት፣ መመሪያ 1. በጥንድ ሆናችሁ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፤

1. ዘዬዎች እንዴት ይፈጠራሉ?

2. በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚኖር የዘዬ ልዩነት መግባባትን አያግድም የሚባለው ለምንድነው?

መመሪያ 2. የሚከተሉት ሐረጎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው። ያያዙትን መልዕክት በራሳችሁ አባባል አብራሩ፤

1. ማኅበራዊና ባህላዊ እድገት

2. ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ

3. የቋንቋ ማኅበራዊ አገልግሎት

በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙ አሥሩም ምዕራፎች ውስጥ እነዚህና ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸው ጥያቄዎች ይገኙበታል። የጥያቄዎቹን አቀራረጽ ስንመለከት በቃል ወይም በንግግር የሚመለሱ ናቸው። ተማሪዎቹ ለእነዚህና መሰል ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት አስቀድመው

በጥንድና በቡድን በመሆን መነጋገርና መወያየት ይጠበቅባቸዋል። ይህን በሚያከናውኑበት ወቅት ደግሞ የንግግር ክሂላቸውን ያሳድጋሉ /አባሪ አራትን ይመልከቱ/።

ለማዳመጥ ክሂል እንዲያገለግሉ የተቀረጹ መልመጃዎችን ለአብነት ያህል ስንመለከት ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 8፣ ክፍል ሦስት፣ መመሪያ 1. መምህራችሁ "መደበኛና ኢ-መደበኛ ቋንቋ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፤

1. አዳምጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ ላይ መዝግቡ።
2. በጥንድ ከሆናችሁ በኋላ በያዛችሁት ማስታወሻ በመታገዝ የጽሑፉን መልዕክት በራሳችሁ አባባል አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተናገሩ።

መመሪያ 2. "የቋንቋ ልደትና ሞት" በሚል ርዕስ በመንስኤና ውጤት የተዋቀሩ አንቀጾችን የያዘ አንድ አጭር ጽሑፍ በንባብ ይቀርብላችኋል።

1. እያዳመጣችሁ በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦችን ብቻ ለይታችሁ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ።
2. በቡድን ሆናችሁ በተናጠል የመዘገባችኋችውን በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦች ዝርዝር አስተያዩ፤ ባዳመጣችሁት መሠረት በትክክል የተወሰዱ ስለመሆናቸው ተወያዩ።
3. በውይይታችሁ የተስማማችሁባቸውን በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦች ዝርዝር በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

እንደነዚህ ያሉ የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ በጥቂት ምዕራፎች ውስጥ ብቻ ይገኛሉ። ከሌሎች የክሂል ዓይነቶች አንጻር ሲታይ የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች ቁጥራቸው ውስን ቢሆንም በባሕርያቸው ግን ጥያቄዎቹ ከተደመጡት ጉደዮች ተነስተው የሚመለሱ ናቸው። ተማሪዎች ጥያቄዎቹን ለመመለስ ሲሉ ያዳምጣሉ፤ በእነዚህና መሰል ሂደቶች የተማሪዎቹ የማዳመጥ ክሂል ይዳብራል /አባሪ አራትን ይመልከቱ/።

የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች ቀደም ሲል በማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች ውስጥ እንደተመለከትናቸው ከሌሎች ክሂሎች ጋር በውህደት የቀረቡ ሲሆኑ ሌሎች ተጨማሪ መልመጃዎችን እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል። ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 11፣ ክፍል አራት ላይ በዚህ ምዕራፍ በቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ላይ የተደረገውን ውይይት በድጋሚ አንብባችሁ

በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦችን በሚከተለው ሠንጠረዥ አስፍሩ፡፡

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ምሳሌ፣ ቋንቋ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ ተናጋሪ ሲያጣ | እሱም አብሮ ይጠፋል |
| ............... ............... ............... ............... | ............... ............... |
| ............... ............... ............... ............... | ............... ............... |

እንደነዚህ ያሉ መልመጃዎች በጽሑፍ የሚመለሱ ናቸው፡፡ ተማሪዎቹም ምላሻቸውን በጽሑፍ በሚሰጡበት ጊዜ የጽሕፈት ክሂላቸውን ያዳብራሉ ማለት ነው /አባሪ አራትን ይመልከቱ/፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 9፣ የክሂል መልመጃዎቹ የትምህርቱን ዓላማ ለማሳካት ያላቸውን ብቃት*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | ለእያንዳንዱ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃት አላቸው፡፡ | 2 (20%) | 3 (30%) | 5 (50%) | - | - |
| 18 | የክሂል ይዘቶቹ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ የማድረግ አቅም ያላቸው ናቸው፡፡ | 4 (40%) | 3 (30% | 2 (20%) | 1 (10%) | - |

በጥያቄ ቁጥር 17፣ ለእያንዳንዱ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃት አላቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 2(20%)፣ "እስማማለሁ" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 3(30%) ሲሆኑ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ የመለሱት 5(50%) ናቸው፡፡ የአሃዝ መረጃው በከፊል የሚያመለክተው መልመጃዎቹ የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት አቅም ያላቸው መሆናቸውን ሲሆን በከፊል ደግሞ መጠይቁን የሞሉ መምህራን መወሰን እንዳቃታቸው ነው፡፡ መጠይቁን ከሞሉት መምህራን መካከል ከፊል የሚሆኑት ለመወሰን የመቸገራቸው ምክንያት መጽሐፉ አዲስ በመሆኑና አይተውት ባለመጨረሳቸው እንደሆነ ከሰጡት ምላሽ መገንዘብ ተችሏል፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን በጥያቄ ቁጥር 18፣ የክሂል ይዘቶቹ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ የማድረግ አቅም ያላቸው ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 3(30%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት የመለሱት 2(20%) ሲሆኑ "አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን ያስፈሩት 1(10%) ናቸው። ይህ አሃዝ የሚያመለክተው የክሂል ይዘቶቹ ለተማሪዎቹ ቋንቋ ማደግ ጉልህ አስተዋጽኦ ያላቸው መሆናቸውን ነው።

በአጠቃላይ ለአራቱም የቋንቋ ክሂሎች ማሳኪያ በመሆን እንዲያገለግሉ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች በየክሂል ርዕሶቹ ስር ያላቸው መጠን የተለያየ ቢሆንም ፋይዳቸው ግን እጅግ የላቀ ነው። የመልመጃ ጥያቄዎቹ የቀረቡበትን ክሂል ዓላማ የማሳከት አቅም ያላቸውና የተማሪዎችን የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ የማዳበር ብቃት የተላበሱ መሆናቸውን መገንዘብ ተችሏል።

የማዳመጥን ክሂል ለማስተማር የሚረዱ በርካታ ዘዴዎች መኖራቸውን በምዕራፍ ሁለት በዝርዝር ለማሳየት ተሞክሯል። ከእነዚህም መካከል ቴፕ፣ ቴሌቭዥን፣ የሰዎች ንግግር፣ የስልክ ንግግሮች፣ ወዘተ. ይጠቀሳሉ። የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ ርዕስ ተሰጥቷቸው የቀረበቡበትን መጠን ስንመለከት ከአሥሩ ምዕራፎች መካከል በሦስት ምዕራፎች ብቻ መሆኑ ቀደም ሲል ተጠቁሟል። በእነዚህ ሦስቱ ምዕራፎች ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች የቀረቡባቸውን ዘዴዎች የተወሰኑ ማሳያዎችን በማንሳት እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፤

ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 8፣ ክፍል ሦስት፡- ማዳመጥ፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ "መደበኛና ኢ-መደበኛ ቋንቋ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፤ እንዲሁም መመሪያ 2 "... በኋላ 'የቋንቋ ልደትና ሞት' በሚል ርዕስ በመንስኤና ውጤት የተዋቀሩ አንቀጾችን የያዘ አንድ አጭር ጽሑፍ በንባብ ይቀርብላችኋል። ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 23፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ መመሪያ 2 ቀጥሎ "የስነ-ቃል ዘውጎች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ጽሑፍ መምህራችሁ አንድ ጊዜ ያነቡላችኋል። እያዳመጣችሁ ...። ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 42፣ ክፍል ሁለት፡- ማዳመጥ፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ "ደራሲና የህይወት ልምዱ" በሚል ርዕስ አንድ ማብራሪያ ሁለት ጊዜ የነቡላችኋል ..."።

እነዚህን የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች ስንመለከታቸው ትዕዛዞቹ በአብዛኛው ተማሪዎቹ መምህራቸው የሚያነቧቸውን ምንባቦች መሠረት በማድረግ የተለያዩ ጥያቄዎችን እንዲመልሱ የሚያዙ ናቸው፡፡ በአንጻሩም በመጽሐፉ ውስጥ ተማሪዎች ከሬዲዮ፣ ከቴፕ፣ ከቴሌቪዥን፣ ከሰዎች ንግግር፣ ወዘተ. አዳምጠው ልዩ ልዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚታዘዙበት ሁኔታ በሚመለከት ያሉትን መልመጃዎች ቀጥለን እናንሳ፡፡

ምዕራፍ አራት፣ ገጽ 63፣ ክፍል ሦስት፦ ንግግር፣ መመሪያ 1 ከልቦለድ ወይም ከሌሎች የፈጠራ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ውይይቶችን፣ የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ወዘተ. ከሬዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን አዳምጣችሁ "ጠቃሚ ሐሳብ ነው" የምትሉትን በራሳችሁ አባባል ጽፋችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡ ምዕራፍ አምስት፣ ክፍል ሁለት፦ ንግግር፣ ገጽ 85፣ ጥያቄ ቁጥር 1 መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መመሪያ መሠረት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የቀረቡ ገለጻዎችን፣ ማብራሪያዎችን ወይም ጥያቄና መልሶችን ተከታትላችሁ ማስታወሻ በመያዝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡ ምዕራፍ ስምንት፣ ክፍል ሦስት፦ ንግግር፣ መመሪያ 2 ከመገናኛ አውታሮች ባገኛችኋቸው ወቅታዊ ጉዳዮች (ኤች አይ ቪ፣ ሙስና፣ የጾታ እኩልነት፣ ወዘተ.) ላይ በቡድን ሆናችሁ ተወያዩ፤ የሚሉ መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ በሦስት ምዕራፎች ውስጥ ይገኙበታል፡፡

በእነዚህ ሦስት ምዕራፎች ውስጥ የቀረቡት የማዳመጥ ክሂል መስተማሪያ ብልሃቶች ሬዲዮን፣ ቴሌቪዥንና ሌሎች የመገናኛ አውታሮችን የሚመለከቱ ናቸው፡፡ ስለሆነም መጽሐፉ ከእነዚህ በተጨማሪ በእንግዳ ሰው የሚቀርቡ ንግግሮችንና በቴፕ የተቀረጹ ቃለ-ምልልሶችን ለመሳሰሉ ለሌሎች የማዳመጥ ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ምንም ትኩረት እንዳልሰጠ መገንዘብ ይቻላል፡፡ ቀጥለን ደግሞ ተማሪዎች በልዩ ልዩ የውይይት መድረኮች ተገኝተው ንግግሮችን በማዳመጥ የተለያዩ ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚያዙ መልመጃዎችን እንመለከታለን፤

ምዕራፍ ሰባት፣ ገጽ 127፣ ክፍል ሦስት፦ ንግግር፣ መመሪያ 1 የአካባቢ እንክብካቤን አለዚያም ሌሎች አካባቢያዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚደረጉ ውይይቶችን፣ ማብራሪያዎችንና ገለጻዎችን አዳምጣችሁ ማስታወሻ በመያዝ በራሳችሁ አባባል በጽሑፍ አዘጋጁ፤ የሚል ይገኝበታል፡፡ የዚህ ዓይነቱ መልመጃ በመጽሐፉ ውስጥ ተደጋግሞ የቀረበበት ሁኔታ አይታይም፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ሠንጠረዥ 10፣ የክሂል መልመጃዎቹ በተገቢ የማስተማሪያ ብልሃቶች ስለመታገዛቸው

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 24 | የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተደግፈዋል (ለምሳሌ በቴፕ፣ በቴሌቭዥን፣ በሰዎች ንግግር፣ ወዘተ.)። | 1 (10%) | 1 (10%) | - | 3 (30%) | 5 (50%) |
| 25 | የንግግር ክሂል መልመጃዎች የተለያዩ ስልቶችን ተከትለው ተዘጋጅተዋል (ለምሳሌ ውይይት፣ ጭውውት፣ ክርክር፣ ቃላዊ ሪፖርት፣ ወዘተ.)። | 4 (40%) | 5 (50%) | 1 (10%) | - | - |
| 26 | የንባብ ክሂል መልመጃዎች ለክሂሉ ማስተማሪያ የሚሆኑ ብልሃቶችን መሠረት ያደረጉ ናቸው (ለምሳሌ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ አንደምታና ትንበያ)። | 3 (30%) | 1 (10%) | - | 4 (40%) | 2 (20%) |
| 27 | የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ ውጤታዊና ሂደታዊ የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው። | 1 (10%) | 3 (30%) | 4 (40%) | 2 (20%) | - |
| 28 | የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ በቁጥጥር ጽሕፈት /controlled writing/፣ በመር ጽሕፈት /guided writing/ እና በነፃ ጽሕፈት /free writing/ ስልት ተለይተው ቀርበዋል። | 1 (10%) | 1 (10%) | 3 (30%) | 2 (20%) | 3 (30%) |
| 29 | የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በወረቀት ላይ በማስፈር መግባባት እንዲችሉ የሚያደርጉ ናቸው። | 4 (40%) | 4 (40%) | - | 2 (20%) | - |

በጥያቄ ቁጥር 24፣ የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተደግፈዋል (ለምሳሌ በቴፕ፣ በቴሌቭዥን፣ በሰዎች ንግግር፣ ወዘተ.)፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 2(20%)፣ "እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 2(20%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት ምላሻቸውን ያስፈሩት 1(10%) "አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 3(30%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ያሉት 2(20%) ናቸው። ይህ መረጃ የሚገልጸው የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች በበቂ ሁኔታ ያልተደገፉ መሆናቸውን ነው።

የንግግርን ክሂል ለማስተማር የሚረዱ ልዩ ልዩ ዘዴዎች እንዳሉና ዘዴዎቹም ምን ምን እንደሆኑ ቀደም ባለው ክፍል ተመልክቷል። ለማስታወስ ያህል ውይይት፣ ጭውውት፣ ክርክር፣ ቃላዊ ሪፖርት፣ ወዘተ. መጥቀስ ይቻላል። የንግግር ክሂል በመጽሐፉ ውስጥ ሰፊ ሽፋን ከተሰጣቸው ይዘቶች አንዱ ሲሆን ክሂሉ ለልምምድ የቀረበባቸውን ዘዴዎች የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማንሳት ማሳየት ይቻላል።

ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 8፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 20፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ የምታውቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች ተጠያየቁ። መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ማብራሪያ ይስጥ። ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 42፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ መወያያ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ የውይይት መመሪያን ተከትላችሁ ተወያዩ። ገጽ 44፣ መመሪያ 2 ባለፈው ሳምንት ያሳለፋችሁትን የእሁድ ቀን ውሎ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን ጠብቃችሁ ከ3 - 5 ደቂቃ የሚረዝም ንግግር አድርጉ። ምዕራፍ አራት፣ ገጽ 63፣ መመሪያ 2 በአጭር ልቦለዱ እንደታየው በሁለቱ ዋና ገጸባሕርያት መካከል ከፍተኛ ያለመግባባት ተፈጥሯል። ስለዚህ ተጠያቂው ማነው? ዘነበ ወይስ በልዩ? አንደኛውን ደግፋችሁ ሌላኛውን በመቃወም ተከራከሩ። ምዕራፍ አምስት፣ ገጽ 84፣ መመሪያ 2 የመረጣችሁትን አንድ ግጥም ወይም ዝርው ጽሑፍ አጥንታችሁ በቃል ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፤ መልዕክቱንም ተናገሩ። ምዕራፍ ሰባት፣ ገጽ 127፣ መመሪያ 3 በክፍላችሁ ውስጥ እንደ ፍላጎታችሁ በጥንድ በጥንድ ተሰባሰቡና በመረጣችሁት ጉዳይ ላይ ጭውውት አድርጉ። ምዕራፍ አሥር፣ ገጽ 175፣ ክፍል ሦስት፣ መመሪያ 1 በምንባቡ ውስጥ ያሉ ገጸባሕርያትን ወክላችሁ ተሟገቱ፤ የሚሉና ሌሎችም ይገኙበታል።

እነዚህን መልመጃዎች ስንመለከታቸው ልዩ ልዩ የንግግር ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን የተከተሉ ናቸው። ከመልመጃዎቹ ትዕዛዞች ባሕርይ አኳያ መረዳት የሚቻለው ውይይት፣ ቃላዊ ሪፖርት፣ ክርክር፣ ጭውውት፣ ሙግት፣ እና የመሳሰሉት አገልግሎት ላይ መዋላቸውን ነው።

ይህ በሚመለከት በጥያቄ ቁጥር 25፣ የንግግር ክሂል መልመጃዎች የተለያዩ ስልቶችን ተከትለው ተዘጋጅተዋል (ለምሳሌ ጭውውት፣ ክርክር፣ ቃላዊ ሪፖርት፣ ወዘተ.)፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ብለው የመለሱት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 5(50%) ሲሆኑ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ ምላሻቸውን ያሰፈሩት 1(10%) ናቸው። የአሃዝ መረጃው የሚያመለክተው በመጽሐፉ ውስጥ የንግግር ክሂልን ለማስተማር የሚስችሉ በቂና የተለያዩ ዘዴዎች ጥቅም ላይ መዋላቸውን ነው።

የንባብ ክሂልን ለማስተማር የሚዘጋጁ መልመጃዎች ለክሂሉ የሚሆኑ የማስተማሪያ ብልሃቶችን መሠረት ያደረጉ መሆን እንዳለባቸው በርካታ ምሁራን ይስማሙበታል፡፡ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶችን በሚመለከት በምዕራፍ ሁለት ላይ በዝርዝር የተመለከተ ሲሆን ለማስታወስ ያህል ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ አንድምታና ትንበያ የሚሉ ይገኙበታል፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ የንባብ ክሂልን ለማስተማር ታስበው የቀረቡት መልመጃዎች የቀረቡበትን ስልት ለማሳየት የተወሰኑትን ምሳሌዎች እንደሚከተለው መጥቀስ ተገቢ ነው፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ አሥሩም ምዕራፎች በመጀመሪያ ክፍላቸው የያዙት ርዕስ "ንባብ" የሚል ሲሆን በእነዚህ ርዕሶች ስር የቀረቡት መልመጃዎችም ተማሪዎች ካነበቧቸው ምንባቦች በመነሳት የሚመልሷቸው ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአብዛኛው የጽሕፈት ክሂል ርዕስ ስር የቀረቡት አብዛኞቹ መልመጃዎችም ቢሆኑ ምንባቦችንና ልዩ ልዩ ጽሑፎችን ተንተርሰው የሚመለሱ ናቸው፡፡ ስለሆነም ጥያቄዎቹ የተማሪዎችን የንባብ ክሂል ከማሳደግ አኳያ ጉልህ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡

የንባብን ክሂል ማስተማሪያ ከሆኑ ብልሃቶች መካከል አንዱ "ጥያቄ መጠየቅ" ነው፡፡ ይህ ብልሃት በመጽሐፉ ውስጥ በብዛት በጥቅም ላይ መዋሉን ማስተዋል ተችሏል፡፡ ለምሳሌ ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 6 - 7፣ ክፍል አንድ፣ መመሪያ 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልሱ፡-

1. ዘዬ ምንድነው?
2. የሰው ልጅ ቋንቋ ከእስሳት መግባቢያ የሚለየው በምንድነው?
3. ቋንቋ እንዴት እንደሚያድግ በምሳሌ አስረዱ፡፡

መመሪያ 2 የሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ፤

1. ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው፡፡ ማንኛውም ድምጽ ደግሞ እስካግባባ ድረስ ቋንቋ ነው፡፡
2. ቋንቋ በሥርዓት የሚሰደሩ ድምጾች ስብስብ ነው፡፡
3. አንድ ቋንቋ "ሞተ" የሚባለው በተናጋሪዎቹ ላይ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲደርስ ነው፡፡

የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይ ጥያቄዎች ይገኙባቸዋል፡፡ የእንደነዚህ ዓይነቶቹ የአጠያየቅ ስልቶች የተለመዱና በሁሉም ምዕራፎች ስር የሚገኙ ናቸው፡፡

ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች መካከል ሁለተኛው "ማብራራትና መተርጎም" የሚለው ነው፡፡ ይህ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃት በመጽሐፉ ውስጥ በጥቂት ምዕራፎች ብቻ ተግባራዊ መሆኑ ተመልክቷል፡፡ እነዚህም፡- ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 8፣ ክፍል ሁለት፣ መመሪያ 2 የሚከተሉት ሐረጎች ከምንባቡ የወጡ ኛቸው፡፡ የያዙትን መልዕክት በራሳችሁ አባባል አብራሩ፤

1. ማኅበራዊና ባህላዊ እድገት
2. ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ
3. የቋንቋ ማኅበራዊ አገልግሎት

ምዕራፍ ሰባት፣ ገጽ 124፣ ክፍል ሁለት፣ መመሪያ 3 የሚከተሉትን ከምንባቡ የወጡ አባባሎች በራሳችሁ አባባል እንደገና ጻፉ፤

1. ማንኛውም የቆሻሻ ዓይነት እኛንና አካባቢን ሊጎዳ ይችላል፡፡
2. ሁላችንም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ቆሻሻ ስለምንፈጥር...
3. አነስተኛ ቦታ እንዲይዝ አድርጎ ማጨቅና ጉዳቱ እንዲቀንስ ማጣራት

ምዕራፍ ዘጠኝ፣ ገጽ 151፣ ክፍል አንድ፣ መመሪያ 3 ለሚከተሉት ቃላት ወይም ሐረጎች በምንባቡ ውስጥ ያያዙትን ፍች በተብራራ መንገድ ስጡ፡-

1. የንግግር ጥበብ
2. የተገራ አንደበት
3. የታረመ አንደበት
4. እንደበተ-ርቱእ
5. መንፈስ ማበልጸግ
6. ምላስ ማስላት

የሚሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ጥያቄዎች በቁጥር ውስን ቢሆኑም በባሕርያቸው ግን ተማሪዎች ካነበቧቸው ምንባቦች ተነስተው የተለያዩ አባባሎችን በራሳቸው አገላለጽ እንዲያብራሩና እንዲተረጉሙ የሚያበረታቱ ናቸው፡፡

ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች መካከል ሦስተኛው "ማጠቃለል" የሚለው ነው፡፡ በመጽሐፉ ውስጥ ግን ተማሪዎች ያነበቧቸውን ምንባቦች ወይም ጽሑፎች አስመልክተው ማጠቃለያ እንዲሰጡ ሲያዝ አንድም ቦታ ላይ አልተመለከተም፡፡ ነገር ግን ያነበቡትን ጽሑፍ አሳጥረው እንዲጽፉ የሚያዝ አንድ መልመጃ ብቻ መኖሩ ተመልክቷል፡፡ ለመጥቀስ ያህል

በምዕራፍ ስምንት፣ ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 139፣ መመሪያ 3 "የሚከተለውን ጽሑፍ በማንበብ ማስታወሻ ከያዛችሁ በኋላ አሳጥራችሁ አቅርቡ" የሚል ነው፡፡ በመሆኑም መልመጃው ተማሪዎቹ ምንባቡን አሳጥረው እንዲጽፉ የሚያደርግ ሲሆን ይህን ለማድረግ ደግሞ ምንባቡን ደጋግሞ ማንበብ ስለሚያስፈልግ የንባብ ክሂልን ለማስተማር የሚጠቅም ብልሃት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች መካከል አራተኛው አንድምታና ትንበያ ነው፡፡ ይህን በሚመለከት በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙት አንዳንድ ምንባቦች መካከል ተማሪዎች በሚያነቡበት ጽሑፍ ውስጥ ቀጥሎ ሊከሰት ስለሚችል ጉዳይ ግምታቸውን እንዲገልጹ ሲጠይቃቸው ይስተወላል፡፡ ለዚህ ማሳያ እንዲሆን የተወሰኑ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል ምዕራፍ አራት፣ ገጽ 57፣ ጥያቄ ቁጥር 3 በቀጣዩ የልቦለድ ክፍል በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል ምን ምን ክስተቶች የሚፈጠሩ ይመስላችኋል? 4. ታሪኩ በምን መልኩ ይቋጫል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ማስረጃችሁ ምንድነው? ምዕራፍ ስድስት፣ ገጽ 98፣ ቄስ ታምሩ ይሳካላቸው ይሆን? ምዕራፍ አሥር፣ ገጽ 167፣ በቀጣዩ የምንባቡ ክፍል ስለክርክር ምን የሚነሳ ይመስላችኋል? የሚሉ ይገኙበታል፡፡

ይህን አስመልክቶ በቁጥር 26፣ የንባብ ክሂል መልመጃዎች ለክሂሉ ማስተማሪያ የሚሆኑ ብልሃቶችን መሠረት ያደረጉ ናቸው (ለምሳሌ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል፣ አንድምታና ትንበያ)፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 1(10%)፣ "አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 4(40%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" በማለት መጠይቁን የሞሉት 2(20%) ናቸው፡፡ የአሃዝ መረጃው የሚያመለክተው ከንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች መካከል በጥቅም ላይ የዋሉ የመኖራቸውን ያህል በአገልግሎት ላይ ያልዋሉ ብልሃቶችም መኖራቸውን ነው፡፡

በአጠቃላይ በመጽሐፉ ላይ ከተካሄደው ምልከታ ለመገንዘብ እንደተቻለው ከአራቱ የንባብ ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች መካከል "ጥያቄ መጠየቅ" በአብዛኛው በጥቅም ላይ ሲውል "ማብራራትና መተርጎም" እንዲሁም አንድምታና ትንበያ አልፎ አልፎ ብቅ ሲሉ ታይተዋል፡፡ በአንጻሩም "ማጠቃለል" የተባለው ብልሃት በመጽሐፉ ውስጥ አንድም ቦታ ላይ አለመገኘቱን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎችን ለማስተማር የመጠቅሙ ዘዴዎች እንዳሉም ቀደም ባሉት ክፍሎች ተጠቁሟል። ከእነዚህም መካከል ውጤታዊና ሂደታዊ የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ። በመጽሐፉ ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎችን በሚመለከት የተወሰኑ ምሳሌዎችን በመጥቀስ እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል።

ከጽሕፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች መካከል አንዱ ውጤታዊ የአቀራረብ ዘዴ ነው። ይህን በሚመለከት በመጽሐፉ ውስጥ የተወሰኑ መልመጃዎች ሰፍረዋል። ለምሳሌ ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 44፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ስለአንቀጽ ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብና የተሰጠውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡ ርዕሰ-ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ፤ ምዕራፍ ስድስት፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት ገጽ 109፣ መመሪያ 3 የቀረበላችሁን የሥራ ደብዳቤ በመከተል በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በሚገኙ ክበቦች ውስጥ በአንዱ ሰብሳቢ ሆናችሁ እንደተመረጣችሁ በመገመት የክበቡ አባል ሆነው አብዛኛውን ጊዜ ለማይገኙ ተማሪዎች የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፉ፤ ምዕራፍ ስምንት፣ ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 138፣ መመሪያ 2 በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ አንቀጽ መጻፍ የሚያስችሉ አንዳንድ መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮችን ጻፉና አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ፤ የሚሉና የመሳሰሉት ይገኙበታል።

ከጽሕፈት ክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶች ሁለተኛው ሂደታዊ የአቀራረብ ዘዴ ነው። በዚህ ዘዴ አማካይነት ተማሪዎች ክሂሉን እንዲማሩ የሚያዙ በጣም ጥቂት መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ። እነሱም፡-

ምዕራፍ ሦስት፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 49፣ መመሪያ 6 በቡድን ሆናችሁ አንድ ተራኪ ድርሰት መጻፍ እንድትችሉ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል አከናውኑ፤

1. እየተወያያችሁ ርዕስ ምረጡ።
2. በርዕሱ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በአስተዋጽኦ መልክ ዘርዝሩ።
3. በሐሳብ የሚቀራረቡ ዝርዝሮችን እየለያችሁ በአንድ ላይ መድቡ።
4. ስለአንቀጽ በተማራችሁት መሠረት የድርሰቱን የመጀመሪያ ረቂቅ ጻፉ።
5. የጻፋችሁትን የድርሰት ረቂቅ አንብባችሁ የስርዓተ-ነጥቦችና የሰዋስው ግድፈቶችን በማረም እንደገና ጽፋችሁ አቅርቡ።
6. ድርሰታችሁን ከሌላ ቡድን ጋር በመለዋወጥ ከሐሳብ ፍሰቱ፣ ከድርጊትና ጊዜ ቅደም

ተከተል አጠባበቁና ከሥርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀሙ አንጻር መርምራችሁ የቡድናችሁን አስተያየት ስጡ።

ምዕራፍ አራት፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 67፣ መመሪያ 5 መምህራችሁ ከሚሰጧችሁ ርዕሶች አንደኛውን መርጣችሁ፣ የላይኛውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ የራሳችሁን አስተዋጽኦ ነድፋችሁ አቅርቡ፤

ምዕራፍ ሰባት፣ ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 126፣ መመሪያ 5 ከላይ የተሰጠውን ማብራሪያ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ስለአካባቢያችሁ የሚያስረዳ አንድ አስረጅ ድርሰት ጻፉና ለክፍላችሁ በንባብ አሰሙ፤

1. ለመጻፍ በቅድሚያ ርዕስ ምረጡ፣
2. በመረጣችሁት ርዕስ ዙሪያ ምን ምን ጉዳዮች ሊነሱ እንደሚችሉ አስተዋጽኦ ንደፉ።
3. ከዚያም በነደፋችሁት አስተዋጽኦ መሠረት ድርሰታችሁን ጻፉ።
4. የጻፋችሁትን ለጓደኞቻችሁ በማሳየት፣ ማሻሻያ ሐሳብ ተቀበሉና ድርሰታችሁን እንደገና ጻፉ፤

የሚሉ ይገኙበታል።

እነዚህ ሁለቱ የጽሕፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች (ውጤታዊና ሂደታዊ የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴዎች) የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ለማሳደግ የሚኖራቸው አስተዋጽኦ የጎላ ነው። ይሁን እንጂ በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡበትን መጠን ስንመለከት በጣም ጥቂት ሊባል የሚችል መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

ጉዳዩን አስመልክቶ በቁጥር 27፣ የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ ውጤታዊና ሂደታዊ የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው "በጣም እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 1(10%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 3(30%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ብለው የመለሱት 4(40%) ሲሆኑ "አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 2(20%) ናቸው። ይህ መረጃ የሚጠቁመው የጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር የሚረዱ ዘዴዎች መኖራቸውን፣ ነገር ግን በበቂ መጠን አለመቅረባቸውን ነው።

በውጤት ተኮር የጽሕፈት ክሂል አቀራረብ ዘዴ በየደረጃው የተለያዩ ተግባራት ይከናወናሉ። እነዚህም፡- የቁጥጥር ጽሕፈት /controlled writing/፣ የመር ጽሕፈት /guided writing/ እና የነፃ ጽህፈት /free writing/ ስልቶች በመባል የሚታወቁ ናቸው። ቀደም ሲል እንደተጠቆመው የጽሕፈት ክሂል በመጽሐፉ ውስጥ በውጤት ተኮር ማስተማሪያ ዘዴ ለልምምድ የቀረበው በሦስት ምዕራፎች ውስጥ ነው። በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙት የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች ከሦስቱ ስልቶች መካከል በየትኞቹ ስልቶች እንደቀረቡ ቀጥሎ እንመለከታለን፤

1ኛ. ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 44፣ መመሪያ 1 "ከዚህ በታች ስለአንቀጽ ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብና የተሰጠውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡ ርዕሰ-ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ" የሚል የገኛል። ይህ መልመጃ ተማሪዎች ከተሰጣቸው ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ እንዲጽፉ የሚያዝ ነው። ስለሆነም ስልቱ የቁጥጥር ጽሕፈት /controlled writing/ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።

2ኛ. ምዕራፍ ስድስት፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት ገጽ 109፣ መመሪያ 3 "የቀረበላችሁን 'የሥራ ደብዳቤ' በመከተል በትምህርት ቤታችሁ ውስጥ በሚገኙ ክበቦች ውስጥ በአንዱ ሰብሳቢ ሆናችሁ እንደተመረጣችሁ በመገመት የክበቡ አባል ሆነው አብዛኛውን ጊዜ ለማይገኙ ተማሪዎች የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ ጻፉ" የሚል ነው። ይህ የጽሕፈት ክሂል መልመጃ ይዘቱ ሰፋ ከማለት ውጭ ከላይ ከቀረበው መልመጃ የተለየ ነገር የሌለውና ተማሪዎቹ ተመሳሳይ ተግባር በተመሳሳይ ስልት እንዲያከናውኑ የሚያዝ ነው። ስለሆነም መልመጃው የተከተለው የቁጥጥር ጽሕፈት /controlled writing/ ስልት መሆኑን መመልከት ይቻላል።

3ኛ. ምዕራፍ ስምንት፣ ክፍል ሁለት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 138፣ መመሪያ 2 "በሚከተሉት ርዕሰ ጉዳዮች ዙርያ አንቀጽ መጻፍ የሚያስችሉ አንዳንድ መንደርደሪያ ዓረፍተነገሮችን ጻፉና አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ" ሲል የቀረበ ነው። ይህም ቢሆን ቀደም ሲል ከቀረቡት የተለየ ነገር የሌለው ነው።

ሦስቱም የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች ውጤታዊ የአቀራረብ ዘዴን የተከተሉ ሲሆኑ ተማሪዎች በተሰጣቸው ርዕስ ላይ ተመስርተው ውስን አንቀጾችን እንዲጽፉ የሚያዙ ናቸው። የአጻጻፍ ስልታቸውም ልዩነት የማይታይባቸው፣ ተማሪዎቹ የተለያዩ የአጻጻፍ ስልቶችን እንዲለማመዱ የማይጋብዙና በአንድ ስልት ብቻ ተወስነው እንዲቀሩ የሚያደርጉ መሆናቸውን

መረዳት ተችሏል። ለምሳሌ ያህል ተማሪዎቹ በመር ጽሕፈት ስልት /guided writing/ የተጀመሩ ዓረፍተ ነገሮችን፣ አንቀጾችን፣ ድርሰቶችን፣ ወዘተ. እንዲጨርሱ እንደዚሁም በነጻ የጽሕፈት ስልት /free writing/ ራሳቸው ርዕስ መርጠው የተለያዩ የጽሕፈት ተግባራትን እንዲያከናውኑ የሚያዝበት ሁኔታ በመጽሐፉ ውስጥ አለመገኘቱ ተመልክቷል።

ይህን በሚመለከት በጥያቄ ቁጥር 28፣ የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ በቁጥጥር ጽሕፈት /controlled writing/፣ በመር ጽሕፈት /guided writing/ እና በነፃ ጽሕፈት /free writing/ ስልት ተለይተው ቀርበዋል፣ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 1(10%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 1(10%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 3(30%)፣ "አልስማማም" ሲሉ መጠይቁን የሞሉት 2(20%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ያሉት 3(30%) ናቸው። ከዚህ የአሃዝ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው መጽሐፉ በመልመጃዎቹ ውስጥ የጽሕፈት ክሂልን ለማስተማር የሚያገለግሉ ልዩ ልዩ ስልቶችን በስፋት አካቶ አለመያዙን ነው።

በአጠቃላይ እጥኚው በመማሪያ መጽሐፉ ላይ ካካሄደው ምርመራና ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ከተገኘው ምላሽ መረዳት እንደቻለው የክሂል ማስተማሪያ ብልሃቶችና ዘዴዎች መጠናቸው የተለያየ መሆናቸውን ነው። ከአራቱም ክሂሎች መካከል አንጻራዊ በሆነ መልኩ ለንግግር ክሂል ማስተማሪ የሚሆኑ በርካታ ብልሃቶች መስፈራቸውንና ለሌሎቹ ክሂሎች የቀረቡት ብልሃቶች ግን በዓይነትም ሆነ በመጠን በበቂ መጠን አለመቅረባቸውን መገንዘብ ተችሏል።

ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ የሆነው የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ዋነኛው ዓላማ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በንግግር ድምጾች አማካይነት በወረቀት ላይ በማስፈር ከሌላ ሰው ጋር መግባባት እንዲችሉ ማድረግ መሆኑ ቀደም ሲል በስፋት ተጠቅሷል። ይህ የጽሕፈት ክሂል ትምህርት ስኬታማ የሚሆነው ደግሞ ለዚሁ ታስበው በሚዘጋጁት ተገቢ በሆኑና ብቃት ባላቸው መልመጃዎች ሲታገዝ ነው። በመሆኑም ለጽሕፈት ክሂል ታስበው የተዘጋጁት መልመጃዎች ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ በማስፈር መግባባት እንዲችሉ የማገዛቸው ደረጃ ምን ያህል እንደሆነ ከመጽሐፉ ውስጥ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማንሳት እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፤

ምዕራፍ አንድ፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 11 በዚህ ምዕራፍ በቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ላይ የተደረገውን ውይይት በድጋሚ አንብባችሁ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦችን በሚከተለው ሠንጠረዥ አስፍሩ፡፡

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ምሳሌ፣ ቋንቋ በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ አደጋ ተናጋሪ ሲያጣ | እሱም አብሮ ይጠፋል |
| | |
| | |

ምዕራፍ ሁለት፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 23፣ መመሪያ 1 በስነ-ቃል ተግባራት ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች በማንበብ በመትከል (ማጠናከር)፣ በመግለጥና በማምለጥ ተግባራት ላይ ማስታወሻ ያዙ፡፡ የያዛችሁትን ማስታወሻ ተመርኩዛችሁ ከአንድ ገጽ ያላነሰ ማብራሪያ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡ መመሪያ 3 ቀደም ሲል ...የከወናችሁትን ጭውውት መሠረት በማድረግ ከሚከተሉት የጭውውት ተሳታፊ ገጸ-ባሕርያት መካከል አንዱን መርጣችሁ ከ3 - 5 ደቂቃ የሚረዝም አንድ ጭውውት ጻፉ፡፡ መመሪያ 4 በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ ባህላዊ ምግቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ፡፡ ከዘረዘራችኋቸው ባህላዊ ምግቦች ውስጥ አንድ አንድ በመከፋፈል ስለአሰራሩ የሚያብራራና የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ መግለጫ ጽፉችሁ...፡፡

ምዕራፍ አራት፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 44፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ስለ አንቀጽ ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብና የተሰጠውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡት ርዕሰ-ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡ መመሪያ 6 በቡድን በቡድን ሆናችሁ አንድ ተራኪ ድርሰት መጻፍ እንድትችሉ የሚከተሉትን ተግባራት በቅደም ተከተል አከናውኑ ....፡፡

ምዕራፍ አራት፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 64፣ መመሪያ 1 ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሐረጋት በልቦለዱ ውስጥ ያላቸውን ፍች የሚያሳዩ ዓረፍተነገሮችን መሥርቱ፡፡ መመሪያ 5 መምህራችሁ ከሚሰጧችሁ ርዕሶች አንደኛውን መርጣችሁ ምሳሌውን መነሻ በማድረግ የራሳችሁን አስተዋጽኦ ነድፋችሁ አቅርቡ፡፡

ምዕራፍ አምስት፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ ገጽ 85፣ መመሪያ 1 የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ በጥሞና አንብቡና "እሱ" የተባለው ሰው ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለው፣ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ የቱን ያህል ጎጂ እንደሆነ ጽፋችሁ ለክፍል አቅርቡ፤ የሚሉና ሌሎችም

ተመሳሳይ መልክና ቅርጽ ያላቸው የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙት በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ሰፍረዋል። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

በጥያቄ ቁጥር 29፣ የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በወረቀት ላይ በማስፈር መግባባት እንዲችሉ የሚያደርጉ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለተነሳላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 4(40%) ሲሆኑ "አልስማማም" በማለት የመለሱት 2(20%) ናቸው።

በአጠቃላይ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች ምን እንደሚመስሉ የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማንሳት ለማሳየት ተሞክሯል። ጉዳዩን በሚመለከት ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኙት መረጃዎች እንደሚያሳዩት የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ በማስፈር መግባባት እንዲችሉ የማድረግ አቅም ያላቸው መሆናቸውን ነው። በሌላ በኩል ሲታይ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በጽሑፍ በማስፈር መግባባት ከሚችሉባቸው ዘዴዎች መካከል እንደ ማመልከቻ፣ ቃለ-ጉባኤ፣ የሥራና የሰላምታ ደብዳቤ፣ ሪፖርት፣ ዘገባ፣ ወዘተ. ያሉት ተጠቃሽ ናቸው። ነገር ግን አጥኚው በመጽሐፉ ውስጥ በቀረቡት የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች ላይ ካካሄደው ምርመራ መረዳት የቻለው እነዚህን የሚመለከቱ መልመጃዎች አለመቅረባቸውን ነው። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

የቋንቋ ክሂል መልመጃዎች በሚዘጋጁበት ጊዜ አሳታፊና ተማሪዎች በልዩ ልዩ ዘዴዎች መለማመድ እንዲችሉ የሚጋብዙ መሆን ይኖርባቸዋል። ይህም የሚሆነው መልመጃዎቹ በአቀራረባቸው ተማሪዎቹ በግል፣ በጥንድና በቡድን ሆነው እንዲያከናውኗቸው የሚያደርጉና ለተግባራቱም የሚያበረታቱ ሆነው ሲገኙ ነው። ከዚህ አኳያ በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት መልመጃዎችን አቀራረብ የተወሰኑ ማስረጃዎችን በማንሳት እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን ምንባቦች ተከትለው የተቀረጹት መልመጃዎች በአብዛኛው የተማሪዎቹን አንብቦ የመረዳት ችሎታ መሠረት በማድረግ በግልና በጥንድ/ቡድን የሚመለሱ ናቸው። ለዚህም የመልመጃዎቹ ትዕዛዞችና የጥያቄዎቹ ባሕርይ ማረጋገጫ ናቸው። ለምሳሌ

በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡት የክሂል መልመጃዎች መካከል የተወሰኑት በየትኛው ዘዴ (በጥንድና በቡድን) እንደሚተገበሩ ከመመሪዎቹ መረዳት የሚቻል ሲሆን አብዛኛው ግን ለአተገባበሩ ግልጽ ትዕዛዝ የሌላቸው ናቸው፡፡ ግልጽ ትዕዛዝ የሌላቸውን መልመጃዎች ተማሪዎቹ በግላቸው እንዲያከናውኗቸው ታስቦ ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ ያህል የተወሰኑ ማሳያዎችን በመውሰድ ቀጥሎ መመልከት ይቻላል፤

## ተማሪዎች በግላቸው የሚመልሷቸው መልመጃዎች

ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 6፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ መመሪያ 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፤

1. ዘዬ ምንድነው?
2. የሰው ልጅ ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ የሚለየው በምንድነው?

ወዘተ.

ገጽ 6፣ መመሪያ 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆኑ "እውነት" ስህተት ከሆኑ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ፤

1. ቋንቋ ድምጻዊ መግባቢያ ነው፡፡ ማንኛውም ድምጽ ደግሞ እስካግባባን ድረስ ቋንቋ ነው፡፡
2. ቋንቋ በሥርዓት የሚሰደሩ ድምጾች ስብስብ ነው፡፡

ገጽ 7፣ መመሪያ 3 ከዚህ በታች ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ቃላት ቀርበዋል፡፡ ቃላቱ በምንባቡ ውስጥ ባላቸው አገባብ መሠረት ፍቻቸውን ስጡ፤

1. ግጠሽ
2. አመሻሽ
3. ኢ-ደመነፍሳዊ
4. ተለዋዋጭ

ወዘተ.

ገጽ 7 - 8፣ መመሪያ 4 ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት መዝገበ ቃላትን ተጠቅማችሁ ቀጥተኛ ፍቻቸውን ስጡ፤

1. ህብረተሰብ
2. መስክ
3. በደመ-ነፍስ
4. ማንነት

ወዘተ.

ገጽ 8፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 2 የሚከተሉት ሐረጎች ከምንባቡ የወጡ ናቸው። የያዙትን መልዕክት በራሳችሁ አባባል አብራሩ፤

1. ማኅበራዊና ባህላዊ እድገት
2. ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ
3. የቋንቋ ማኅበራዊ አገልግሎት

ገጽ 8፣ ክፍል ሦስት፡- ማዳመጥ፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ "መደበኛና ኢ-መደበኛ ቋንቋ" በሚል ርዕስ የተዘጋጀ አንድ ጽሑፍ ያነቡላችኋል፤

1. እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ።

ገጽ 9፣ መመሪያ 2 ..."የቋንቋ ልደትና ሞት" በሚል ርዕስ በመንስኤና ውጤት የተዋቀሩ አንቀጾችን የያዘ አንድ አጭር ጽሑፍ በንባብ ይቀርብላችኋል፤

1. እያዳመጣችሁ በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦችን ብቻ ለይታችሁ በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ።

ገጽ 11፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ በዚህ ምዕራፍ በቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ላይ የተደረገውን ውይይት በድጋሚ አንብባችሁ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦችን በሚከተለው ሠንጠረዥ አስፍሩ፤

| ምክንያት | ውጤት |
|---|---|
| ምሳሌ፣ ቋንቋ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ተናጋሪ ሲያጣ | እሱም አብሮ ይጠፋል |
| | |
| | |

ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 19፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት አንዱ ከስነ-ቃል ሊመደብ አይችልም፤

ሀ) ምሳሌያዊ ንግግር
ለ) እንቆቅልሽ
ሐ) የሥራ ላይ ግጥሞች
መ) ልቦለድ መጻሕፍት

ወዘተ.

ገጽ 20፣ መመሪያ 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

1. "በጽሑፍ ያልሰፈረ ነገር ግን በቃል የሚከወኑ የቋንቋ ጥበቦች" ሲል ምን ማለቱ

ነው? በምሳሌ አብራሩ፡፡

ወዘተ.

ገጽ 23፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ መመሪያ 1 ስለ ስነ-ቃል ተግባራት ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች በማንበብ በመትከል (ማጠናከር)፣ በመግለጽና በማምለጥ ተግባራት ላይ ማስታወሻ ያዙ፡፡ የያዛችሁትን ማስታወሻ ተመርኩዛችሁ ከአንድ ገጽ ያላነሰ ማብራሪያ በጽሑፍ አቅርቡ፤

ገጽ 23፣ መመሪያ 2 ቀጥሎ "የስነ-ቃል ዘውጎች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ጽሑፍ መምህራችሁ አንድ ጊዜ ያነቡላችኋል፤

1. እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ፍሬ ሐሳቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ፡፡

ገጽ 23፣ መመሪያ 3 ...ከሚከተሉት የጭውውት ተሳታፊ ገጸ-ባሕርያት መካከል አንዱን ምረጣችሁ፤

1. ከ3 - 5 ደቂቃ የሚረዝም አንድ ጭውውት ጻፉ፤

*አማራጭ ርዕሶች*

ሀ) አባት፣ እናትና ልጅ

ለ) ርዕሰ መምህር፣ ተማሪና መምህር

ሐ) ሻጭ፣ ገዢና ደላላ

መ) በሽተኛ፣ ሐኪምና አስተማማሚ

ሠ) ዳኛ፣ አቃቤ ሕግና ጠበቃ

ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 37፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ መመሪያ 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ፤

1. ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ የሰው ልጅ ጽሕፈትን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የተገለጸባቸውን ቃላዊ ፈጠራዎች ያመለክታል፡፡
2. አንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊ ነው ለመባል በጽሑፍ መቅረብ ብቻ በቂ አይደለም፡፡

ወዘተ.

ገጽ 37 - 38፣ መመሪያ 2 ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መልስ ምረጡ፤

1. ከሚከተሉት አንዱ የአንድ ጽሑፍ ኪነ-ጥበባዊ ብቃት መመዘኛ አይደለም፡፡

ሀ) በአገላለጹ የተባ መሆን

ለ) በጽሑፍ አማካይነት መገለጹ

ሐ) ሕይወትን ማሳየት

መ) ማራኪና ሳቢ መሆን

ወዘተ.

ገጽ 39፣ መመሪያ 3 በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ እየተሰመረባቸው ለቀረቡ ቃላት አገባባዊ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ በሰጣችሁት ፍች መሠረት የራሳችሁን ዓረፍተነገር መስርቱ፤

1. ስነ-ጽሑፍ በጽሑፍ የተቀረጸውን የቋንቋ ጥበብ ይመለከታል፤
2. ሰዎች ስለሕይወት ያላቸውን ግንዛቤ በቋንቋ አማካይነት ያንጸባርቃሉ።

ወዘተ.

ገጽ 39 - 40፣ መመሪያ 4 ለሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው፤

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፈጠራ | 3. አጓጊ | 5. ህይወት |
| 2. ኪነ-ጥበብ | 4. ቅርጽ | 6. ቁርኝት |

ገጽ 40፣ መመሪያ 5 ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ ርዕሰ-ጉዳዮች አንዱን ምረጡና በአካባቢያችሁ ወደሚገኘው የሕዝብ ቤተ-መጻሕፍት ወይም ወደ ትምህርት ቤታችሁ ቤተ-መጻሕፍት በመሔድ ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች መረጃ ሰብስቡ፤

ሀ) ከአሥር ያላነሱ የልቦለድ መጻሕፍትን በማገላበጥ፦ የደራሲውን ስም፣ የመጽሐፉን ስም፣ የህትመት ስፍራ፣ አሳታሚ ድርጅትና የመጽሐፉን የገጽ ብዛት ዝርዝር አቅርቡ።

ወዘተ.

ገጽ 42፣ ክፍል ሁለት፦ ማዳመጥ፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ "ደራሲና የህይወት ልምዱ" በሚል ርዕስ አንድ ማብራሪያ ሁለት ጊዜ ያነቡላችኋል። ማብራሪያውን ከማዳመጣችሁ በፊት ከርዕሱ በመነሳት የርዕሱ ትኩረት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ፤

መመሪያ 2 ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥቄዎች አንብባችሁ በአእምሮኣችሁ በመያዝ ማብራሪያውን እያዳመጣችሁ መልሶቻችሁን ስጡ፤

1. ልምድ ምንድነው?
2. ደራሲው የሚጽፈው በተግባር በራሱ ደርሰው የተገለጡለትን ልምዶች ብቻ ነው?

ወዘተ.

ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ ገጽ 44፣ መመሪያ 2 ባለፈው ሳምንት ያሳለፋችሁትን የእሁድ ቀን ውሎ የድርጊት እና የጊዜ ቅደም ተከተሉን ጠብቃችሁ ከ3 - 5 ደቂቃ የሚረዝም ንግግር አድርጉ፤

ገጽ 44፣ ክፍል አራት፡- ጽሕፈት፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ስለ አንቀጽ ምንነት የቀረበውን ማስታወሻ በማንበብና የተሰጠውን ምሳሌ መሠረት በማድረግ ቀጥሎ ከተሰጡት ርዕሰ-ጉዳዮች አንዱን በመምረጥ አንድ አንቀጽ ጻፉ፤

1. ማርፈድ
2. ከትምህርት ቤት መቅረት

ወዘተ.

ገጽ 46. መመሪያ 3 ከዚህ በታች በቀረበው አንቀጽ ውስጥ በተጓደሉ ሥርዓተ-ነጥቦች ምትክ ቁጥሮች ሰፍረዋል። በቁጥሮቹ ቦታ መግባት ያለበትን ሥርዓተ ነጥብ ግለጹ፤

ገጽ 47፣ መመሪያ 4 ቀጥሎ "ፈሪው ወታደር" በሚል ርዕስ አንድ ተራኪ ድርሰት ቀርቦላችኋል። ድርሰቱን በጥንቃቄ ካነበባችሁ በኋላ በስተመጨረሻ የቀረቡትን ጥያቄዎች በጽሑፍ መልሱ፤

ገጽ 48፣ መመሪያ 5 የሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ቅደም ተከተላቸው ቢስተካከል አንድ ተራኪ ድርሰት ይወጣቸዋል። ዓረፍተነገሮቹን በጥንቃቄ መርምራችሁ ቅደም ተከተላቸውን አስተካክሉ። ለድርሰቱም ርዕስ ስጡ፤

1. በክረምት ለእረፍት ትምህርት ቤት ሲዘጋ እንደምጠይቃት አስቀድሜ ለአክስቴ ...
2. በዚያው ሰሞን እናቴ አክስቴን ጠይቃ ስትመለስ ...
3. በልጅነቴ የምወዳትን አክስቴን ለመጠየቅ ...

ወዘተ.

ለአብነት ያህል እስከ ምዕራፍ ሦስት ያሉት ተጠቀሱ እንጂ በመጽሐፉ ውስጥ የእነዚህ ዓይነት መልመጃዎች በቀሩት ሰባቱም ምዕራፎች ውስጥ በብዛት ይገኙባቸዋል። የእነዚህን ቀደም ሲል በዝርዝር የቀረቡትን የመልመጃ ትዕዛዞችና ጥያቄዎች ባሕርይ ስንመለከት ተማሪዎች ምንባቦችንና የተሰጡ ምሳሌዎችን መሠረት በማድረግ ምላሽ እንዲሰጡ የሚጋብዙ ናቸው። ምላሽ የሚሰጡባቸውን ሁኔታዎች ስናጤናቸው በጥንድ ወይም በቡድን እንዲያከናውኗቸው የሚያበረታቱና በግልጽ ትዕዛዝ የታገዙ አይደሉም። በመሆኑም እነዚህ

መልመጃዎች ከጥንድና ከቡድን ሥራ ይልቅ የተማሪዎችን የግል ጥረትና ተግባራት የሚያበረታቱ መሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል።

**ለአተገባበራቸው ግልጽ ትዕዛዝ ያላቸው (በጥንድና በቡድን የሚሠሩ) መልመጃዎች**

ቁጥራቸው በጣም ጥቂት ይሁን እንጂ ተማሪዎች በጥንድ ወይም በቡድን ሆነው እንዲያከናውኗቸው የሚያዙ መልመጃዎችና ትምህርታዊ ተግባራትም በመጽሐፉ ውስጥ መገኘታቸው ተመልክቷል። እነዚህን በሚመለከት ቀደም ሲል በተጠቀሱት በሦስቱ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙትን መልመጃዎች በመረጃነት በማንሳት ንጽጽራቸውንም ጭምር ከዚህ ቀጥሎ መመልከት ይቻላል።

ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 2፣ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች፣ መመሪያ 1 መምህራችሁ በሚነግሯችሁ መሠረት ቡድን መስርታችሁ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፤

1. ቋንቋ ምንድነው?
2. ቋንቋ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የሚሰጠው አገልግሎት ምንድነው?

መመሪያ 2 በውይይታችሁ የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፤

ገጽ 8፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ፤

1. ዘዬዎች እንዴት ይፈጠራሉ?
2. በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚኖር የዘዬ ልዩነት መግባባትን አያግድም የሚባለው ለምንድነው?

ገጽ 9 - 10፣ መመሪያ 2 ..."የቋንቋ ልደትና ሞት" በሚል ርዕስ በመንስኤና ውጤት የተዋቀሩ አንቀጾችን የያዘ አንድ አጭር ጽሑፍ በንባብ ይቀርብላችኋል፤

2. በቡድን ሆናችሁ በተናጠል የመዘገባችኋቸውን በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦች ዝርዝር አስተያዩ፤ ባዳመጣችሁት መሠረት በትክክል የተወሰዱ ስለመሆናቸው ተወያዩ።

3. በውይይታችሁ የተስማማችሁባቸውን በመንስኤና ውጤት የተገለጹ ሐሳቦች ዝርዝር በቡድን መሪያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 20፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ የምታውቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች በየተራ ተጠያየቁ፡፡ መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ መብራሪያ ይስጥ፤

ገጽ 21፣ መመሪያ 2 ከዚህ በታች አጥንታችሁ የምትተውኑት ጭውውት ቀርቧል፡፡ ...

ገጽ 23፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ መመሪያ 2 ቀጥሎ "የስነ-ቃል ዘውጎች" በሚል ርዕስ የተዘጋጀውን ጽሑፍ መምህራችሁ አንድ ጊዜ ያነቡላችኋል፤

2. ቡድን መስርታችሁ በተናጠል የያዛችሁትን ማስታወሻ አስተያዩ፡፡

3. የተስማማችቡባቸውን ፍሬ ሐሳቦች የያዘ ማስታወሻ ለመምህራችሁ አቅርቡ፡፡

ገጽ 23፣ መመሪያ 3 ...ከሚከተሉት የጭውውት ተሳታፊ ገጸ-ባሕርያት መካከል አንዱን መርጣችሁ፡-

2. የጻፋችሁትን ጭውውት አጥንታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ገጽ 24፣ መመሪያ 4 በቡድን ሆናችሁ በመወያየት፡-

1. በአካባቢያችሁ የሚዘወተሩ ባህላዊ ምግቦች ምን ምን እንደሆኑ ዘርዝሩ፡፡
2. ከዘረዘራችኋቸው ባህላዊ ምግቦች ውስጥ አንድ አንድ በመከፋፈል ስለአሠራሩ የሚያብራራና የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ መግለጫ ጽፋችሁ ለቡድናችሁ አባላት በማቅረብ ተወያዩበት፡፡

ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 42፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ ርዕሶች መካከል አንዱን በመምረጥ የውይይት መመሪያን ተከትላችሁ ተወያዩ፤

*የመወያያ ርዕሶች*

ሀ) የትምህርት ቤታችን ተማሪዎች የንባብ ልምድ ያለበት ደረጃ፣ ችግሮቹና መፍትሄዎች

ለ) ለትምህርት ቤታችን የ"ሚኒ-ሚዲያ" አገልግሎት ያለበት ደረጃና የሚጠናከርባቸው መንገዶች

ሐ) በትምህርት ቤታችን የስነ-ጽሑፍ ክበብ አስፈላጊነትና አሁን ያለበት ደረጃ

ገጽ 45፣ መመሪያ 2 በጥንድ ሆናችሁ የጻፋችሁትን ከተለዋወጣችሁ በኋላ፡-

1. የጓደኞቻችሁን አንቀጽ ኃይለ-ቃልና መዘርዝር ዓረፍተነገሮችን ለዩ።
2. አንቀጹ የያዛቸውን ዓረፍተነገሮች የሐሳብ ዝምድናቸውን የጠበቁና በኃይለ-ቃሉ ከሰፈረው ዋና ሐሳብ ያልወጡ መሆናቸውን አረጋግጡ።

ወዘተ.

ገጽ 49፣ መመሪያ 6 በቡድን ሆናችሁ አንድ ተራኪ ድርሰት መጻፍ እንድትችሉ የሚከተሉትን ተግባራ በቅደም ተከተል አከናውኑ፤

1. እየተወያያችሁ ርዕስ ምረጡ
2. በርዕሱ ሊካተቱ የሚገባቸውን ነጥቦች በአስተዋጽኦ መልክ ዘርዝሩ

ወዘተ.

እነዚህ በዝርዝር የተመለከቱት ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን ሆነው የሚያከናውኗቸው የክሂል መልመጃዎች ናቸው። በሦስት ምዕራፎች ውስጥ ከተካተቱት የክሂል መልመጃዎችና ለመልመጃዎቹ አሰራር ከተሰጡት ትዕዛዞች መገንዘብ እንደሚቻለው ትምህርታዊ ተግባራቱ በተለያዩ ስልቶች የሚከናወኑ መሆናቸውን ነው። እነዚህም ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን በመሆን የቋንቋ ክሂሎችን እንዲለማመዱ የሚያደርጉ መሆናቸውን ያመለክታል። በአጠቃላይ በተጠቀሱት ሦስቱ ምዕራፎች ወስጥ የቀረቡት የመልመጃ ትዕዛዞች በሁለቱ የመለማመጃ ስልቶች (በግልና በጥንድ/በቡድን) የቀረቡበትን መጠን ከሚከተለው ሠንጠረዥ መገንዘብ ይቻላል፤

*ሠንጠረዥ 11፣ ስለመልመጃዎች አተገባበር ዘዴ የቀረቡት ትዕዛዞች*

| ምዕራፍ | ስለአተገባበራቸው በግልጽ ያልተገለጹ (በግል የሚከወኑ) ትዕዛዞች ብዛት | በጥንድ/በቡድን እንዲከናወኑ የሚያዙ ትዕዛዞች ብዛት |
|---|---|---|
| አንድ | 8 | 2 |
| ሁለት | 5 | 5 |
| ሦስት | 12 | 3 |
| ጠቅላላ | 25(71.5%) | 10(28.5%) |

እዚህ ላይ ልብ ሊባሉ የሚገባቸው ሁለት ጉዳዮች አሉ። እነሱም፡- የመልመጃ ጥያቄዎቹ ባሕርይ ተማሪዎቹ በጥንድና በቡድን በመሆን ለሚያካሒዱት የቋንቋ ልምምድ ያላቸው አመቺነትና ለመልመጃ ጥያቄዎቹ የቀረቡት ትዕዛዞች ናቸው። በዚህ መሠረት የተወሰኑ ትዕዛዞች ምንም እንኳን ስለመልመጃ ጥያቄዎቹ አተገባበር ግልጽ አቅጣጫ የሚጠቁሙ

ባይሆኑም በስራቸው የሚገኙት ጥያቄዎች ግን በራሳቸው ችግር የሌለባቸውና መምህራን እንደአመቺነታቸው ተስማሚ በሆኑ ዘዴዎች ሁሉ እንዲተገብሯቸው የሚያስችሉ መሆናቸው መረዳት ተችሏል፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

*ሠንጠረዥ 12፣ የክሂል መልመጃዎቹ አዘገጃጀት ተማሪዎች ቋንቋውን እንዲለማመዱ የሚያስችሉ ስለመሆናቸው*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 19 | የክሂል መልመጃዎቹ (ጥያቄዎቹ) አቀራረብ የተማሪዎችን በግል፣ በጥንድና በቡድን የመማር ሂደት የሚያበረታቱ ናቸው፡፡ | 6 (60%) | 2 (20%) | 2 (20%) | - | - |
| 30 | የክሂል መልመጃዎቹ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ለሚደረጉ የቋንቋ ልምምዶች የሚጋብዙ ናቸው፡፡ | 2 (20%) | 2 (20%) | 2 (20%) | 4 (40%) | - |
| 32 | የክሂል መልመጃዎቹ አዘገጃጀት ተማሪዎች ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም ሲጠቀሙበት በሚያስችላቸው መልኩ ነው፡፡ | 3 (30%) | 5 (50%) | 1 (10%) | - | 1 (10%) |

በጥያቄ ቁጥር 19፣ የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ የተማሪዎችን በግል፣ በጥንድና በቡድን የመማር ሂደት የሚያበረታቱ ናቸው፣ ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 6(60%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 2(20%) ሲሆኑ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት የገለጹት 2(20%) ናቸው፡፡ ይህ አሃዝ የሚያሳየው የመልመጃዎቹ አቀራረብ በግል፣ በጥንድና በቡድን ለሚካሔድ የመማር ሂደት አመቺ መሆናቸውን ነው፡፡

በምሳሌነት በተወሰዱት ሦስቱ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙት የክሂል መልመጃዎች በጥያቄ ደረጃ ሲታዩ ጉልህ ችግር የሌለባቸው ቢሆኑም አንዳንድ መልመጃዎች ከያሏቸው ትዕዛዞች አኳያ ሲታዩ ግን ሁለት መልክ ያላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህም የመጀመሪያው አብዛኞቹ (71.5%) ጥያቄዎች ተማሪዎች በየትኛው ዘዴ ታግዘው ምላሽ እንደሚሰጡባቸው በግልጽ ያልተቀመጡ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ ለተወሰኑት (28.5%) የመልመጃ ጥያቄዎች የመተግበሪያ ዘዴዎች ተለይተው የተቀመጡላቸው መሆናቸው ነው፡፡ በመሆኑም በግልጽ ትዕዛዝ ታግዘው ያልቀረቡ የመልመጃ ጥያቄዎች በግል ከመከናወናቸው በተጨማሪ በጥንድና በቡድን ለሚካሄዱ የቋንቋ ልምምዶች አጋዥ ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል፡፡

የቋንቋ ትምህርት ዓላማ ግቡን ሊመታ የሚችለው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን ቋንቋ በማኅበራዊ ኑሯቸው ውስጥ ሊለማመዱበትና ሊጠቀሙበት ሲችሉ ነው፡፡ ለዚህ ደግሞ የመልመጃዎቹ አዘገጃጀት የሚኖራቸው ሚና የጎላ ነው፡፡ በመልመጃዎች ውስጥ የሚገኙት ጥያቄዎች በባሕርያቸው ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ ከሚያደርጓቸው ተግባራት ባሻገር ላላቸው የቋንቋ ልምምዶችና ለሚያካሒዱት የዕለት ተዕለት መስተጋብር ትልቅ ድርሻ መበርከት ይጠበቅባቸዋል፡፡ በዚህ መሠረት በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙት የክሂል ይዘቶችና የመልመጃ ጥያቄዎች ምን መልክ እንዳላቸው የተወሰኑ ምሳሌዎችን በማንሳት እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል፡፡

ምሳሌ 1. ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 20፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ የምታውቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች በየተራ ተጠያየቁ፡፡ መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ማብራሪያ ይስጥ፤

ምሳሌ፡- "ጠያቂ፣ እንቆቅልህ(ሽ)"

መላሽ፣ "ምን አውቅልህ(ሽ)"

ጠያቂ፣ "የሰራኝ ይሸጠኛል፤ የገዛኝ አይጠቀምብኝም፤ የሚጠቀምብኝ አያየኝም፡፡
እኔ ማን ነኝ?"

መላሽ፣ "የሬሳ ሳጥን"

መልሱ የሬሳ ሳጥን የሆነበትን ልግለጽ፤ በመጀመሪያ ሰው ይሞታል....

ምሳሌ 2. ምዕራፍ ሦስት፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ ገጽ 40፣ መመሪያ 5 ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ ርዕስ ጉዳዮች አንዱን ምረጡና በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ የሕዝብ ቤተ-መጻሕፍት ወይም ወደ ትምህርት ቤታችሁ ቤተ-መጻሕፍት በመሔድ ከመጻሕፍት፣ ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች መረጃ ሰብስቡ፤

ሐ) በተለይ ጋዜጦችን በማገላበጥ የሚያጋጥሟችሁን ከአሥር በላይ ተረትና ምሳሌ ከመዘገባችሁ በኋላ፡- ተረትና ምሳሌዎቹን ያገኛችሁባቸውን ጋዜጦች ስም፣ የታተሙበትን ዓመተ ምህረት፣ ወርና ቀን በመዘርዘር አቅርቡ፡፡

ምሳሌ 3. ምዕራፍ አራት፣ ገጽ 63፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 ከልቦለድ ወይም ከሌሎች የፈጠራ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የሚደረጉ ውይይቶችን፣ የተሰነዘሩ

አስተያቶችን ወዘተ. ከሬዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን አዳምጣችሁ "ጠቃሚ ሐሳብ ነው" የምትሉትን በራሳችሁ አባባል ጽፋችሁ ለክፍል አቅርቡ።

ምዕራፍ 4. ምዕራፍ ስምንት፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ ገጽ 141፣ መመሪያ 4 የሸንኮራገዳ ተክል እንዴት እንደሚመረትና በፋብሪካ ውስጥ ወደ ስኳር ምርትነት እንዴት እንደሚለወጥ በማታወሻችሁ ላይ ተመስርታችሁ ለጓደኞቻችሁ ገለጻ አድርጉ፤

ይህ አስመልክቶ በጥያቄ ቁጥር 30፣ የክሂል መልመጃዎቹ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ለሚደረጉ የቋንቋ ልምምዶች የሚጋብዙ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደሚቻለው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 2(20%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 2(20%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት የገለጹት 2(20%) ሲሆኑ "አልስማማም" ሲሉ ምላሽ የሰጡት 4(40%) ናቸው። ይህ መረጃ የሚያሳየው መጽሐፉ በተወሰነ መልኩም ቢሆን ተማሪዎቹ ከክፍል ውጭ ላላቸው የቋንቋ ልምምድ የሚረዱ መልመጃዎችን አካቶ መያዙን ነው፤

በአጠቃላይ አጥኚው በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት የክሂል ይዘቶችና የመልመጃ ጥያቄዎች መረዳት እንደቻለው፣ አብዛኛዎቹ መልመጃዎች በምንባቦች ላይ የተመሰረቱና በክፍል ውስጥ የቋንቋ ልምምድ ወቅት የሚከናወኑ መሆናቸውን ነው። በአንጻሩም መጠናቸው አነስተኛ ቢሆንም በተወሰኑ ምዕራፎች ውስጥ ተማሪዎች ከክፍል ውጭ ለሚያከናውኑት የቋንቋ ክሂሎች ልምምድ የሚጋብዙ መልመጃዎች መኖራቸውን መገንዘብ ተችሏል።

የአንድ ቋንቋ ትምህርት ትልቁ ግብ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በተማሩት መሠረት ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም ውስጥ በሚፈልጉበት ቦታና ጊዜ እንዲጠቀሙ ማስቻል ነው። ቋንቋው በተማሪዎች የዕለት ተዕለት ህይወት ውስጥ በተገቢ ሁኔታ ጥቅም ላይ እንዲውል ከተፈለገ ደግሞ ለትምህርትነት የቀረቡት የክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት ትልቁን ሚና ይጫወታል። ከዚህ ረገድ መማሪያ መጽሐፉ፣ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም እንዲጠቀሙ የሚያስችሉ መልመጃዎችን ማካተት አለማካተቱን የተወሰኑ መልመጃዎችን በማንሳት እንደሚከተለው መመልከት ይቻላል።

ምዕራፍ አንድ፣ ገጽ 8፣ ክፍል ሦስት፡- ማዳመጥ፣ መመሪያ 1፣ ጥያቄ ቁጥር 1 እያዳመጣችሁ ዋና ዋና ነጥቦችን በማስታወሻ ደብተራችሁ መዝግቡ። ጥያቄ ቁጥር 2. ...የጽሑፉን መልዕክት በራሳችሁ አባባል አንዳችሁ ለአንዳችሁ ተናገሩ፤

ምዕራፍ ሁለት፣ ገጽ 20፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 በጥንድ ሆናችሁ የምታውቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች በየተራ ተጠያየቁ። መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ማብራሪያ ይስጥ፤

ምዕራፍ ሦስት፣ ገጽ 42፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ መመሪያ 1 ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ መወያያ ርዕሶች አንዱን በመምረጥ የውይይት መመሪያን ተከትላችሁ ተወያዩ። ውይይታችሁን በተሳካ ሁኔታ ለማካሔድ የሚከተሉትን ተግባራት በጥንቃቄ ፈጽሙ፤

1. ከመካከላችሁ አወያይ የሚሆን አንድ ተማሪ፣ ተወያይ የሚሆን አራት በድምሩ አምስት ተማሪዎችን ምረጡ።
2. በተወያይነት የተመረጣችሁ ተማሪዎች ከሦስቱ የመወያያ ርዕሶች አንዱን ምረጡ።
3. በመረጣችሁት ርዕስ ላይ ያተኮሩ ጽሑፎችን በማንበብና የሚመለከታቸው ሰዎች በማነጋገር መረጃ ሰብስባችሁና ለተከታዩ ክፍለ ጊዜ ለውይይት ተዘጋጅታችሁ ቅረቡ።
4. ተወያዮች ሀሳባቸውን ሲሰነዝሩ የቀራችሁት የውይይቱ ታዳሚዎች ሀሳባቸውን በማስታወሻ መዝግቡ።
5. ስለውይይቱ ሂደትና ስለተንጸባረቁ ሐሳቦች የሚያትት የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ አንድ ገጽ ጽሑፍ ለመምህራችሁ አቅርቡ።

*የመወያያ ርዕሶች*

ሀ) የትምህርት ቤታችን ተማሪዎች የንባብ ልምድ ያለበት ደረጃ፣ ችግሮቹና መፍትሔዎቹ
ለ) በት/ቤታችን የ"ሚኒ-ሚዲያ" አገልግሎት ያለበት ደረጃና የሚጠናከርባቸው መንገዶች
ሐ) በትምህርት ቤታችን የስነ-ጽሑፍ ክበብ አስፈላጊነትና አሁን ያለበት ደረጃ

ምዕራፍ አራት፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ ገጽ 61፣ መመሪያ 3 በልቦለድ ታሪኮች ላይ የተከሰተው ችግር ከመነሻው እንዳይፈጠር፣ ችግሩ ከተፈጠረ በኋላም በቀላሉ እንዲፈታ ምን መደረግ አለበት ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በየቡድን መሪያችሁ በክፍል አቅርቡ። ገጽ 63፣ ክፍል ሦስት፣ መመሪያ 2 በአጭር ልቦለዱ እንደታየው በሁለቱ ዋና ገጸባህርያት መካከል ከፍተኛ ያለመግባባት ተፈጥሯል። ለዚህ ተጠያቂው ማን ነው? ዘነበ ወይስ በልዩ? አንደኛውን ደግፋችሁ ሌላውን በመቃወም ተከራከሩ። በክርክሩ ያልተሳተፋችሁ ደግሞ በተከራካሪዎቹ የሚሰነዘሩ ሐሳቦች የቱን ያህል ምክንያታዊ መሆን አለመሆናቸው ላይ አስተያየት በመስጠት ተሳተፉ።

ምዕራፍ አምስት፣ ገጽ 84፣ ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ ጥያቄ ቁጥር 1 "ዳግመኛ ቃል ኪዳን" በሚል ርዕስ በቀረበው የገጣሚው ሐሳብ ላይ ትስማማላችሁ? ወይስ የሌለ ችግር ነው የተነሳው? በጥንድ በጥንድ ተወያዩና አቋማችሁን ከምክንያቶቻችሁ ጋር አቅርቡ።

ምዕራፍ ሰባት፣ ገጽ 127፣ ክፍል ሦስት፡- ንግግር፣ መመሪያ 4 የተለያዩ ቡድኖች በመመስረት፣ ከየቡድናችሁ ተከራካሪዎች ምረጡ፤ ከዚያም መምህራችሁ በሚሰጧችሁ መከራከሪያ ርዕሶች መካከል አንዱን በመውሰድ ቡድናችሁን ወክለው ለሚከራከሩት፣ የመከራከሪያ ሐሳቦች ስጧቸውና መመሪያን የተከተለ ክርክር አካሂዱ። በክርክሩ ሂደትም የቡድናችሁን አቋም የሚያንጸባርቁ የማዳበሪያ ሐሳብ ስጡ፤ የሚሉና ሌሎችም ተመሳሳይነት ያላቸው መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ።

ይህን በሚመለከት በጥያቄ ቁጥር 32፣ የክሂል መልመጃዎቹ አዘገጃጀት ተማሪዎች ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም ሲጠቀሙበት በሚያስችላቸው መልኩ ነው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 5(50%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ መጠይቁን የሞሉት 1(10%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" የሚል ምላሽ ያሰፈሩት 1(10%) ናቸው። ከዚህ የአሃዝ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው በመመሪያ መጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙ የክሂል መልመጃዎች መካከል ተማሪዎቹ ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም እንዲጠቀሙበት በሚያስችላቸው መልኩ የተዘጋጁት መልመጃዎች መኖራቸውን ነው።

በአጠቃላይ አጥኚው በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ በሚገኙት የክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀትና አቀራረብ ላይ ካካሄደው ፍተሻ መረዳት እንደቻለው አብዛኞቹ መልመጃዎች ለክፍል ውስጥ ልዩ ልዩ ተግባራትና የቋንቋ አጠቃቀም ትኩረት ያደረጉ መሆናቸውን ነው። ነገር ግን አልፎ አልፎ ሊባል በሚችል መልኩ ተማሪዎች በገሃዱ ዓለም ስለሚገጥማቸው ጉዳዮች የሚመለከቱ ልምምዶችን እንዲያከናውኑ የሚያዙ መልመጃዎች መኖራቸውም ተመልክቷል። ይህንንም በተዘዋዋሪ መንገድም ቢሆን ተማሪዎች በተለያዩ ጉዳዮች ላይ እንዲነጋገሩ፣ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ ሀሳብ እንዲሰጡ፣ ወዘተ. ከሚያበረታቱ መልመጃዎች ማወቅ ይቻላል።

መማሪያ መጽሐፉ በአሥር ምዕራፎች ተከፋፍሎ መቅረቡና በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ለአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ልምምድ የሚረዱ መልመጃዎች መቅረባቸው ቀደም ሲል ተጠቅሷል።

ከዚህ ጎን ለጎን መልመጃዎቹም የተቀረጹት በርካታ ሥነ-ጽሑፋዊ ሥራዎችንና ልዩ ልዩ ምንባቦችን መነሻ በማድረግ መሆኑም ተጠቁሟል። በዚህም የተነሳ የመልመጃ ጥያቄዎቹ አልፎ መመሳሰልና መደጋገም እንደሚታይባቸው ተስተውሏል። ለዚህ ማሳያ እንዲሆን የተወሰኑት እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል።

*ምሳሌ 1*፣ ምዕራፍ አንድ፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ *መመሪያ* 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፤

1. ዘዬ ምንድነው?

ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ *መመሪያ* 1 በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፤

1. ዘዬ እንዴት ይፈጠራል?

*ምሳሌ 2*፣ ክፍል አንድ፡- ንባብ፣ *መመሪያ* 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ፤

4. የቋንቋ ስነ-ልሳናዊ አገልግሎት ግለጹ።

*መመሪያ* 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ፤

4. የቋንቋ ስነ-ልሳናዊ አገልግሎት የተናጋሪውን ማንነት ማሳወቅ ነው።

*ምሳሌ 3*፣ *መመሪያ* 2 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ከሆነ "እውነት" ስህተት ከሆነ "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለጹ።

7. በአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች መካከል የዘዬ ልዩነት መኖር መግባባትን አያግድም።

ክፍል ሁለት፡- ንግግር፣ *መመሪያ* 1 በጥንድ ሆናችሁ ቀጥሎ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ተወያዩ። የደረሳችሁበትን መደምደሚያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፤

2. በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚኖር የዘዬ ልዩነት መግባባትን አያግድም የሚባለው ለምንድነው?

እነዚህ ሦስቱ ምሳሌዎች ከምዕራፍ አንድ የተወሰዱ ናቸው። የእነዚህ ዓይነቶቹ የተመሳሳይ ጥያቄዎች መደጋገም መጠናቸው ይነስ እንጂ በሌሎች ምዕራፎችም ውስጥ ተንጸባርቀዋል። የመመሳሰል ሁኔታም በብዛት የታየው አንድ ዓይነት ጉዳይን ደጋግሞ

በመጠየቅ ነው። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*ሠንጠረዥ 13፣ የክሂል መልመጃዎቹ ጥያቄዎች የቀረቡበት ስልት*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 21 | በክሂል መልመጃዎቹ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆኑና ድግግሞሽ የሚታይባቸው ናቸው። | 2 (20%) | 4 (40%) | - | 3 (30%) | 1 (10%) |
| 33 | የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ የተለያየና ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸውን ምላሾች የሚሹ ናቸው። | 3 (30%) | 4 (40%) | 2 (20%) | - | 1 (10%) |
| 34 | የክሂል መልመጃዎቹ ልዩ ልዩ የአጠያየቅ ስልቶችን የተከተሉ ናቸው። | 4 (40%) | 4 (40%) | - | 1 (10%) | 1 (10%) |

በጥያቄ ቁጥር 21፤ በክሂል መልመጃዎቹ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆኑና ድግግሞሽ የሚታይባቸው ናቸው፣ በሚል ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 2(20%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "አልስማማም" በማለት የመለሱት 3(30%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን ያሰፈሩት 1(10%) ናቸው።

ከመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በአብዛኞቹ የክሂል መልመጃዎች መካከል ተመሳሳይነትና መደጋገም የሚታይባቸው መሆኑን ነው። አጥኚውም ከመልመጃዎች ባሕርይ ምርመራ ያገኘው መረጃ የሚያመለክተው የመልመጃዎቹ ተመሳሳይነትና የመደጋገሙ ደረጃ በተወሰኑት ምዕራፎች እንዲሁም በተወሰነ ደረጃ የሚታይ መሆኑን ነው።

በሌላ በኩል በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙ የክሂል መልመጃዎች መካከል አብዛኞቹ የተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶችን የተከተሉና ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸውን ምላሾች የሚሹ ስለመሆናቸውም ተመርምረዋል። በዚህም መሠረት የክሂል ጥያቄዎቹ ያላቸው ልዩ ልዩ የአጠያየቅ ስልት ለምላሾቹ ቅርጽ መለያየት ምክንያት መሆናቸው ተመልክቷል። የጥያቄዎቹን አቀራረብ ስልቶች ስንመለከት ምንባቦችን ተመስርተው የቃል በቃል ምላሽ የሚሰጥባቸው፣ "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት የሚመለሱ፣ አማራጭ መልሶችን የያዙ፣ በቃላት ዓረፍተነገሮች እንዲመሰረቱ የሚያዙ፣ በቃል ወይም በጽሑፍ ማብራራትን የሚፈልጉ፣ ተማሪዎች እንዲነጋገሩ፣ እንዲወያዩ፣ እንዲከራከሩ፣ እንዲጨዋወቱ የሚጋብዙ፣ ካዳመጡት ጉዳይ ተነስተው በቃልና በጽሑፍ የሚመልሷቸው፣ አንቀጾችንና ድርሰቶችን እንዲጽፉ የሚያዙ፣ ወዘተ. መልመጃዎች መኖራቸው ተመልክቷል።

እነዚህን ጉዳዮች አስመልክቶ በጥያቄ ቁጥር 33፣ የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ የተለያየና ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸውን ምላሾች የሚሹ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምለሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 4(40%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ መጠይቁን የሞሉት 2(20%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን የሰፈሩት 1(10%) ናቸው።

እንዲሁም በጥያቄ ቁጥር 34፣ የክሂል መልመጃዎቹ ልዩ ልዩ የአጠያየቅ ስልቶችን የተከተሉ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 4(40%)፣ "እስማማለሁ" ያሉት 4(40%)፣ "አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 1(10%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ያሉት 1(10%) ናቸው።

በአጠቃላይ መምህራን ከሞሉት የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ የሚያመለክተው የክሂል መልመጃዎቹ የተለያዩ የአጠያየቅ ስልቶችን የተከተሉና ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸውን ምላሾች የሚሹ መሆናቸውን ነው። ይህን በሚመለከት አጥኚውም በመጽሐፉ ውስጥ በሚገኙ የክሂል መልመጃዎች ላይ ካከሄደው ምርመራ ለማረጋገጥ ችሏል። ስለሆነም የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ስልት ሲጤን ውስን እና ክፍት መጠይቆች ያሏቸው፣ ከቃል ደረጃ እስከ ድርሰት ያሉትን ምላሾች የሚፈልጉ፣ በግልና በጋራ የሚመለሱ፣ ወዘተ. ናቸው።

## 4.2. የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አደረጃጀት

ለአንድ የትምህርት ዓላማ ማሳኪያ እንዲሆኑ የሚመረጡ ይዘቶች የአደረጃጀት መርህን ተከትለው መደራጀት እንዳለባቸው ግልጽ ነው። በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች የተደራጁበትን ስልት የተወሰኑ መልመጃዎችን በምሳሌነት በመጠቀም እንደሚከተለው ማሳየት ይቻላል፤

በአሥሩም ምዕራፎች ላይ ያሉትን መልመጃዎች ስንመለከታቸው ወጥ በሆነ መልኩ በክፍል አንድ፡- ንባብ የሚሉ ሲሆኑ በእነዚህ ስር የቀረቡ ጥያቄዎች ተማሪዎቹ ካነበቧቸው ምንባቦች ተነስተው ቃል በቃል፣ "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት፣ ከቀረቡት አማራጮች መካከል በመምረጥ፣ ለቃላትና ሐረጋት አውዳዊ ፍች በመስጠት፣ በቃላት ዓረፍተነገሮችን በመመስረትና እንደነዚህ ባሉ ስልቶች የሚከናወኑ ናቸው።

በአምስት ምዕራፎች ውስጥ በክፍል ሁለት፣ በአምስት ምዕራፎች ውስጥ ደግሞ በክፍል ሦስት ስር የቀረቡ መልመጃዎች የንግግር ክሂልን ትኩረት ያደረጉ ሲሆን ከምንባቦቹ ውስጥ አወያይ ጉዳዮችን፣ ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸውን፣ ጭውውትን፣ አከራካሪ ነጥቦችን፣ ወዘተ. አስመልክተው ተማሪዎች እንዲወያዩ፣ እንዲነጋገሩ፣ እንዲጨዋወቱና እንዲከራከሩ፣ ወዘተ. የሚጋብዙ ናቸው፡፡

በአንድ ምዕራፍ ውስጥ በክፍል ሦስት ስር፣ በሁለት ምዕራፎች ውስጥ በክፍል ሁለት ስር የቀረቡ መልመጃዎች ማዳመጥን በርዕስነት የያዙ ናቸው፡፡ የመልመጃዎቹም ተማሪዎች አዳምጠው ማስታወሻ እንዲይዙ፣ ስላዳመጡት ነገር ለጓደኛቸው እንዲናገሩ፣ ያዳመጡትን ጉዳይ ተንተርሰው ጥያቄዎችን እንዲመልሱ፣ ባዳመጡት መሠረት ገላጭና ተገላጭን እንዲያዛምዱ፣ ወዘተ. የሚያዙ ናቸው፡፡

በሦስት ምዕራፎች ውስጥ በክፍል አራት ስር፣ በአራት ምዕራፎች ውስጥ በክፍል ሦስት ስር እንዲሁም በሦስት ምዕራፎች ውስጥ በክፍል ሁለት ስር የቀረቡት መልመጃዎች የጽሕፈት ክሂልን ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡ የመልመጃዎቹም ባሕርይ ተማሪዎቹ ያነበቧቸውን ምንባቦች መሠረት አድርገው ሠንጠረዥ እንዲሞሉ፣ አንብበው ማስታወሻ እንዲይዙ፣ ከተሰጣቸው ርዕሰ-ጉዳዮች መካከል አንዱን መርጠው አንቀጽ እንዲጽፉ፣ ከምንባቦቹ በተወጣጡ ቃላት ዓረፍተነገሮችን እንዲመሠርቱ፣ ከምንባቦቹ የተወሰዱ ሐሳቦችን በራሳቸው አባባል አብራርተው እንዲጽፉ፣ ዓረፍተነገሮችን በአያያዥ ቃላት እንዲያይዙ፣ በጽሑፍ ውስጥ ሥርዓተ-ነጥቦችን በተገቢ ቦታቸው እንዲያስገቡ፣ ወዘተ. የሚያዙ ናቸው፡፡

ከላይ በዝርዝር የተገለጹትን የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎችን አደረጃጀት በአጭሩ ከሚከተለው ሠንጠረዥ መመልከት ይቻላል፡፡

*ሠንጠረዥ 14፣ የክሂል ርዕሶች በመጽሐፉ ውስጥ ያላቸው አደረጃጀት*

| ክፍል | ም.1 | ም.2 | ም.3 | ም.4 | ም.5 | ም.6 | ም.7 | ም.8 | ም.9 | ም.10 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| አንድ | ንባብ | ንባብ | ንባብ | ንባብ | ንባብ | ንባብ | ንባብ | ንባብ | ንባብ | ንባብ |
| ሁለት | ንግግር | ንግግር | ማዳመጥ | ማዳመጥ | ንግግር | ንግግር | ጽሕፈት | ጽሕፈት | ንግግር | ጽሕፈት |
| ሦስት | ማዳመጥ | ጽሕፈት | ንግግር | ንግግር | ጽሕፈት | ጽሕፈት | ጽሕፈት | ንግግር | ጽሕፈት | ንግግር |
| አራት | ጽሕፈት | - | ጽሕፈት | ጽሕፈት | - | - | - | - | - | - |

ከላይ ከቀረቡት ሐሳቦችም ሆነ ከዚህ ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የክሂሎች ይዘትና መልመጃዎች በተለይ ከንባብ ክሂል ውጭ ያሉት ወጥ የሆነ የአደረጃጀት ቅርጽ የሌላቸው፣ በፈለጉ ጊዜ ባሻቸው ቦታ ላይ ብቅ ብለው በፈለጉ ጊዜ ደግሞ

የሚጠፉ መሆናቸውን ነው። ይህም በመሆኑ የክሂሎች ይዘትና መልመጃዎች አደረጃጀት ተከታታይነት ወጥ በሆነ መልኩ እንዳልሆነ፣ የክሂሎች የክብደት ደረጃና ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል የሚታይበት አለመሆኑን መረዳት ይቻላል።

የተለጣጣቂነት ጉዳይ ሲነሳ በአንድ ምዕራፍም ሆነ በተከታታይ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ የትምህርት ይዘቶች በስፋትም ሆነ በጥልቀት አንዱ ከሌላኛው ላቅ ብሎ የሚታይበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው። በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶች ግን ይህ ባሕርይ ይታይባቸዋል ለማለት አያስደፍርም፤ ምክንያቱም በተለያዩ ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙ መልመጃዎች ተመሳሳይ ተግባራትን የሚያዙ በመሆናቸው ነው። ከምሳሌ ያህል "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት የሚመለሱ፣ ምርጫ ያላቸው፣ ቃል በቃል የሚመለሱ፣ አውዳዊ ፍቺ የሚፈልጉ፣ በቃላት ዓረፍተነገሮችን እንዲመሠርቱ የሚያዙ፣ ወዘተ. ጥያቄዎች ከሞላ ጎደል በሁሉም ምዕራፎች ውስጥ ስለሚገኙ ነው።

ውህደትን በሚመለከት የቋንቋ ክሂሎች በተፈጥሮ ብቻቸውን የማይቆሙና እርስ በርሳቸው የሚደጋገፉ በመሆናቸው በብዙ ቦታዎች ላይ ተዋህደው መቅረባቸው ተስተውሏል። ይህም የሆነው ተማሪዎቹ ካነበቡት ምንባብና ካዳመጡት ነገር ተነስተው ጥያቄዎችን ለመመለስ ንግግርን ወይም ጽሕፈትን እንዲጠቀሙ በብዙ ቦታዎች የሚያዝ በመሆኑ ነው። ለዚህም ማሳያ እንዲሆን ከብዙዎቹ መካከል የተወሰኑትን ማቅረብ ይቻላል።

ምሳሌ 1. በመጽሐፉ ምዕራፍ አምስት ገጽ 85፣ ክፍል ሦስት፡- ጽሕፈት፣ መልመጃ 1 "የሚከተለውን ግጥም ዜማውን ጠብቃችሁ በጥሞና *አንብቡና* 'እሱ' የተባለው ሰው ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለው፣ እንዲህ ዓይነት ባሕርይ የቱን ያህል ጎጂ እንደሆነ *ጽፋችሁ* ለክፍል አቅርቡ። ባቀረባችሁት ላይም *ተወያዩ*፣

ምሳሌ 2. ምዕራፍ ሰባት፣ ገጽ 127፤ መልመጃ አንድ "የአካባቢ እንክብካቤን አለዚያም ሌሎች አካባቢያዊ ጉዳዮችን አስመልክቶ የሚደረጉ ውይይቶችን፣ ማብራሪያዎችንና ገለጻዎችን *አዳምጣችሁ ማስታወሻ በመያዝ* በራሳችሁ አባባል *በጽሑፍ አዘጋጁ*። በጽሑፍ ያዘጋጃችሁትንም ለክፍላችሁ *በንግግር አቅርቡ*"፤ የሚሉ ይገኙበታል። ይህንኑ ለማረጋገጥ ለቀረበላቸው ጥያቄ መምህራን የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

*ሠንጠረዥ 15፣ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አደረጃጀት*

| ተ/ቁ | አስተያየት | በጣም እስማማለሁ | እስማማለሁ | ለመወሰን እቸገራለሁ | አልስማማም | ፈጽሞ አልስማማም |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች የአደረጃጀት መርህን (ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትንና ውህደትን) የተከተሉ ናቸው። | 2 (20%) | 1 (10%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 2 (20%) |
| 23 | በክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት ሂደት አራቱም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርስ ተዋህደው ቀርበዋል። | 3 (30%) | 4 (40%) | 2 (20%) | - | 1 (10%) |
| 6 | የመልመጃ ጥያቄዎቹ አቀማመጥ የክብደት ደረጃ ቅደም ተከተል አላቸው። | 2 (20%) | 1 (10%) | 2 (20%) | 3 (30%) | 2 (20%) |
| 22 | የመልመጃዎቹ አቀራረብ የቋንቋ ክሂሎችን ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) የጠበቁ ናቸው። | 2 (20%) | 2 (20%) | 1 (10%) | 2 (20%) | 3 (30%) |

በጥያቄ ቁጥር 10፣ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች የአደረጃጀት መርህን (ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትንና ውህደትን) የተከተሉ ናቸው፣ ተብሎ ለመምህራን ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 2(%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 1(10%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት የገለጹት 2(20%)፣ "አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 3(30%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ያሉት 2(20%) ናቸው። ይህ የአሃዝ መረጃ የሚያመለክተው የክሂል ይዘቶቹ በአብዛኛው የአደረጃጀት መርህ ተከትለው የተዘጋጁ አለመሆናቸውን ነው።

በጥያቄ ቁጥር 23፣ በክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት ሂደት አራቱም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርስ ተዋህደው ቀርበዋል፣ በሚል ለመምህራን ለቀረበላቸው የጽሑፍ መጠይቅ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 3(30%)፣ "እስማማለሁ" በማለት የመለሱት 4(40%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" በማለት የገለጹት 2(20%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ሲሉ ምላሻቸውን የሰጡት 1(10%) ናቸው። ከዚህ የአሃዝ መረጃ መገንዘብ የሚቻለው የቋንቋ ክሂሎቹ በአብዛኛው እርስ በርስ ተዋህደው መቅረባቸውን ነው።

በጥያቄ ቁጥር 6፣ የመልመጃ ጥያቄዎቹ አቀማመጥ የክብደት ደረጃ ቅደም ተከተል አላቸው ተብሎ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 2(20%)፣ "እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 1(10%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ያሉት 2(20%)፣ "አልስማማም" በማለት ምላሻቸውን የሰጡት 3(30%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ብለው መጠይቁን የሞሉት 2(20%) ናቸው። ይህ የአሃዝ መረጃ የሚጠቁመው የክሂል መልመጃ

ጥያቄዎቹ የክብደት ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ቀርበዋል ለማለት የሚያስደፍር ነገር እንደሌላቸው ነው፡፡

በጥያቄ ቁጥር 22፣ የመልመጃዎቹ አቀራረብ የቋንቋ ክሂሎችን ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) የጠበቁ ናቸው፣ ተብሎ ለተነሳላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ እንደሚያመለክተው "በጣም እስማማለሁ" ያሉት 2(20%)፣ "እስማማለሁ" ሲሉ የመለሱት 1(10%)፣ "ለመወሰን እቸገራለሁ" ሲሉ መጠይቁን የሞሉት 2(20%)፣ "አልስማማም" በማለት የመለሱት 2(20%) ሲሆኑ "ፈጽሞ አልስማማም" ያሉት ደግሞ 3(30%) ናቸው፡፡

በአጠቃላይ እነዚህ ከላይ የቀረቡት የአሃዝ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ከአደረጃጀት መርህ (ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነትና ውህደት) እና ከክሂሎች ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል አኳያ መስተካከል ያለባቸው በርካታ ጉዳዮች መኖራቸውን ነው፡፡ አጥኚውም እነዚህን ጉዳዮች በሚመለከት ምርመራ ባካሄደበት ወቅት በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች ከአደረጃጀት አንጻር ቀደም ሲል እንደተገለጸው በርካታ ችግሮች መኖራቸውን ለመረዳት ችሏል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ

## 5.1 ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ እንደተጠቀሰው የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በ2004 ዓ.ም. በተዘጋጀው የዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱት የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት በመተንተን ድክመታቸውንና ጥንካሬያቸውን ማሳየት ነው፡፡

በዚህ መሠረት ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች በውስጡ ማካተቱም ተጠቁሟል፡፡ እነሱም፡-

1. አራቱን የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) የሚመለከቱ ይዘቶችና መልጃዎችን አቀራረብ መፈተሽ፣
2. ይዘቶቹና መልመጃዎቹ ለአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ያላቸውን የስርጭት መጠን መመርመር፣
3. የክሂል መልጃዎቹ ለተማሪዎቹ ከክፍል ውስጥ የመማር ተግባራት ባሻገር ላላቸው የቋንቋ ልምምድ የሚኖራቸውን አስተዋጽኦ ማጤን፣ እና
4. የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ የተደራጁበትን ስልት መገምገም

ናቸው፡፡

ለጥናቱ የተመረጠው በአሁኑ ወቅት እየተሰራበት ያለው የዘጠነኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መመሪያ መጽሐፍ ሲሆን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹም ሰነድ ፍተሻ እና የመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው፡፡ ለዚህም እንዲያመች መጽሐፉ በውስጡ አካቶ የያዛቸውን አራቱንም የቋንቋ ክሂል ይዘቶች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብና መጻፍ) ከተለያዩ ንድፈሐሳባዊ ቅኝቶች አንጻር ለመቃኘት ጥረት ተደርጓል፡፡

ይህ ክፍል ደግሞ በሰነድ ምርመራና በመምህራን የጽሑፍ መጠይቅ አማካይነት የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነው ባስገኙት ውጤት መሠረት ማጠቃለያና የመፍትሔ ሐሳብ የቀረበበት ነው። በዚህ መሠረት በጥናቱ ሂደት ከመረጃ ትንተና የተገኙ ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት የክሂል ይዘቶች ለመማር-ማስተማሩ ሂደትም ሆነ ለተማሪዎቹ የክሂል ልምምድ አመቺ ናቸው፤ ለዚህም በምክንያትነት የተጠቀሰው መልመጃዎቹ በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜና በድኅረ ንባብ ጊዜ ለሚከናወኑ የቋንቋ ክሂሎች ልምምድ በሚመች መልኩ ተከፋፍለው በመቅረባቸው ነው።
- የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ያለመጣጣም ችግሮች መኖራቸውን መረጃዎች አመልክተዋል። የክሂል መልመጃዎቹን መጽሐፉ በሚያዘው መሠረት ለመተግበር ጥረት በሚደረግበት ወቅት ሰዓቱ ቀድሞ እንደሚጠናቀቅና በዚህም ምክንያት ሊዘለሉ የሚችሉ ይዘቶች እንደሚኖሩ አሊያም የተወሰኑ ተማሪዎች ብቻ እንዲሳተፉ እንደሚደረግ መገንዘብ ተችሏል።
- በመጽሐፉ ውስጥ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች መካከል አብዛኞቹ አንጻራዊ በሆነ መልኩ በበቂ ደረጃ የመቅረባቸውን ያህል የማዳመጥ ክሂል ከመለማመጃ ጥያቄዎች ጋር በበቂ ሁኔታ ተካተው አልቀረበም።
- ለክሂል መልመጃዎች ከቀረቡት መመሪያዎች መካከል የመለማመጃ ጥያቄዎቹ በምን መልኩ እንደሚተገበሩ የተሟላ መረጃ የሚሰጡ የመኖራቸውን ያህል ስለመልመጃዎቹ አሰራር ሙሉ መረጃ የማይሰጡ መመሪያዎች በመጽሐፉ ውስጥ እንደሚገኙ ማረጋገጥ ተችሏል።
- በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡ የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብ የተማሪዎችን ደረጃ፣ ዕድሜና ችሎታ መሠረት ያደረገ እንዲሁም ዳራዊ ዕውቀታቸውን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው።
- የክሂል መልመጃዎቹ በመምህራንና በተማሪዎች ተግባራዊ የሚደረጉ፣ መምህሩም እንዲያስተምር፣ ተማሪውም እንዲማር በሚያስችል መልኩ በግልጽ ቋንቋ የቀረቡ እንዲሁም ለክሂሎች ልምምድ የቀረቡ ይዘቶችም ቢሆኑ በቋንቋው ተናጋሪ ኅብረተሰብ ዘንድ የተለመዱና የተማሪዎችን አካባቢያዊና ባህላዊ ጉዳዮች ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ናቸው።

- ለቋንቋ ክሂሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃት ያላቸው ናቸው። ለያንዳንዱ ክሂል የቀረቡ መልመጃዎች በመጠን የተለያዩ ቢሆኑም ተማሪዎቹ ለሚያካሄዱት የክሂሎች ልምምድ ጉልህ ፋይዳ ያላቸው ናቸው።
- የቋንቋ ክሂሎች በተገቢ የማስተማሪያ ብልሃቶችና ዘዴዎች ታግዘው ከመቅረብ አንጻር ሲታዩ መጠነኛ ልዩነቶች ታይተዋል። የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በቴፕ፣ በቴሌቪዥን እና በልዩ ልዩ ባለሙያዎች (በእንግዳ ሰዎች) ንግግር ታግዘው አልቀረቡም። የንግግር ክሂል መልመጃዎች በበቂና በተለያዩ ዘዴዎች (ለምሳሌ በውይይት፣ በጭውውት፣ በክርክርና በቃላዊ ሪፖርት፣) አማካይነት ታግዘው ቀርበዋል። የንባብ ክሂልም ቢሆን በአብዛኛው "ጥያቄ መጠየቅ" በሚለው ብልሃት የቀረበ ሲሆን "ማብራራትና መተርጎም" እንዲሁም "አንደምታና ትንበያ" አልፎ አልፎ ጥቅም ላይ ውለዋል። በአንጻሩም "ማጠቃለል" የተባለው ዘዴ የትም ቦታ ላይ ጥቅም ላይ ሲውል አልተስተዋለም። የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች ምንም እንኳን መጠናቸው ውስን ቢሆንም በውጤታዊና በሂደታዊ የጽሕፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴዎች ታግዘው ቀርበዋል፤ ነገር ግን በውጤታዊ ዘዴ የቀረቡት መልመጃዎች ለቁጥጥር ጽሕፈት ስልት (controlled writing) ብቻ ትኩረት የሰጡና ለመር ጽሕፈት (guided writing) እና ለነጻ ጽህፈት (free writing) ስልቶች ምንም ዓይነት ትኩረት ያልሰጡ ናቸው።
- የክሂል መልመጃዎች በባሕርያቸው ተማሪዎች በግል፣ በጥንድና በቡድን ለሚያካሄዷቸው የቋንቋ ክሂል ልምምዶች ጉልህ ሚና ያላቸው ናቸው። ከዚህ ጎን ለጎን መልመጃዎቹ ተማሪዎቹን በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ላሉ የቋንቋ ክሂሎች አጠቃቀም የመጋበዝ አቅም ያላቸው ናቸው።
- የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙትን ምንባቦች ተከትለው የተዘጋጁ እንጂ ሳይንሳዊ የይዘት አደረጃጀት መርህን (ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት እና ውህደት) መሠረት አድርገው በጥንቃቄ የተዘጋጁ አይደሉም። በመሆኑም የክሂል ይዘቶቹ ወጥነት ባለው መልኩ ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል ያልያዙ እንዲሁም መልመጃዎቹ የክብደት ደረጃ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ያልተደራጁ ናቸው።

## 5.2 የመፍትሔ ሐሳቦች

በጥናቱ ውጤት ላይ በመመሥረት በክሂል ይዘቶቹ ላይ በደካማ ጎንነት ለተነሱ ነጥቦች አጥኚው የሚከተሉትን አስተያየቶች በመፍትሔነት አቅርቧል፤

- የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር እንዲጣጣሙ ለማድረግ ተመሳሳይ ባሕርይ ያላቸውንና የሚደጋገሙ ጥያቄዎችን ማስቀረት፣ የምርጫ እና የ"እውነት"፣ "ሐሰት" ጥያቄዎችን መጠን ማሳነስ እንዲሁም ከተቻለም የክፍለ ጊዜ መጠን ማድረግ፣
- ለሌሎች ክሂሎች የተሰጠውን ያህል የማዳመጥ ክሂልም ትኩረትና በቂ ሽፋን ተሰጥቶት እንዲሁም በተገቢ የመለማመጃ ጥያቄዎች ታግዞ እንዲቀርብ ማድረግ፣
- በመጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት ሁሉም የክሂል መልመጃዎች ምላሽ ስለሚሰጥባቸው ሁኔታ የተሟላ መመሪያዎች እንዲኖራቸው ማድረግ፣
- ሁሉም የቋንቋ ክሂሎች በተገቢ የማስተማሪያ ብልሃቶችና ዘዴዎች ታግዘው እንዲቀርቡ ማድረግ፤ ለምሳሌ የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በቴፕ፣ በቴሌቪዥን፣ በልዩ ልዩ ባለሙያዎች (በእንግዳ ሰዎች) ንግግር ወዘተ.፣ የንባብ ክሂል በማብራራትና መተርጎም፣ በአንደምታና ትንበያ እንዲሁም በማጠቃለል ዘዴዎች፣ ወዘተ. የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎች በውጤታዊና በሂደታዊ ዘዴዎች እንዲታገዙ እንዲሁም ውጤታዊ ዘዴ በቁጥጥር (controlled writing)፣ በመር (guided writing) እና በነጻ (free writing) የጽሕፈት ስልቶች እንዲታገዙ ማድረግ፣
- የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች በመጽሐፉ ውስጥ ከሚገኙት ምንባቦች ጎን ለጎን ሳይንሳዊ የይዘት አደረጃጀት መርህን (ተከታታይነት፣ ተለጣጣቂነት እና ውህደት) ተከትለው እንዲዘጋጁ፣ የክሂል ይዘቶቹ ወጥነት ባለው መልኩ ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተላቸውን ይዘው እንዲሁም መልመጃዎቹ የክብደት ደረጃ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው እንዲደራጁ ማድረግ፣

የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ እንደሚያስችሉ አጥኚው ያምናል።

## ዋቢ ምንጮች


ሃና ታምራት። "በሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የአማርኛ ጽሕፈት ክሂል II ኮርስ የአቀራረብና የአተገባበር ፍተሻ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ፣ ሰኔ 2003 ዓ.ም።

መስፍን ደፈረሱ። "በአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ መልመጃዎች ይዘትና አዘገጃጀት ግምገማ 11ኛ እና 12ኛ ክፍል ተተኳሪነት።" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ትምህርት ክፍል አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ስነዘዴ ለሁለተኛ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት። አዲስ አበባ፣ ሰኔ 2000 ዓ.ም።

በየነ ማሞ። "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች የቋንቋውን ክሂሎች የሚያዳብሩ ናቸው?" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። አዲስ አበባ፣ ሰኔ 1985 ዓ.ም።

በድሉ ዋቅጅራ። <u>በስነ-ጽሑፍ ቋንቋን ማስተማር</u>። አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 1996 ዓ.ም።

ባየ ይማም። <u>የአማርኛ ሰዋስው የተሻሻለ ሁለተኛ እትም</u>። አዲስ አበባ፤ እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ. ማህበር፣ 2000 ዓ.ም።

ተስፋዬ ሸዋዬ። "ስነ-ልሳንና ቋንቋን ማስተማር።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ጽሑፍ ክፍል። አዲስ አበባ፣ 1981 ዓ.ም። (ያልታተመ)።

አለም እሼቴ። "በሁለተኛ ቋንቋ የማስተማሪያ ዝግጅት ሂደት ውስጥ የክሂሎች አደረጃጀትና ትኩረት የሚሹ ይዘቶች አወቃቀር።" ከጥቅምት 25 — 29/1995 ዓ/ም ለአማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የተዘጋጀ የ7ኛና የ8ኛ ክፍሎች መርሀ ትምህርቶችን ለማሻሻል ለተዘጋጀው አውደጥናት የቀረበ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የስርዓተ ትምህርት ዝግጅት ጥናትና ምርምር እንስቲትዩት፣ 1995 ዓ.ም። (ያልታተመ)።

አንለይ ጣሴ። "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የጽሕፈትን ክሂል ለማዳበር መልመጃዎች እንዴት መቅረብ አለባቸው?" በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ክፍል ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ። አዲስ አበበ ዩኒቨርሲቲ፣ ሰኔ 1987 ዓ.ም.

አያልሰው ይታየው። "ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ባሉ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት ውስጥ በሚገኙ የልቦለድ ምንባቦች ስር የሚገኙ የመናገር ክሂል ይዘቶች አቀራረብ ትንተናና ግምገማ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቋንቋዎች ጥናት ፋኩልቲ የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ ትምህርት መርሀ ግብር በተግባራዊ ስነ-ልሳን አማርኛን ለማስተማር ኤም.ኤ. ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት። አዲስ አበባ፣ 2003 ዓ.ም።

እቴነሽ ተገኝ። "በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መርሀ ትምህርት ውስጥ የማዳመጥን ክሂል ለማዳበር የቀረቡ ይዘቶች ትንተናና ግምገማ።" ለድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የቀረበ ቴሰስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አማርኛን በማስተማር ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ። አዲስ አበባ፣ ሰኔ 1986 ዓ.ም።

ወንድወሰን በየነ። "የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሀዲይኛ የሆነ የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና የፈተና ውጤታቸው ዝምድና።" በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት በቋንቋዎች ጥናት ተቋም አማርኛን በማስተማር ዘዴ ለማስተርስ ዲግሪ መሟያ የቀረበ ጽሑፍ። አዲስ አበባ፣ ግንቦት 1989 ዓ.ም።

የሺጥላ ምንይልሸዋ። "በ9ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ አንብቦ የመረዳት ትምህርት አቀራረብ ግምገማ።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር ለአማርኛ ማስተርስ (TEAM) ኤም.ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ። አዲስ አበባ፣ ሰኔ 2000 ዓ.ም።

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር። <u>አማርኛ የተማሪ መጽሐፍ 9ኛ ክፍል</u>። አዲስ አበባ፤ ኩራዝ እንተርናሽናል አሳታሚ ኃ/የተ/የግ/ማህበር፣ 2004 ዓ.ም።

ያለው እንዳወቀ ሙሉ። <u>የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር</u>። ባህር ዳር፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ 2004 ዓ.ም።

Anderson, A & Lynch, T. Listening. Language Teaching: A Scheme for Teacher Education. New York: Oxford University Press, 1988.

Bygate, M. Speaking. New York: Oxford University Press, 1987.

Byrne, D. Teaching Writing Skills. London: Longman Group UK Limited, 1988.

Davies, F. Introducing Writing. London: Penguin Books Ltd. 1995.

Dawson, A. and etal. Fundamentals of Basic Reading Instructions. New York: D...Mackay, Co, 1963.

Doff, A. Teach English: A Trainning course for Teachers. New York: Cambridge University press, 1988.

Gomez, R. and etal eds. Pragmatics Applied to Language Teaching and Learning. Cambridge: Cambridge Scholars Publishing, 2009.

Grant, N. Making the Most of Your Textbook. New York: Longman Ink. 1987.

Greenall, S. & Swan, M. Effective Reading. Reading Skills for Advanced Students. Cambridge: Cambridge University Press, 1986.

Grellete, F. Developing Reading Skills. Cambridge University Press, 1981.

Hedge, T. Writing. Resource books for Teachers. Hong Kong: Oxford University Press, 1988.

Hutchinson, T. & Torres, E. The Textbook as Agent of Change. ELT Jornal, Volume 48, Issue 4, 1994.

Jamse, Mc. Writing With a Purpose. 3rd ed. New York: Houghton Mifflin Press, 1863.

Jordan, R.R. Academic Writing Course. London: Butter and Tanner Ltd. 1980.

Lewis, M. & Hill, J. Practical Techniques for Languge Teaching. London: Commericial Colour Press, 1985.

Littlejohn, A. Writing. Cambridge Skills for Fluency. Cambridge: Cambridge University Press, 1993.

Nunan, D. Designing Tasks for the Communicative Classroom. New York: Cambridge University Press, 1989.

Nuttall, Ch. Teaching Reading Skills in foreign Languages. London: Heinemann Educational Books Ltd. 1982.

Pincas, A. Teaching English Writing. Hong Kong: Macmillan publisher Ltd. 1982.

Raimes, A. Techniques in Teaching Writing. Oxford: Oxford University Press, 1983.

Rexon, S. Developing Listening Skills. Hong Kong: Macmillan University Press, 1986.

Richards, J.C. The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press, 1990.

Smith, F. Reading. 2nd ed. Camridge: Cambridge University Press, 1987.

Underwood, M. Teaching Listening. New York: Longman Group UK Limited, 1989.

Ur, P. A Course In Language Teaching: Practice and Theory 13th Printing. Cambridge: Cambridge University, 2006.

Widdowson, H. G. Teaching Language as Communication. New York: Oxford University Press, 1978.

Williams, Ed. Reading in the Language Classroom. London: Macmillan Publishers Ltd. 1984.

# አባሪዎች

## አባሪ አንድ

### በመምህራን የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ፤

**ውድ መምህር፡-** የዚህ መጠይቅ ዋና አላማ በ2004 ዓ.ም. ለዘጠነኛ ክፍል በተዘጋጀው የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱ የቋንቋ ክሂሎችን የሚመለከቱ ይዘቶችና መልመጃዎች አቀራረብና አደረጃጀት ምን መልክ እንዳላቸው ለመገምገም የሚያስችል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ጥናቱ ግቡን እንዲመታ የእርስዎ አስተዋጽኦ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ ስለዚህ ጥያቄዎቹን በጥንቃቄ አንብበው ትክክለኛ ምላሽ እንዲሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ውድ ጊዜዎትን መስዋዕት በማድረግ መጠይቁን ስለሚሞሉ በቅድሚያ አመሰግናለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡- ስም መጻፍ አስፈላጊ አይደለም፡፡

**ክፍል አንድ፡-** ክፍት ቦታዎችን በተገቢ መረጃ ይሙሉ፡፡

1. ፆታ ..............................................
2. የትምህርት ደረጃ ..............................
3. የአገልግሎት ዘመን ..........................
4. የሰለጠኑበት የትም/ት ዓይነት ..............
5. የምያስተምሩበት ት/ቤት ......................

**ክፍል ሁለት፡-** ከዚህ ቀጥሎ ለቀረቡ ጥያቄዎች በመመዘኛ መስፈርቶቹ ላይ በተገለጹ መገለጫዎች አማካይነት ተገቢ ነው የምሉትን ምላሽ የ"X" ምልክት በማድረግ ያመልክቱ፡፡

*የመመዘኛ መሥፈርቶቹ መግለጫ፡-* 5. በጣም እስማማለሁ 4. እስማማለሁ 3. ለመወሰን እቸገራለሁ 2. አልስማማም 1.ፈጽሞ አልስማማም

| ተ/ቁ | የጽሑፍ መጠይቆች | 5 | 4 | 3 | 2 | 1 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የክሂል መልመጃዎቹ አዘገጃጀትና አቀራረብና ለመማር ማስተማሩ ሂደት አመቺ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 2 | የክሂል መልመጃዎቹ ተገቢ የሆኑና ተሟልተው የቀረቡ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 3 | የመልመጃዎቹ አቀራረብ ለትምህርቱ ከተመደበው ሰዓት ጋር ተጣጣሚነት አላቸው፡፡ | | | | | |
| 4 | መልመጃዎቹ ለክሂሎች ልምምድ አመቺ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 5 | አራቱም የቋንቋ ክሂሎች በመልመጃዎቹ ላይ በእኩል ደረጃ ቀርበዋል፡፡ | | | | | |
| 6 | የመልመጃ ጥያቄዎቹ አቀማመጥ የክብደት ደረጃ ቅደም ተከተል አላቸው፡፡ | | | | | |
| 7 | እያንዳንዱ የክሂል ይዘት በተገቢ የመለማመጃ ጥያቄዎች ታግዞ ቀርቧል፡፡ | | | | | |
| 8 | ለክሂል መልመጃዎቹ ተገቢ የሆኑ መመሪያዎች ተሰጥተዋል፡፡ | | | | | |
| 9 | የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ ማራኪነትና ሳቢነት አላቸው፡፡ | | | | | |
| 10 | የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎች የአደረጃጀት መርህን (ተከታታይነትን፣ ተለጣጣቂነትንና ውህደትን) የተከተሉ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 11 | የክሂል ይዘቶችና መልመጃዎቹ ለደረጃው ተማሪዎች የሚመጥኑ ናቸው፡ | | | | | |
| 12 | የክሂል መልመጃዎቹ ከተማሪዎቹ እድሜ፣ ችሎታና ፍላጎት ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 13 | የክሂል መልመጃዎቹ የተማሪዎቹን ዳራዊ ዕውቀት ከግንዛቤ ውስጥ ያስገቡ ናቸው፡፡ | | | | | |
| 14 | የክሂል መልመጃዎቹ በመምህራንና በተማሪዎች ተግባራዊ የሚደረጉ ናቸው፡፡ | | | | | |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | በመጽሐፉ ውስጥ የተካተቱት የክሂል ይዘቶች በሙሉ መምህሩ እንዲያስተምር፣ ተማሪውም እንዲማር በሚያስችል መልኩ በግልጽ ቋንቋ ቀርበዋል። | | | | | |
| 16 | ተማሪው እንዲማረውና እንዲለማመደው የቀረበው የቋንቋ አካል (ይዘት) በቋንቋው ተናጋሪ ኅብረተሰብ ዘንድ የተለመደ ነው። | | | | | |
| 17 | ለእያንዳንዱ ክሂል ማስተማሪያ እንዲሆኑ የተዘጋጁት መልመጃዎች የትምህርቱን ዓላማ የማሳካት ብቃት አላቸው። | | | | | |
| 18 | የክሂል ይዘቶቹ ተማሪዎቹ ቋንቋውን በሚገባ እንዲካኑ የማድረግ አቅም ያላቸው ናቸው። | | | | | |
| 19 | የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ የተማሪዎችን በጥንድና በቡድን የመማር ሂደት የሚያበረታቱ ናቸው። | | | | | |
| 20 | መጽሐፉ አራቱንም የቋንቋ ክሂሎች ለማስተማር የሚያስችሉ በቂ ይዘቶችን አሟልቶ ይዟል። | | | | | |
| 21 | በክሂል መልመጃዎቹ ውስጥ የቀረቡ ጥያቄዎች ተመሳሳይ የሆኑና ድግግሞሽ የሚታይባቸው ናቸው። | | | | | |
| 22 | የመልመጃዎቹ አቀራረብ የቋንቋ ክሂሎችን ተፈጥሯዊ ቅደም ተከተል (ማዳመጥን፣ መናገርን፣ ማንበብንና መጻፍን) የጠበቁ ናቸው። | | | | | |
| 23 | በክሂል መልመጃዎች አዘገጃጀት ሂደት አራቱም የቋንቋ ክሂሎች እርስ በርስ ተዋህደው ቀርበዋል። | | | | | |
| 24 | የማዳመጥ ክሂል መልመጃዎች በልዩ ልዩ የማስተማሪያ ዘዴዎች ተደግፈዋል (ለምሳሌ በቴፕ፣ በቴሌቭዥን፣ በሰዎች ንግግር፣ ወዘተ.)። | | | | | |
| 25 | የንግግር ክሂል መልመጃዎች የተለያዩ ስልቶችን ተከትለው ተዘጋጅተዋል (ለምሳሌ ጭውውት፣ ክርክር፣ ቃላዊ ሪፖርት፣ ወዘተ.)። | | | | | |
| 26 | የንባብ ክሂል መልመጃዎች ለክሂሉ ማስተማሪያ የሚሆኑ ብልሃቶችን መሠረት ያደረጉ ናቸው (ለምሳሌ ጥያቄ መጠየቅ፣ ማብራራትና መተርጎም፣ ማጠቃለል እና አንድምታና ትንበያ)። | | | | | |
| 27 | የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ ውጤታዊና ሂደታዊ የጽሕፈት ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተከትለው የተዘጋጁ ናቸው። | | | | | |
| 28 | ይህን በሚመለከት በጥያቄ ቁጥር 28 የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ በቁጥጥር ጽሕፈት /controlled writing/፣ በመር ጽሕፈት /guided writing/ እና በነፃ ጽሕፈት /free writing/ ስልት ተለይተው ቀርበዋል። | | | | | |
| 29 | የጽሕፈት ክሂል መልመጃዎቹ ተማሪዎች ሐሳባቸውን በወረቀት ላይ በማስፈር መግባባት እንዲችሉ የሚያደርጉ ናቸው። | | | | | |
| 30 | የክሂል መልመጃዎቹ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ለሚደረጉ የቋንቋ ልምምዶች የሚጋብዙ ናቸው። | | | | | |
| 31 | በክሂል መልመጃዎቹ ላይ የቀረቡ ይዘቶች ከተማሪዎቹ አካባቢያዊና ባህላዊ ጉዳዮች ጋር ዝምድና ያላቸው ናቸው። | | | | | |
| 32 | የክሂል መልመጃዎቹ አዘገጃጀት ተማሪዎች ቋንቋውን በገሃዱ ዓለም ሲጠቀሙበት በሚያስችላቸው መልኩ ነው። | | | | | |
| 33 | የክሂል መልመጃዎቹ አቀራረብ የተለያየና ልዩ ልዩ ቅርጽ ያላቸውን ምላሾች የሚሹ ናቸው። | | | | | |
| 34 | የክሂል መልመጃዎቹ ልዩ ልዩ የአጠያየቅ ስልቶችን የተከተሉ ናቸው። | | | | | |

ክፍል ሦስት፡- ለሚከተሉት ክፍት የጽሑፍ መጠይቆች ዘርዘር ያለ ምላሽ ይስጡ።

1. አራቱንም የቋንቋ ክሂል መልመጃዎች መጽሐፉ በሚያዘው መሠረት ለማስተማር አመቺ ነው? ..............................
   ለምን? ..............................
   ..............................
   ..............................

2. በመጽሐፉ ውስጥ ከቀረቡ የክሂል መልመጃዎች መካከል ምላሽ ሳይሰጥባቸው የሚታለፉ አሉ? ..............................

3. የሚዘለሉ መልመጃዎች ካሉ ምክንያቱ ምን ሊሆን ይችላል?
   ..............................
   ..............................
   ..............................

4. መጽሐፉ ከአራቱም የቋንቋ ክሂሎች መካከል በይበልጥ ትኩረት የሚሰጠው ክሂል አለ?
   ..............................
   ..............................
   ..............................

5. ለጥያቄ ቁጥር 4 መልስዎ "አዎን" የሚል ከሆነ ለየትኛው ክሂል ነው? ..............................
   ምን ማረጋገጫ አለዎት? ..............................
   ..............................
   ..............................
   ..............................

6. በክሂል መልመጃዎቹ አደረጃጀትና አቀራረብ ላይ መሻሻል አለባቸው የሚሏቸው ነጥቦች አሉ? ..............................

7. ለጥያቄ ቁጥር 6 መልስዎ "አዎን" የሚል ከሆነ ነጥቦቹን በአጭሩ ይግለጹ፤
   ..............................
   ..............................
   ..............................

## አባሪ ሁለት

## የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ምዕራፍ ሁለት፣

1. ስነ-ጽሑፍ ምንድን ነው?
2. ደራሲያን ለምን ይጽፋሉ?
3. በተጻፈውና ባልተጻፈው ስነ-ጽሑፍ መካከል ያለው አንድነትና ልዩነት ምንድን ነው?
4. እስከ ዛሬ ካነበባችኋቸው የስነ-ጽሑፍ ውጤቶች (ልቦለዶች፣ ግጥሞችና ድራማዎች) የምታስታውሱትን ተናገሩ።

ምዕራፍ አራት፣

1. አጭር ልቦለድ ከረጅም ልቦለድ ተለይቶ የሚታወቀው በምንድን ነው?
2. ካነበባችኋቸው ወይም ካዳመጣችኋቸው ልቦለዶች መካከል ከሌሎቹ በበለጠ የምታስታውሱት የትኛው ነው? ይህን ልቦለድ እንድታስታውሱ ያደረጋችሁን ምክንያት ግለጹ።

ምዕራፍ አምስት፣

1. ከግጥምና ከዝርው (ከስድ ጽሑፍ) አንባቢውን ወይም አድማጩን ይበልጥ የሚስበው የትኛው ነው? ለምን ይመስላችኋል?
2. በግጥምና በዝርው ጽሑፍ መካከል ያሉ ልዩነቶች ምን ምን ናቸው?
3. "ግጥም ሙዚቃው ቃና ወይም ዜማ አለው" ሲባል ምን ማለት ነው?
4. ግጥም በሚነበብበት ጊዜ ዜማውን ለመጠበቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት ትላላችሁ? ለምን?

ምዕራፍ ስድስት፣

1. ተውኔት ምንድነው?
2. ካነበባችኋቸው የልቦለድ መጻሕፍት ውስጥ የምታስታውሷቸውን ገጸ-ባህርያት ጥቀሱ።
3. በሬዲዮ እና በቴሌቪዥን በመድረክ ቀርበው ከተከታተላችኋቸው ተውኔቶች ውስጥ የምታስታውሷቸውን ገጸ-ባህርያት ዘርዝሩና ገጸ-ባህርያቱን ለምን እንደምታስታውሷቸው ግለጹ።
4. ገጸ-ባህርያት ማለት ምን ማለት ነው? መቼትስ?
5. ስለተውኔታዊ ቃላት የምታውቁትን ግለጹ።

ምዕራፍ ሰባት፣

1. የአካባቢ ብክለትን የሚያስከትሉ ነገሮች ምን ምን ናቸው? በቡድን ተወያዩና በጋራ ውይይት አንድ አቋም ላይ ድረሱ። የደረሳችሁበትን ከምንባቡ ጋር አገናዝቡ።
2. የአካባቢ ንጽህና አለመጠበቅ፣ ምን ዓይነት ችግሮችን ያስከትላል?
3. የግልና የአካባቢያችንን ንጽህና ለመጠበቅ ከእያንዳንዳችን ምን ይጠበቃል?

ምዕራፍ ስምንት፣

1. መገናኛ ብዙሃን ተብለው የሚጠቀሱት የትኞቹ ናቸው? ዘርዝሩ።
2. አዘውትራችሁ የምትከተሉት የትኛውን መገናኛ ብዙሃን ነው? ለምን?
3. መገናኛ ብዙሃን ባይኖሩ ምን የሚከሰት ይመስላችኋል?
4. ከተለያዩ መገናኛ ብዙሃን መረጃ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው ምን ማድረግ አለበት ትላላችሁ?

ምዕራፍ ዘጠኝ፣

1. የምርጥ ተናጋሪ ጥበብ እንዴት ያለ ነው?
2. ስለ ጥንት የግሪክ ስልጣኔ አንብባችሁ ወይም ሰምታችሁ ታውቃላችሁ?
3. ጥሩ ተናጋሪ መሆን እንዴት ያሉ ጥቅሞች አሉት?
4. አንድ ንግግር የአድማጩን ቀልብ ሊስብ ወይም ላይስብ የሚችልባቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው?

ምዕራፍ አሥር፣

1. ክርክር ከውይይት ወይም ከጭውውት በምን ይለያል?
2. ክርክር ለምን ይካሔዳል?
3. ክርክር ሲደረግ አዳምጣችሁ ታውቃላችሁ? ያዳመጣችሁትን ክርክር ሂደት ምን እንደሚመስል ግለጹ።
4. ክርክር ሲካሔድ ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች ምንድን ናቸው?
5. ስለ ክርክር አካሔድ ማወቅ ምን ጥቅም ይሰጣል ትላላችሁ?

## አባሪ ሦስት

## የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ምዕራፍ አራት፣

1. ታሪኩን ከማንበባችሁ በፊት የገመታችሁት ትክክል ሆነ ወይስ አልሆነም? ለምን? በማስረጃ ግለጹ።
2. በልቦለዱ የእስካሁን ክፍል ምን ምን ነጥቦች ተነሱ?
3. በቀጣዩ የልቦለድ ክፍል በሁለቱ ወንድማማቾች መካከል ምን ምን ክስተቶች የሚፈጠሩ ይመስላችኋል?
4. ታሪኩ በምን መልኩ ይቋጫል ብላችሁ ትገምታላችሁ? ማስረጃችሁስ ምንድን ነው?

ምዕራፍ ስድስት፣

1. ቁስ ታምሩ ይሳካላቸው ይሆን? "ይሳካላቸው ይሆናል" ወይም "አይሳካላቸውም" የምትሉ፣ ካነበባችሁት ውስጥ ማስረጃ በመጥቀስ አብራሩ።

ምዕራፍ አሥር፣

1. በምንባቡ የእስካሁን ክፍል ምን ምን ነጥቦች ተነሱ?
2. ምን አዲስ ነገር ጨበጣችሁ?
3. በቀጣዩ የምንባቡ ክፍል፣ ስለ ክርክር ምን የሚነሳ ይመስላችኋል?

አባሪ አራት
የድኅረ ንባብ ጥያቄዎች



መልመጃዎች

## ክፍል አንድ፡- ንባብ

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡ ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሠረት ተስማሚውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት አንዱ ከስነ-ቃል ሊመደብ አይችልም።
   ሀ) ምሳሌያዊ ንግግር፣
   ለ) እንቆቅልሽ፣
   ሐ) የሥራ ላይ ግጥሞች
   መ) ልቦለድ መጻሕፍት።
2. ስለስነ-ቃል ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ከትውልድ ወደ ትውልድ በቃል ይሸጋገራል።
   ለ) በጽሑፍ ባለመስፈሩ በስነጽሑፍ ስር አይመደብም።
   ሐ) የልዩ ልዩ ኪነቃላዊ ቅርጾች ጥቅል መጠሪያ ነው።
   መ) ራሱን የቻለ የጥናት መስክ ነው።
3. በዘምኑ ጊዜ የተደራሲያን ተግባር ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ከዋኙን ማጀብ፣
   ለ) መልስ መስጠት፣
   ሐ) የስነ-ቃል ቅርጹን በመከወን መምራት፣
   መ) ማዳመጥ፣
4. ለስነ-ቃል ግለሰብ ደራሲ የማንጠቅስለት ለምንድን ነው?
   ሀ) የህዝብ አእምሮና የልማድ ውጤት በመሆኑ፣
   ለ) ምድቡ ከስነጽሑፍ ባለመሆኑ፣
   ሐ) በተለያዩ ጊዜያት የሚከወን በመሆኑ፣
   መ) ደራሲው በሁሉም ዘንድ የሚታወቅ በመሆኑ፣





4. ከሚከተሉት ስለስነ-ቃል ከዋኙ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?
   ሀ) ከዋኙ ከዋና ዋና የስነ-ቃል ባህሪያት አንዱ ነው፤
   ለ) የሚከወንበት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታን ይፈልጋል፤
   ሐ) ከዋኙ የተደራሲያንን መኖር አይፈልግም፤
   መ) ከዋኙ ማህበራዊ ባህርይ አለው።

፪. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል መልሱ።

1. "በጽሑፍ ያልሰፈሩ ነገር ግን፣ በቃል የሚከወኑ የቋንቋ ጥበቦች" ሲል ምን ማለቱ ነው? በምሳሌ አብራሩ።
2. ቀደም ባለው ዘመን "የንቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ" እየተባለ ይተረት ነበር። ዛሬ ዛሬ ደግሞ "የንቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ብሎኬት" ተብሎ ሲተረት ይደመጣል። ይህ ሁኔታ ከስነቃል ባህሪያት የትኛውን ያመለክታል?
3. ከስነ-ቃል ተግባራት አንዱ የሆነውን የማስተማር ተግባር በምሳሌ አስረዱ።
4. ስነ-ቃል ያልተጻፈና በቃል ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፍ እንደመሆኑ የጽሑፍ መስፋፋትና ስልጣኔ ሊያጠፋው ይችላልን? መልሳችሁን በማስረጃ አስደግፋችሁ ተናገሩ።

## ክፍል ሁለት፡- ንግግር

፩. በጥንድ ሆናችሁ የምታውቋቸውን ሦስት ሦስት እንቆቅልሾች በየተራ ተጠያየቁ። መላሹ መልሱን ከሰጠ በኋላ፣ የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተሉን የጠበቀ ማብራሪያ ይስጥ።

ምሳሌ፡-

**ጠያቂ፡** "እንቆቅልህ(ሽ)"

**መላሽ፡** ምን አውቅልህ(ሽ)"

**ጠያቂ፡** "ሃሰራኝ ይሸጠኛል፤ የገዛኝ አይጠቀምብኝም፤ የሚጠቀምብኝ አያየኝም። እኔ ማን ነኝ?"

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ:- ንባብ

፩. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት "እውነት" ወይም "ሐሰት" በማለት ከመለሳችሁ በኋላ ምክንያታችሁን ግለፁ።

1. ስነ-ጽሑፍ የሚለው ቃል በቁሙ ሲታይ የሰው ልጅ ጽሕፈትን ከመፍጠሩ አስቀድሞ የተገለጸባቸውን ቃላዊ ፈጠራዎች ያመለክታል።
2. አንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊ ነው ለመባል በጽሑፍ መቅረቡ ብቻ በቂ አይደለም።
3. በጽሑፍ ሰፍሮ ተቀምጦ በቃላት የተገለጸ ሁሉ ከስነጽሑፍ ይቆጠራል።
4. ስነ-ጽሑፍ በማህበረሰቡ ልዩ ቦታ እንዲይዝ ያደረገው መተላለፊያው በጽሑፍ መሆኑ ነው።
5. የሰው ልጅ ሁል ጊዜም ገጠመኙን ለማውጋት ያለው ፍላጎት ለስነ-ጽሑፍ መኖር እንደ አንድ ምክንያት ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ከሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከቀረቡት አማራጮች መካከል ተስማሚውን መልስ ምረጡ።

1. ከሚከተሉት አንዱ የአንድ ጽሑፍ ኪነጥበባዊ ብቃት መመዘኛ አይደለም።
   ሀ) በአገላለጹ የተዋበ መሆን፣
   ለ) በጽሑፍ አማካይነት መገለጽ፣
   ሐ) ሕይወትን ማሳየት፣
   መ) ማራኪና ሳቢ መሆን፣
2. ከሚከተሉት አንዱ "የተጻፈ ነገር ሁሉ ስነ-ጽሑፍ ነው" የሚሉ ወገኖችን ሀሳብ አያንጸባርቅም።
   ሀ) የዕለት ውሎ ማስታወሻና የሥራ ደብዳቤዎች ከስነ-ጽሑፍ ይቆጠራሉ።





   ለ) በጽሑፍ ያልሰፈረ ነገር ስነ-ጽሑፍ ሊባል አይችልም።
   ሐ) አንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊ መሆኑ የሚረጋገጠው በጽሑፍ በመስፈሩ ነው።
   መ) የአንድ ጽሑፍ ስነጽሑፋዊነት መለኪያው ኪነጥበባዊ ብቃቱ ነው።
3. ከሚከተሉት አንዱ ለስነ-ጽሑፍ መኖር ምክንያት አይደለም።
   ሀ) ደራሲያን ለሰው ልጅ ያላቸው ጥልቅ ፍቅርና እሱን ለማወቅ የሚያደርጉት ጥረት፣
   ለ) የሰው ልጅ ገጠመኙን ለማካፈል ያለው ፍላጎት፣
   ሐ) ድርሰትን ሽጦ ገንዘብ የማግኘት ፍላጎት መኖር፣
   መ) የሰው ልጅ ለውበት ጥልቅ ፍቅር ያለው መሆን፣
4. "በጽሑፍ የተገለጸ ሁሉ ስነ-ጽሑፍ ነው" የሚሉ ወገኖች ለአቋማቸው ዋና መመዘኛ የሚያደርጉት ምንድን ነው?
   ሀ) በጽሑፍ መስፈርና አለመስፈር፤
   ለ) በፈጠራ መንገድ መጻፍና አለመጻፍ፤
   ሐ) ህይወትን እውነትና ፈጠራን ባንድ ላይ መያዝ አለመያዝን፤
   መ) ያልተጻፈ ስነ-ጽሑፍ መኖርን፤
5. "የስነ-ጽሑፍ ዋና ጉዳይ ሰው ነው" ሲባል፣ ምንን ለማመልከት ነው?
   ሀ) ከሰው ልጅ ገጠመኝ የሚቀዳ መሆኑን፤
   ለ) ፈጣሪው ሰው መሆኑን፤
   ሐ) የሚጻፈው ለሰው መሆኑን፤
   መ) ሁሉም መልስ ናቸው

፫. በሚከተሉት ዓረፍተነገሮች ውስጥ እየተሰመረባቸው ለቀረቡ ቃላት አገባባዊ ፍች ከሰጣችሁ በኋላ፣ በሰጣችሁት ፍች መሠረት የራሳችሁን ዓረፍተነገር መስርቱ።

**ምሳሌ፦**

በዚህ ምዕራፍ ደግሞ የተጻፈውን ስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖር ምክንያት እንመከለታለን።

አገባባዊ ፍች፣ ክፍል

ዓረፍተነገር፣ በዚህ ክፍል ደግሞ የተጻፈውን ስነ-ጽሑፍ ምንነትና የመኖር ምክንያት እንመለከታለን።

1. ስነ-ጽሑፍ በጽሑፍ የተቀረፀውን የቋንቋ ጥበብ ይመለከታል።
2. ሰዎች ስለህይወት ያላቸውን ግንዛቤ በቋንቋ አማካይነት ያንፀባርቃሉ።
3. ስነ-ጽሑፍ በጽሑፍ መስፈር ብቻ ሳይሆን ኪነ ጥበባዊ ብቃት ሊኖረው ይገባል።
4. ስነ-ጽሑፍ የህይወት ገበመኘ ይንፀባረቅበታል።
5. ሰው ስለህይወት የተገነዘበውን በጎም ሆነ ክፉ ነገር ለመስሉቹ ማካፈል ይፈልጋል።
6. ሕይወትን እነሱ እንደተመለከቷት ለሌላው ለማስተላለፍ ይተጋሉ።
7. የስነ ጽሑፍ ምንጩም፣ ፈጣሪውም፣ ተቀባዩም ሰው ነው።

፬. በሚከተሉት ከምንባቡ ለወጡ ቃላት ቀጥተኛ ፍቻቸውን ከሰጣችሁ በኋላ፣ ዓረፍተነገር ሥሩባቸው።

**ምሳሌ፦**

በቁሙ = በህይወት እያለ

ዓረፍተነገር= አባቱ በቁሙ የተናዘዘልንን ሀብት ከእህቶቹ ጋር ተከፋፈልን።





| | | |
|---|---|---|
| 1. ፈጠራ | 5. ህይወት | 9. ቁርኝት |
| 2. ኪነጥበብ | 6. ዝርው | 10. ትኩረት |
| 3. አግጊ | 7. ግንዛቤ | 11. መጋተር |
| 4. ቅርጽ | 8. መማረክ | 12. መትጋት |

፭. ከዚህ በታች ከቀረቡላችሁ ርዕሰ ጉዳዮች አንዱን ምረጡና በአካባቢያችሁ ወደሚገኝ የህዝብ ቤተመጻህፍት ወይም ወደትምህርት ቤታችሁ ቤተመጻህፍት በመሔድ ከመጻህፍት ከመጽሔቶችና ከጋዜጦች መረጃ ሰብስቡ።

*መረጃ የሚሰበሰብባቸው ርዕሰ ጉዳዮች፣*

ሀ) ከአስር ያላነሱ የልቦለድ መጻሕፍትን በማገላበጥ፦ የደራሲውን ስም፣ የመጽሐፉን ስም፣ የህትመት ስፍራ፣ አሳታሚ ድርጅቱንና የመጽሐፉን የገጽ ብዛት ዝርዝር አቅርቡ።

ለ) ልዩ ልዩ መጽሔቶችን በማገላበጥ ከአስር ያላነሱ ጽሑፎችን መርጣችሁ፦ የጽሑፉን ባለቤት ስም፣ የህትመት ዓመተ ምህረትና ወር፣ የጽሑፉን ርዕስ፣ የመጽሔቱን ስም፣ በመጽሔቱ የሰፈረበትን ገጽ (ከገጽ_ እስከ _በማለት) በመዘርዘር አቅርቡ።

ሐ) የተለያዩ ጋዜጦችን በማገላበጥ የሚያጋጥሟችሁን ከአስር በላይ ተረትና ምሳሌዎች ከመዘገባችሁ በኋላ፦ ተረትና ምሳሌዎቹን ያገኛችሁባቸውን ጋዜጦች ስም፣ የታተሙበትን ዓመተ ምህረት፣ ወርና ቀን በመዘርዘር አቅርቡ።

ሽማግሌው የአስር አለቃ የትምህርት ቤት ዳይሬክተር የሆነውም፣ ለአካባቢው ህዝብ አንድ ውለታ ጥሎ ለማለፍ ስለፈለገ ነበር። በህጻናቱ ጠባይ ላይ እንዲቀረጽ የሚፈልገው ነገር ቢኖር፣ መጀመሪያውም መጨረሻውም ፍቅር ነበር። እናም፣ ሰው ማፍቀርን ለታዳጊዎች አስተማረ፡ ህጻናት፣ እየመጡ እንደጓደኛቸውና እንደአባታቸው ያጫውቱት፣ ችግራቸውንም ያወያዩት ነበር።

*(ቬኔዴም የታወቁ አጫጭር ልቦለዶች፣ ትርጉም ለምለም አበበ) ለትምህርቱ እንዲመች መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት የቀረበ።*

## መልመጃዎች

### ክፍል አንድ፡- ንባብ

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በልቦለዱ የመጀመሪያ ክፍል መሰረት ትክክል ከሆኑ «እውነት» ስህተት ከሆኑ ደግሞ «ሐሰት» በማለት መልሱ፤ የመልሳችሁንም ምክንያት ከጽሁፉ ውስጥ በመፈለግ ግለጹ።

1. የውርስ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ የሆነው፣ በሁለቱ ወንድማማቾች አለመስማማት ምክንያት ነበር።
2. በወርቅ ሰዓቱ ጨረታ ብዙ ሰዎች ተሳትፈዋል።
3. ለዘነበ የጨረታ አሸናፊነቱን ያበሰረው የጨረታው መሪ አልነበረም።
4. የበልዩን ላም የገደላት ዘነበ ለመሆኑ ማረጋገጫ አለ።
5. ጨረታውን ሁለት ሺ አንድ መቶ ብር ያደረሰው በልዩ ነበር።
6. ዘነበ ማሸነፉ ሲነገረው የተጸጸተው፣ ለሰዓቱ የሚከፍለው ገንዘብ በመብዛቱ አልነበረም።
7. ዘነበ ወንድሙ ቤት ድረስ በመሄድና "ሰዓቱን ከሆነ የፈለግህ መውሰድ ትችላለህ" በማለት ሲናገር ከንፈሩ የተንቀጠቀጠው ሰዓቱን ለመስጠት ስለጨነቀው ነበር።
8. ዘነበ የተጎሳቆለው አልኮል በብዛት በመጠጣቱ ነበር።
9. ወንድማማቾቹ ተጣልተው በነበሩባቸው ዓመታት ሁለቱም ደስተኞች አልነበሩም።
10. የበልዩ ባለቤት ወንድማማቾቹ እንዲስማሙ ከፍተኛ ፍላጎት ነበራት።






ለ. ልቦለዱን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች በቃል መልሱ።

1. የውርስ ንብረቱ በጨረታ እንዲሸጥ የሆነበት ምክንያት ምንድን ነው?
2. ዘነበ ከሳቀ በኋላ፣ "ሶስት ሺ ብርና የኔንም ወንድምነት ከዚሁ ጋር" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አብራሩ።
3. ለበልዩ ድሃ መሆን "ምክንያቶች ናቸው" የምትሏቸውን ዘርዝሩ።
4. የአካባቢው ባለስልጣኖች ዘነበን በቃጠሎው የጠረጠሩት ከምን ተነስተው ነው?

ሐ. በልቦለዱ ባለታሪኮች ላይ የተከሰተው ችግር ከመነሻው እንደይፈጠር፣ ችግሩ ከተፈጠረም በኋላ በቀላሉ እንዲፈታ ምን መደረግ ነበረበት ብላችሁ ታስባላችሁ? በቡድን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩበትና የደረሳችሁበትን ድምዳሜ በየቡድን መሪያችሁ በክፍል አቅርቡ።

መ. ዋና ዋና የሆኑትን የልቦለዱን ድርጊቶች በቅደም ተከተል አስቀምጡ። ይህንን ስታደርጉ ጥንድ ጥንድ ሆናችሁ በመወያየትና የሚከተለውን ምስል ደብተራችሁ ላይ በመጠቀም ይሁን።



## ክፍል ሁለት:- ማዳመጥ

፩ በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በጥንድ /በቡድን/ ተወያዩና የደረሳችሁበትን ማጠቃለያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. ፊት ለፊት ከሚደረግ የሀሳብ ልውውጥና በስልክ ከሚደረግ ንግግር በቀላሉ አዳምጦ ለመረዳት የሚያስችለው የትኛው ነው? ለምን?
2. አንድን ንግግር ወይም ውይይት አዳምጦ ለመረዳት የሚጠቅሙና የማይጠቅሙ ነጥቦችን በሚከተለው ስእላዊ መግለጫ አሳዩ፡፡

**ለአዳምጦ መረዳት**

- **የሚጠቅሙ**
  - ንግግርን በሙሉ ስሜት ማዳመጥ
- **የማይጠቅሙ**
  - የሚያደምጡትን ሁሉ በማስታወሻ ለመያዝ መሞከር

፪ መምህራችሁ አንድ አጭር ጽሑፍ ያነቡላችኋል፡፡ በጥሞና አዳምጡና በ«ሀ» ስር የተገለጹትን ገለጻዎች በ«ለ» ስር ከተዘረዘሩት ተገላጮች ጋር አዛምዱ፡፡

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. በፊት ለፊትና በስተጓዳ አለ | ሀ. ሶፋ |
| 2. ድንክዬ ጠረጴዛ | ለ. ከዘራ |
| 3. ጠየም ያለ | ሐ. በር |
| 4. ወጪ ገቢውን የሚታዘብ አዛውንት የሚመስል | መ. ስልክ |
| 5. እንደ ጅብራ የተገተረ | ሠ. አልጋ |
| 6. የተሞሸረ | ረ. መስኮት |
| | ሰ. ቁምሳጥን |





## ክፍል ሦስት:- ንግግር

፩. ከዕቦለድ ወይም ከሌሎች የፈጠራ ሥራዎች ጋር በተያያዘ የተደረጉ ውይይቶችን፣ የተሰነዘሩ አስተያየቶችን ወዘተ. ከሬዲዮ ወይም ከቴሌቪዥን አዳምጣችሁ «ጠቃሚ ሐሳብ ነው» የምትሉትን በራሳችሁ አባባል ጽፋችሁ ለክፍል አቅርቡ፡፡

ጽሑፋችሁ - የድርጊትና የጊዜ ቅደም ተከተልን የጠበቀ፣
- መንስኤና ውጤትን ያገናዘበ መሆኑን አረጋግጡ፡፡

**ምሳሌ**

- መጸነስ፣ ማርገዝ፣ መውለድ (የድርጊት ቅደም ተከተልን የጠበቀ፣)
- ባለፈው ዓመት፣ ባለፈው ወር፣ ባለፈው ሳምንት፣ ዛሬ፣ ነገ (የጊዜ ቅደም ተከተልን የጠበቀ)
- ታሞ ሞተ (መንስኤና ውጤትን ያገናዘበ)

፪. በአጭር ልቦለዱ እንደታየው በሁለቱ ዋና ገፀባህርያት መካከል ከፍተኛ ያለመግባባት ተፈጥሯል፡፡ ለዚህ ተጠያቂው ማነው? ዘነበ ወይስ በልዩ? አንደኛ ውን ደግፋችሁ ሌላውን በመቃወም ተከራከሩ፡፡ በክርክሩ ያልተሳተፋችሁ ደግሞ በተከራካሪዎች የሚሰነዘሩ ሃሳቦች የቱን ያህል ምክንያታዊ መሆን አለመሆናቸው ላይ አስተያየት በመስጠት ተሳተፉ፡፡

**በክርክር ጊዜ ለእነዚህ ነጥቦች ትኩረት ስጡ፣**

- በቂ ዝግጅት ማድረግ፣
- ከርእሱ ጋር የተዛመዱ ሐሳቦችን ማቅረብ፣
- የሚቀርቡ ሐሳቦች በማስረጃ የተደገፉ መሆኑን ማረጋገጥ
- ተራን ጠብቆ መናገር፣
- የሌላውን ሰው ሐሳብ አለማንቋሸሽ፣
- ለተቃዋሚ ሐሳብ ተገቢ መልስ መስጠት፡፡

### መልመጃዎች

## ክፍል አንድ፦ ንባብ

ሀ. ግጥሙን መሰረት በማድረግ ትክክል ከሆነ እውነት ትክክል ካልሆነ ሐሰት በማለት መልሱ።

1. እንደ ግጥሙ ከሆነ ባለታሪኩ ቃል ሲገባ የመጀመሪያ ጊዜው አይደለም።
2. ባለ ብዙ ልሳን ሲል ንግግር ታበዛለሽ ማለቱ ነው።
3. "ያን ስምሽን ፍቶ" የሚለው ኋላ ቀርነትን ነው።
4. ባለ ታሪኩ ሀገሩን ለማልማት ሥራ ውስጥ ገብቶ በመንቀሳቀስ ላይ ይገኛል።
5. "መከዳዬ ነሽ" የሚለውን ሐረግ የተጠቀመው ሀገሩ መኖሪያው መሆኗን ለማመልከት ነው።

ለ. በግጥሙ መሠረት ለተከታዩቹ ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጡ።

1. ኢትዮጵያን ለደፈራት ጠላት መነሻ ምክንያት የሆነው የትኛው ነው?

    ሀ) ረሀብ ሐ) እርዛት
    ለ) ጦርነት መ) አለመማር

2. ባለታሪኩ "ፊቱን ሳልመልሰው" ሲል ምን ማለቱ ነው?

    ሀ) ያለፈውን ሳልመለከት
    ለ) ሳላፈገፍግ
    ሐ) ከኋላዬ ያለውን ሳልመለከት
    መ) የልጅነት መልኬን ሳልመለከት

3. "ያን ስምሽን ፍቶ" የሚለው የትኛውን ስሟን ነው?

    ሀ) የጥንት ስልጣኔና ክብሯን ሐ) ኢትዮጵያ የሚለውን
    ለ) ለምለም ሀገር መሆኗን መ) ኋላ ቀርነቷን

4. እንደ ተራኪው አገላለጽ ኢትዮጵያን የማይመለከተው የትኛው ነው?

    ሀ) ተረጅነት ሐ) የጥንት ገናናነት
    ለ) ቅኝ ተገዢነት መ) ኋላ ቀርነት





5. ገጣሚው ሃገሩን "ብርኩማዬ ነሽ" ሲል ምኑ መሆኗን ለማመልከት ነው?

    ሀ) መኖሪያው ሐ) ትውልድ ቦታው
    ለ) መመገቢያው መ) መመኪያው

6. "ክንዴን አፈርጥሜ" ሲል ምን ማለቱ ነው?

    ሀ) ክንዴን አወፍሬ ሐ) ክንዴ አፈር ተጠምቶ
    ለ) ክንዴን ተማምኜ መ) ክንዴን አጠንክሬ

ሐ. ግጥሙን መሠረት አድርጋችሁ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጡ።

1. ጸሐፊው ኢትዮጵያን «ባለብዙ ልሳን፣ እናት የብዙሐን" ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ አብራሩ።
2. ገጣሚው "እልል በይ እማዬ" የሚልበት ምክንያት ምንድን ነው?
3. "የተደፈው ስምሽ ዳግመኛ ታድሶ" የሚለው ስንኝ ምንን ያመለክታል?
4. ገጣሚው ክንዱን የሚያዝለውና ከትግል ፊቱን የሚያዞረው መቼ ነው?
5. በገጣሚው እምነት ራስ መቻል በምን ይገለጻል?

## ክፍል ሁለት፦ ንግግር

1. "ዳግመኛ ቃል ኪዳን" በሚል ርዕስ በቀረበው የገጣሚው ሀሳብ ላይ ትስማማላችሁ? ወይስ የሌላ ችግር ነው የተነሳው? በጥንድ በጥንድ ተወያዩና አቋማችሁን ከምክንያቶቻችሁ ጋር አቅርቡ።
2. የመረጣችሁትን አንድ ግጥም ወይም ዝርው (ስድ ጽሑፍ) አጥንታችሁ በቃል (ጽሑፉን ሳትመለከቱ) ለክፍላችሁ አቅርቡ። መልዕክቱንም ተናገሩ።

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ ሙሉ በሙሉ የራሴ ሥራ ስለመሆኑ በፊርማዬ አረጋግጣለሁ።

ተሻለ ክፍሌ

ፊርማ

ሰኔ፣ 2005 ዓ.ም.